

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌባ ወዳ ወሸኙ

ደራሲ—ነጋ፡ብ ማሀፉ፣ህ

ተርጓሚ—አህመድ አህመዲን

መጋቢት 1982

t.me/OLDBOOKSPDF

መብቱ — የተጠበቀነው
All – Right Reserved

ምሥጋና

ይህንን መፅሐፍ ተርጉሚ ለማቅረብ የግብፅ ኤምባሲ የማስታወቂያ ቢሮ ስለደራሲው ሥራዎች የበለጠ ለመረዳት እንድችል አስፈላጊውን የማቴሪያል እርዳታ ስላደረገልኝና የቅርብ የሥራ ባልደረቦቹም የሞራል ድጋፍ በመስጠት እንድገፋበት ስላበረታቱኝ ከልብ አመሠግናለሁ ።

አህመድ አህመዲን

t.me/OLDBOOKSPDF

መግቢያ

ደራሲው የስነ ዕውፍ የሞቪል ሽልማት ከመሸለማቸው በፊት ለአገራችን አንባቢዎች እምብዛም ያልታወቁ ስለሆኑ ለማስተዋወቅ ያህል የሚከተሉትን ቁም ነገሮች ስለ ደራሲው ለማቅረብ እንዲፈቀድልኝ በትህትና እጠይቃለሁ። በመዕሀፉ ውስጥ የተጠቀሱት የዘመን አቆጣጠርም እንደ አውሮፓውያን መሆኑንም ለመጠቆም እፈልጋለሁ ።

= ነጂብ ማሀፉዝ አብደል አዚዝ በታህሳስ 11/1911 በጀማሊያ ቀበሌ ካይሮ ተወለዱ ።

= አግብተዋል ፡ የሁለት ሴት ልጆች አባት ናቸው ።

= የመጀመሪያውን ትምህርታቸውን በካይሮ በሁሰይንያ ት/ቤት ፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ፋዐድ የመጀመሪያ ት/ቤት ፡ ከዚያም ወደ ፋዐድ ዩኒቨርስቲ (አሁን ካይሮ ዩኒቨርስቲ) በሚባለው በአርት ፋኩልቲ ተማሩ ።

= በ1934 በፍልስፍና ትምህርት በዲግሪ ተመረቁ ።

= ድርሰት የጀመሩት በሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበሩበት ጊዜ ነው ።

= የመጀመሪያ ዕሁፋቸው በነሀሴ 3/1934 አዲስ መዕሔት በተባለው ታትሞ ወጣ ።

= በ1939 የመጀመሪያው አጫጭር ልቦለድ ድርሰታቸውን የያዘው "ሐምስ ኡልጅኑን" የዕብደት ሹክሹክታ የተባለው መዕሐፋቸው ታትሞ ወጣ ።

= ከ1934 እስከ 1972 የመንግሥት ሠራተኛ ሆነው ሠርተዋል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

= በመጀመሪያ የሠሩት በንጉሥ ፋዕድ ዩኒቨርስቲ ሲሆን ፡
ቀጥሎም በባህል ሚኒስቴር አማካሪ ሆነው አገልግለዋል ።

ለስመ ጥሩው ደራሲ ለነጂብ ማህፉዝ የደራሲነት ዝንባሌ መጻበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉላቸው አንዳንድ የታወቁ ደራስያን የሚከተሉት ናቸው ።

ከግብፅ ጣሃ ሁሴን ፡ አባስ ኤል አቃድ ፡ አ.ብራሂም አልማዚኒ ፡ መ.ሀመድ ሁሴን ሃይካል ፡ ተውፊቅ አልሀኪምና ያህያ ሐቂ ናቸው ።

ከውጭው አገር ደራስያን ደግሞ ፡

ዊልያም ሼክስፒር ፡ ቺኮ ቭ ከፍካ ፡ ጆይስ ቶልስቶይ ፡ ዶስቶይቭስኪ ፡ የጂን አ ኒል ፡ አ.ብሴንና ታጎር ናቸው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የንጂብ ማህፉዝ ድርሰቶች

ንጂብ ማህፉዝ በልጅነታቸው በጋማሊያ ቀበሌ ያሳለፉት ጊዜ በድርሰታቸው ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። በድርሰታቸው የተጠቀሱት ወንዶችና ሴቶች በዚህ አካባቢ በተለያዩ ጊዜዎች የነበሩ ሰዎች ናቸው ። በጣም ከታወቁ ድርሰቶቻቸውም መካከል "በያነ አልቀስሬን" (በሁለቱ ፎቆች መካከል) የሚባለውን መፅሐፍ ለመግፍ አራት ዓመት ያህል ጊዜ ወስዶባቸዋል ። የካይሮ በጎ ቤቶች ፡ የጥንትም ሆኑ አዳዲሶች ፡ እንዲሁም በጣም ጠባብ የሆኑ የካይሮ ከተማ የሰፈር መንገዶችና በነዚህ ሰፈሮች ውስጥ የሚኖሩ ጐስቋሎች ህይወት ስንጂብ ማህፉዝ ድርሰቶች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል ። በአገር ውስጥም ሆነ በወጭ አገር ታዋቂነትን ያተረፈላቸው ድርሰት "አልሱላሲ" (ሳልሳዊ) ሲሆን ይህ ባለ ሶስት ተከታታይ ጥራዝ መፅሐፍ በግብፅ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል ያለውን ተጨባጭ የፖለቲካና የሶሻል ሁኔታዎችን የሚገልፀው ድርሰት ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የነጂብ ማህፉዝ የዕለት ተዕለት ሥራዎች

ነጂብ ማህፉዝ የዕለቱን ሥራ የሚጀምሩት በአግር ጉዞ ሲሆን ከቢታቸው ተነስተው በሉጉዛ ቁበሲ ወደ ታህሪር ለደባባይ ይሂዱና ከዚያም በይንበኝነት ነጣሚታወቁባቸው ቡና ቤቶች ይደርሳሉ ። ብዙውን ጊዜም ከተወለዱበት ለካባቢ ወደሚገኘ ውና ሬሻዊ ቡና ቤት በመሳል ወደሚታወቀው መዝናኛ መሂድን ያዘወትሩ ነበር ። በለሁኑ ጊዜ ወደ ታህሪር ለደባባይ ወደሚገኙት ቡና ቤቶች ቡና ወይም ሻይ ለመጠጣት ጧት ጧት ሁለት ሰዓት ያህል ያሳልፉሉ ። ቀጥለውም የተለመደውን የጧት የአግር ጉዞ በካይሮ መንገዶች ይደርጋሉ ። ቡና ከጠጡ በኋላ የጧት ጋዜጦችን ያነባሉ ። ከዚያም በትርፍ ሰዓት ወደሚሠሩበት ወደአልአህራም ጋዜጣ ማተሚያ ቤት በአግራቸው ይመራሉ ። ሥራቸውን ጨርሰው ለምሳ በአግራቸው ወደቢታቸው ይመለ ሳሉ። ከምሳ በኋላም ለጭር አረፍት ያደርጋሉ ። በ11 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ነጂብ ማህፉዝ ከእንቅልፋቸው ይነሱና መፃፉ ይጀምራሉ። ወይም ወደተለመደው ቡና ቤቶች ይሂዳሉ ። ከሚወዷቸው ጓደኞቻቸው "ለለሀራፊሽ" ከሚባሉ የኪነት ሰዎች ማለት ለርቲስቶች፡ ደራስያን ፡ የሲኒማ ፊልም ዳይሬክተ ሮች ፡ ተዋንያንና የቅኔ ሰዎች ጋር ስለ ኪነ ጥበብና ስነፅሑፍ እንዲሁም ስለተለያዩ ጉዳዮች ውይይት ያደርጋሉ ። በበጋ ወራት

t.me/OLDBOOKSPDF

ነጂብ ማህፉዝ ለአረፍተ ወደ አሌክሳንደሪያ ይሄዳሉ ። ከዚያም ከሰኔ ወር መባቻ አስከ ጥቅምት ወር መጀመሪያ ድረስ ከዚያ ይቀያሉ ። በአሌክሳንደሪያ ከተማ ነው "ሊባውና ውሾቹ" የተባለው መፅሐፉቸውን የዛሬ 28 ዓመት ገደማ የፃፉት ። ነጂብ ማህፉዝ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው ወደ ውጭ አገር የሄዱት ። አንድ ጊዜ ወደ ዩጐዝላቪያ ፡ ሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ወደ ሰሜን የመን ። ሁለቱም ጉብኝቶች ለመንግሥት ሥራ ነበር ።

ነጂብ ማህፉዝ ከ60 በላይ የሚሆኑ መፅሐፍትን አንዲሁም በርካታ ቁጥር ያላቸው ሌሎች ድርሰቶችን ፅፈዋል ። ከነዚህም መካከል (አል ሊስ ወል ኪሳብ) "ሊባውና ውሾቹ" የሚለው ይገኝበታል ። የነጂብ ማህፉዝ በርከት ያሉ መፅሐፎች ወደ እንግሊዝኛ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ጀርመንኛ ፡ ስዊድን ፡ ራሽያ ፡ ቻይና ፡ ጃፓንና ስፓኒሽ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

መቅድም

ነጂብ ማሀፉዝ (አልሊሰ ወልኪላብ) "ሌባውና ውሾቹ" የተባለው መፅሐፍ የገፉት በአሌክሳንደሪያ ከተማ በ1961 መሆኑን በመግቢያው የተገለፀ ሲሆን ፡ መፅሐፉን እንዴት እንደፃፉት የሳቸው የቅርብ ጓደኞቹው የሆኑት ደራሲ ያህያ ሐቂ እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል ።

በካይሮ ከተማ ከፍተኛ ሽብር ፈጥሮ የነበረው የታወቀው ሌባ መሀመድ ሱለይማን የተባለው የዛሬ 28 ዓመት ገደማ በጊዜው ትልቅ ዜና ከመሆኑም በላይ ፖሊሶችን ግራ አጋብቶ ነበር ። በሀገሩም ዘንድ ደጋፊዎች አሳጣም ። (አልአክባር) የተባለውም ጋዜጣ በዚህ ጉዳይ እጁን በማስገባት ማንኛውም ሰው የሌባውን መደበቂያ ከጠቆመ ከፍተኛ የገንዘብ ሰጠታ የሚደረግለት መሆኑን ገለፀ ። ይህ ሁኔታ ደራሲው በልቦለድ መልክ አሳምረው ፅፈውታል ።

በመሆኑም መፅሐፉ በአንድ ሀብረተሰብ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሕይወት ገፅታዎችንና የኑሮ ውጣ ውረድ ፡ ፍቅርና ጥላቻን ፡ ማማንትና ማጣትን ፡ መወደድና መጠላትን ፡ ቁልጭ አድርጐ የሚያመለክት ጥሩ መልእክት ሆኖ ስላገኘሁት ፡ ተተርጉሞ ቢቀርብ የኛም ሀብረተሰብ ቁም ነገር ያገኝበታል ፡ ትምህርት ይገበይበታል የሚል እምነት ስላሳደረብኝ፡ ከነጂብ ማሀፉዝ ምርጥ ስነ ፅሑፍ ሥራዎች መካከል "ሌባውና ውሾቹ" የተሰኘውን ይህን መፅሐፍ ለሀብረተሰቡ በሚጥም መልኩ ተርጉሚ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ ።

በፅሑፉ ውስጥ አልፎ አልፎ ስሞችና ቅፅሎች በአረብኛ ቋንቋ ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ዝርዝራቸውን ከነትርጉማቸው አያይዠ አቅርቢአለሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የኖቬል ሽልማት

የስዊድን አካዳሚ በወሰነው መሰረት በ1988 የስነ ፅሑፍ የኖቬል ሽልማት ለግብፃዊው ደራሲ ለነጂብ ማህፉዝ እንዲሰጥ ተደረገ ።

በካይሮ የሚገኘውም የስዊድን ኤምባሲ ስለዚሁ ጉዳይ በዕለቱ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል ።

"የግብፅ ታላቅ ደራሲ ከፍተኛ የስነ ፅሑፍ ግኝት አስገኝተዋል ። በልቦለድ (ኖቭልስ) የስነ ፅሑፍ ድርሰታቸው የዓረብን ስነ ፅሑፍና ባህል እንዲሻሻል ረድተዋል ። ከዚህም አልፎ ሥራቸው ወደቀረው የዓለም ክፍል ተዳርሷል ። የነጂብ ማህፉዝ ድርሰቶች ከታወቀው የእንግሊዝ ደራሲ ከቻርለስ ዲክንስ ድርሰቶች ጋር የሚወዳደሩ ናቸው ። ዲክንስ ስለ ለንደን ከተማ በዝርዝር ሲፅፍ ነጂብ ማህፉዝ ስለ ካይሮ ከተማ መንገዶችና በዚያ አካባቢ ስለሚኖሩ ሰዎች ሰፋ አድርገው ፅፈዋል ። ሥራዎቻቸው የራሽያው ደራሲ ዶስቶይ ፊስኪ ስለ ቅዱስ ጴጥሮስ ከተማ ከፃፈው ጋር ተመሳሳይነት አለው ። ከፈረንሳዊ ደራሲ ኢሚልዞላ ስለ ፓሪስ ከተማ ከፃፈው ይመሳሰላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

—1—

ከእሥር ቤት ወጥቶ እንደገና የነፃነት አየር መተንፈስ ጀመረ። አየሩም በጣም የሚያቃጥል አቧራማ ነበር ። ከራሱ በስተቀር አንድም ስለ እሱ የሚያስብለት ሰው አልነበረም ። ከንብረቱም ያገኘው ነገር ቢኖር ሰማያዊ ሙሉ ልብሱና የላስቲክ ጫማውን ብቻ ነበር ። ብዙ ስቃዮችን አምቆ የያዘለትን የወህኒ ቤት በር ተራምዶ ሲወጣ ዓለም እንደገና መንቀሳቀስ የጀመረች መሰለው ።

ፀሐይ ያቃጠለቻቸው ገመዳናዎች ፡ እንደ ዕብድ የሚበሩ መኪናዎችና ፀጥ ረጭ ብሎ የነበረው ሕዝብ እንደገና መንቀሳቀስ የጀመሩ ይመስላል ። አንድም ሰው የደስታ ፈገግታ አይታይበትም ። ማን ማን እንዴሱ ከውድ ሕይወቱ ላይ አራት ዓመት ሙሉ የተሰቃየና በክህደት ምክንያት ገዜውን በከንቱ ያሳለፈ አለ? ከጠላቶቹ ጋር የሚጋጭበት ሰዓት እየደረሰ ስለሆነ ንዴቱ መፈንዳቱ አይቀርም ። የካዱትም ሰዎች ቢሆኑ ከእሥር ቤት ከወጣ ይፈጅናል በሚል ፍርሃት ከሞት አፋፍ ላይ መሆናቸው አይጠረጠርም ። "ክህደት ለፈፀሙት ሥራ ዋጋዋን ማግኘት አለባት ። ነበዊያና ዓሊሽ ስማችሁ በአዕምሮዬ ተቀርጿል ። እናንተም

t.me/OLDBOOKSPDF

ለዚሁ ለዛሬው ቀን ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደምታደርጉ አልጠራ ጠርም ። ለመሆኑ በእናንተ ቤት የወሂኒ ቤቱ በር የማይከፈት መስሏችሁ ነበር? በተጠንቀቅ ላይም እንደሆናችሁ ይገባ ኛል። ግን እንደገና ከእናንተ ወጥመድ አልገባም ። እንዲያ ውም አመቺ ጊዜ ጠብቄ እንደ ድንገተኛ ሞት ከተፍ ነው የምልባችሁ ። ስለ ሰናእ ልጇስ አዲስ ነገር ይኖር ይሆን? የእሷ ሀሳብ በአዕምሮዬ ውስጥ ሲተራመስ የአየሩ ሙቀት ፡ አቧራው ፡ ጥላቻና ሕመም በሙሉ ይሰወራሉ ። ፍቅሯም መንፈሴን በዝናብ እንደታጠበ ሰማይ ያፀዳዋል።" እያለ ሰዒድ ከራሱ ጋር ከርከር ጀመረ ።

ቢሆንም ሕፃኗ ልጅ ስለ አባቷ ምን ማወቅ ትችላለች? ከዚህ መንገድ ከመንደሯች የተሻለ የምታውቀው ነገር አይኖርም ። ሆኖም ሰዒድ አራት ዓመት ሙሉ በእሥር ቤት በቆየበት ጊዜ ልጁ ከአዕምሮው ተሰውራ አታውቅም ። እንደህልም ትታየው ነበር ። ዕድሉ ካማረ ከዕለታት አንድ ቀን በፍቅር ከልጁ ጋር አብሮ ለመኖር ይችል ይሆን? ነበዊያና ዓሊሽ የፈፀሙት በደልና አሰጠሊ ትዝታስ ይረሳ ይሆን? ሰዒድ በሀሳብ ተውጦ ጠላቶቹ ትዝ ሲሉት ግልፍ አለውና ያለፈውን የጀብደኝነት ታሪኩን አስታውሶ እንዲህ አለ ።

"ባለህ ጥበብና ችሎታ ሁሉ የመጠቀምን ነገር እወቅበት ። በወሂኒ ቤት ሆነህ ያሳለፍከውን ስቃይና መከራ ሁሉ ስለምታስታውስም ከእንግዲህ የበቀል ከንድህ ጠላቶችህን የሚያደባይ መሆኑን አትዘንጋ ። እንግዲህ ምን ይዋጣችሁ እንደ ዓሣ በውሃ የሚሰምጥ ፡ እንደ አሞራ በአየር የሚከንፍ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ አይጥ ግንቡን እየቧጨረ የሚወጣ ፡ እንደ ጥይት ጠንካራ በሮችን በስቶ የሚሾልክ ወንድ መጣባችሁ!"

"ለመሆኑ በምን ዓይነት ሁኔታ እንገናኝ ይሆን? ዓይኖ ቻችንስ እንዴት ይገጣጠሙ ይሆን? ዓሊሽ እንደ ውሻ እግሬ ስር ወድቀህ ትተሻሸ የነበረውን ረሳህ ወይ? ማነው በሁለት እግሮችህ እንድትቆም ያደረገህ? ማነው ከቁርጥራጭ ሲጃራ ለቃሚነት አውጥቶ ሰው ያደረገህ? አንተ ብቻ አይደለህም የረሳኸው ነበዊያም ብትሆን ረስታዋለች ፡ ያቺ በከሀዲት በበሰበሰ ጭቃ ላይ የበቀለችው ቃል ኪዳን አፍራኗ! ። በዚህ በጨለማ ዓለም ውስጥ ሰናእ ያንቺ ፊት ብቻ ነው ፈካ ብሎ የሚታየኝ ። በቅርቡ ከአንቺ ለመገናኘት ምን ዓይነት ዕድል እንዳለኝ እሞክራለሁ ።"

"ደህናዎቹንም ሆነ አንዳንድ ደባ የሚካሄድባቸውን ግራና ቀኝ የሚገኙ የመጠጥ ቤቶች አልፌ የተሽከርካሪዎችና የትራሞች ድብልቅልቅ ጩኸት ከሚሰማበት ከዋናው መን ገድ ገባሁ ። ጉዞዬንም በመቀጠል አልሰይረፊ ወደምትባለ ውና ብዙ የጨለማ ትዝታዎችን ወደምታስታውሰኝ የእግር መንገድ ደረስኩ ። በዚች መንገደ ላይ በምትገኘው ቤቱ ነው በስርቆት ተይዤ በወህኒ ቤት አራት ዓመት ያሳለፍኩት ። ፖሊሶች ቦታውን በመክበብ በደረታቸው እንደ እባብ እየተ ሳቡ ከበቡኝ ፡ ለመያዝም በቃሁ ።" በዚች ጠባብ መንገድ ወህኒ ቤት ከመግባቱ ከአንድ ዓምት በፊት ጣፋጭ ምግቦችን ለበዓሉ ለመሥራት ዱቄት ተሸክሚ ያቺ ከሃዲ ሴትም ከኔ ፊት ሆና ሰናእን በጨርቅ ታቅፋ ስትሄድ ትዝ ይለኛል ። የእነዚያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሥኖች አስደሳችነት ማንም ሰው ቢሆን እውነት ነው ብሎ ሊያምን አይችልም ። ዓመት በዓል—ፍቅር—ወላጅነትና ወንጀል በአንድ ቦታ ተደበላልቀው መገኘታቸውን ማንም አያውቅም ።

"ታላላቅ መስጊዶችና ከበስተጀርባቸው ደግሞ በከፍተኛ ቦታ ላይ ጎልቶ የሚታየው የቀልዓ መስጊድ ከሌሎቹ ጋር ተደምሮ የአካባቢው ውበትና ድምቀት በጠራ ሰማይ ላይ የሚያበሩ ከዋክብት ይመስላል ። መንገዱም ወደ አደባባዩ አመራ ። አረንጓዴው መናፈሻም በሚያቃጥል የፀሐይ ጨረር ፈካ ብሎ ታየ ። የደረቁ አየር ነፋስ የሚያቃጥል ቢሆንም አርኪነት ነበረው ።

የቃልዓ አደባባይም ከሚያቃጥሉ ትዝታዎች ጋር መታየት ጀመረ ። "አሁን ላንተ የሚያስፈልግህ ምንድን ነው? ስሜትህ ላይ ትንሽ ቅዝቃዛ ውሃ መድፋት ነው። ወዳጅና እርቅ ፈላጊ መልለህ ለመታየትና እቅድህም በአመርቂ ሁኔታ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ነው ።" የሚል ሃሳብ በሰዒድ አዕምሮ መጣ። ወዲያው አደባባዩን ሰንጥቆ ጉዞውን ቀጠለ። በመጨረሻም ሁለት ታናናሽ መንገዶች ከዋናው ጐዳና ጋር ወደሚገናኙበት ባለሶስት ፎቅ ሕንፃ ደረሰ ። እንግዲህ ጠላት ምን ዓይነት ዝግጅት አዘጋጅቶ ይሆን? ብለህ መመርመር አለብህ ። መንገዱንም በጥንቃቄ አጥና ። የተደበቀ ምን ነገር እንዳለም እወቅ ። ለምሳሌ ያህል በዚህ ያሉ ባለመደብሮች አተኩረው አድፍጠው እንደአይጥ ይመለከቱሃል ።"

"ሰዒድ ማህራን!" የሚል ድምፅ በስተጀርባው ሰማ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዴት ግሩም ነው እባክህ? እንኳን ደህና ወጣህ!" አለው። ሰዒድ ጉሠውን አቱም ሰላምታ ተለዋወጠ ። ሁለቱም ስሜታቸውን በመደበቅ የይስሙላ ፈገግታ አሳዩ። ይህ የሚያመለክተው ርኩሱ ዓሊሽ ተከታዮች አሉት ማለት ነው። ለዚህ አቀባበል መልሱ ምን እንደሆነ ታያለህ ። "እርግጠኛ ነኝ ዓሊሽ በመስኩት ቀዳዳ እንደ ሴት ተደብቀህ እንደምትመለከተኝ አልጠራጠርም" ካሰ በኋላ ሰዒድ በሃሳቡ "አመሰግናለሁ ሙዓሊም ቢያዛ" አለ ።

ሰዒድን እንኳን ደስ አለህ የሚሉ ሰዎች በብዛት መጡ፡ በሰዎችም ተከበበ። በሙሉ የጠላቱ የዓሊሽ ሰዎች እንደሆኑ ግን አይጠረጠርም ።

"እንኳን ደህና መጣህ"

"ለጓደኞችህና ለወዳጆችህ እንኳን ደስ አላቸው!"

"እኛም በአብዮት በዓል ቀን በነፃ ትለቀቃለህ ብለን ተስፋ አድርገን ነበር"

"ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው" አላቸው ። ቀላ ባለው የለውዝ ቅርፅ ባላቸው ዓይኖቹ እየተመለከተ ።

"ና ወደ ቡና ቤት ሄደን የደስ ደስ ቀዝቃዛ ለስላሳ መጠጥ እንጠጣ" አለው ቢያዛ ትከሻውን ነካ ነካ በማድረግ ።

"በኋላ ስመለስ" አለ ሰዒድ ረጋ በማለት ።

"ስመለስ?" አለ ቢያዛ በመገረም ።

"ሙዓሊም ዓሊሽ! ሙዓሊም ዓሊሽ! ና! ውረድና ሰዒድ ማሀራንን እንኳን ደስ አለህ በለው" አለ አንድ ከተቀባዮቹ ድምፁን ወደ ሁለተኛ ፎቅ አትጣጫ በማድረግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሮጭ ብሎ ።

"አንተ ጥቁር ጠንዚዛ መጠንቀቅ አያሰፈልግህም ፡እኔ የመጣሁት በቀን በብርሃን ነው ፡እንደምትጠባበቁኝ አውቃለሁ" አለ ሰዒድ በሃሳቡ ።

"ስመለስ ያልከው ከምን ነው የምትመለሰው?" አለ ቢያዛ ጥያቄውን በመቀጠል ።

"ሂሳብ አሰኝ የግድ ማጣሪት አለብኝ"

"ከማን ጋር ነው?" አለ ቢያዛ ።

"ረሳህ እንዴ እኔ እኮ አባት ነኝ፣ ትንሿ ልጄ ከዓሊሽ ጋር ነው እኮ ያለችው?" አለ ።

"አም ማንሾውም አለመጣባት ምን ጊዜም በህግ ይፈታል"

"መጣባት ነው ጥሩ " አለ አንድ ሌላ ሰው ።

"ሰዒድ አንተኮ ገና አሁን ነው ከወህኒ የወጣኸው ፡ብልህ ሰው ከስህተቱ የሚማር ነው" አለ ሶስተኛ ሌላ ሰው በሰላማዊ ሁኔታ ።

"ለጠብ ነው የመጣሁት ያለው ማነው?" አለ ሰዒድ ንዴቱን በሆዱ አምቆ በመያዝ ። የሁለተኛው ፎቅ መስኮት ተከፈተ ። ዓሊሽ ብቅ አለ ። ሰዎቹ ጭንቅላታቸውን በድንጋጤ ወደሱ አንጋጠጡ ። ባለመስመር ጀለቢያ የለበሰ ፡የፖሊስ ጫማ ያደረገ ፡አንድ ግዙፍ ሰው አንድም ቃል ሳይናገር ከቤቱ በር ወጣ ።

ሰዒድ ከመቅፅበት ነጭ ለባሽ ሐሰበላህ የሚባል ሰው መሆኑን ካወቀ በኋላ ፡"እንዲህ የሚያስፈራንታችሁ ምንድን

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ? እኔ የመጣሁት ለነገር ወይም ለጠብ አይደለም" አለ ሰዒድ ሆን ብሎ የተገረመ በመምሰል።

"ዝም በል አንተ የቀበሮ ልጅ ምን እፈልጋለሁ ነው ያልከው?" አለ ነጭ ለባሹ ወደ ሰዒድ ጠጋ ብሎ ፡ ኪሱን በዘዴና በቅልጥፍና ዳሰሰው ።

"እኔ የመጣሁት ስለ ልጄ የወደፊት ዕድል ለመነጋገር ነው ።"

"አንተ በሰላማዊ መንገድ ተግባብቶ ነገርን መጨረስ ታውቃለህ?"

"አዎ ለልጄ ስል"

"ፍርድ ቤት አለልህ"

"ወደዚያው የምሄደው ተበሳ ስቆርጥ ብቻ ነው"

"ተወው ይግባ እናንተም ግቡ" አለ ዓሊሽ ከላይ ከፎቁ ሆኖ ።

"ና አንተ ፈሪ ፡ ብጤዎችህን በዙሪያህ አሰልፋቸው ። እኔ የመጣሁት መደበቂያ ምሽግህን ለመሰልል ነው ። ጊዜው ሲደርስ ነጭ ለባሽም ፡ ብጤዎችህም ፡ ግንብም ዋጋ የለውም። " አለ ሰዒድ በሀሳቡ ።

ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ገቡ ። በሶፋዎች ላይ ተቀመጡ ። መስኮቶቹ ተከፈቱ ። ብርሃንና ዝምቦችም ገፍትረው ገቡ ። በተንጠፈፈው በሰማያዊው ምንጣፍ ላይም በሲጋራ እሳት የተቃጠሉ የሚመስሉ ጥቋቁር ነጥቦች ይታ ያሉ።

ዓሊሽ ከግድግዳ በተሰቀለው ትልቅ ፎቶ በሁለት እጆቹ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወፍራም ዱላ ይዞ ሰውን ያመለክታል። ነጭ ለባሹ ከሰዲድ ጐን ተቀመጠ። በእጁ በያዘው መቁጠሪያ ይጫወት ጀመረ። ዓሊሽ በርሜል ያሚያህለውን ሰውነቱን በሰፊ ጀለቢያ ሸፍኖ ወደ ክፍሉ ገባ። ፊቱ ክብ፣ አገጩ አራት ማዕዘን፣ አፍንጫው ግዙፍ ሆኖ ከመሀከሉ ላይ የተሰበረ ድልድይ ይመስላል።

"ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው እንኳን ለዚህ በቃህ" አለ ዓሊሽ ደፋር ዘመምሰል የሰዲድን እጅ እየጨበጠ። ወዲያውኑ ስብሰባው በዝምታ ተዋጠ። ጥረጣሬ የሰፈነባቸው የዓይን ግልምጫዎች ታዩ።

"ያለፈው አልፏል። የደረሰው ነገር በየጊዜው የሚደርስ ነው" እንዳንድ አሳዛኝ ነገሮች ሊደርሱ ይችላሉ። እንዲሁም አንዳንድ የቆዩ ወዳጅነቶች ሊፈርሱም ይችላሉ። ግን ሰውን የሚያስነውረው ነውር መሥራት ብቻ ነው።" አለ ዓሊሽ አዲስ ምዕራፍ ለመክፈት እንደፈለገ ሰው።

ሰዲድ በሚያብለጨልጩ ዓይኖቹ፣ በጠንካራና ቀጭን ሰውነቱ ንግግሩን በጥሞና ይከታተል ነበር። ሁኔታው ዝሆን ላይ ጉብ ለማለት የሚዘጋጅ ነብር ይመስል ነበር።

"ሰውን የሚያስነውረው ነውር መሥራት ብቻ ነው" የሚለውን የዓሊሽን ቃል እየደጋገመ ሲናገር በርከት ያሉ ዓይኖች በትኩረት ይመለከቱት ነበር። ነጭ ለባሹ በእጁ በያዘው የመቁጠሪያ ዶቃዎች መጫወቱን አቆመ።

"አውን በተናገርከው በሙሉ አንድ በአንድ እስማማበታለሁ" አለ ሰዲድ በሰዎች አዕምሮ የሚመላለሰውን ሃሳብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ካጤነ በኋላ ።

“እባካችሁ ከዋናው ጉዳያችሁ ግቡ ፡ ጥምጥም ሁሪያ እየሠራችሁ አታሰልቹን” አለ ነጭ ለባሹ ።

“ከጉዳዩ ግቡ ስትል በምን በኩል ነው?” አለ ሰዒድ በማፈዝዝ መልክ ።

“በአንድ በኩል ብቻ ነው ለመናገር የሚቻለው ይኸ ውም በልጅህ ጉዳይ ነው!”

“እናንተ ውሾች ባለቤቱስ? ገንዘቤስ? ፡ ወሮውልሽ! አንድ ጊዜ እንዳይሸ አፈልጋለሁ ፡ ሥራሽ ሁሉ እንደ ጠንዚዛ፡ እንደጊንጥና እንደ ተባይም በመሆኑ ሞት ላንቺና አንቺን በመሳሰሉ ሴቶች ድምፅ ለሚደሰት ሁሉ” በሃሳቡ ካለ በኋላ ስለ ልጁ ጉዳይ የሚነገረውን ለመስማት በመጓጓት ጭንቅላቱን ነቀነቀ ።

“ልጅህ ከእናቷ ጋር በጥሩ ሁኔታ ነው የተያዘችው ። በሕጉም መሰረት የስድስት ዓመት ልጅ ከእናቷ ጋር መሆን ነው ያለባት ። ካስፈለገም በየሳምንቱ እንድትጎበኛት ይደረ ጋል” አለ አንድ አመደዳለሁ ባይ ።

“በሕጉ መሰረት የእኔ ናት ። ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶችና ሁኔታዎች ...” አለ ሰዒድ ሆን ብሎ ድምፁን ወደ ሌላው ክፍል እንዲሰማ በማድረግ ።

“ምን ማለትህ ነው?” አለ ዓሊሽ በቁጣ ።

“ብዙ ንግግር ከራስ ምታት ሌላ ምንም ጥቅም የለ ውም” አለ ነጭ ለባሹ ፊጠን በማለት ።

“እኔ ምንም ወንጀል አልሠራሁም ፡ ነገር ግን የፅድል

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳይ ነው ፡ ግዴታም ነው ። የርሀራሄ ግዴታዉ ነው ይህን ለማድረግ ያስገደደኝ ለትንሿ ልጅም ሞምር ነው!" አለ ዓሊሽ በእርግጠኝነት አነጋገር ።

"የርሀራሄ ግዴታ ነው አልከው አንተ የእባብ ልጅ? ለከሀዲና ጉዳር አፍራሽ ለሆነ ሁሉ የሚገባው መዶሻ ፡ መጥረቢያና የስቅላት ገመድ ነው።" በሆዱ ካለ በኋላ "ለመሆኑ ሰናእ ምን ትመስላለች አውን?" አለ በተቻለ መጠን ስውነቱን እየተቆጣጠረ ። "እኔ እኮ እንዲሁ አልተው ኳትም ። ብዙ ገንዘብ ነው የተውኩላት" ሲል ሰዒድ ተናገረ።

"በስርቆት ያገኘኸው ገንዘብ ነው ያ በፍርድ ቤት የካድከው?" አለ ነጭ ለባሹ ፍሽሽ ብሎ ።

"ይሁን እንደፈለግህ በለው ፡ ነገር ግን የት ደረሰ?"

ዓሊሽ ፍሽሽ በማለት "እሞኙኝ አንድ ሳንቲም አልተወም። የነበረው ሁኔታ ጠላትም ሆነ ወዳጅ የማያስደስት ነው። በእርግጥ ግዴታዬን ተወጥቻለሁ" አለ ዓሊሽ ፍሽሽ ብሎ በማስተባበል ።

"እስኪ ንገረኝ እንዴት በድሎት ለመኖርና ሌሎችንም ለመርዳት ቻልክ?" አለ ሰዒድ በቁጣ ።

"አንተ ፈጣሪ ነህ እንዴ የምትቆጣጠረኝ?" አለ ዓሊሽ ፊቱን ኮስተር በማድረግ ።

"ሰዒድ ሰይጣንን አሳጥረው" አለ አንዱ ከዓሊሽ ወዳጆች ።

"እኔ አበጥሬ አውቀዋለሁ ። በአዕምሮህ ውስጥም ምን ዓይነት ሃሳብ እንደሚጉላላ በደንብ ነው የማውቀው ። አንተ

t.me/OLDBOOKSPDF

ራስህን ለማጥፋት ነው የምትፈልገው ። የሚሻልህ ግን ከልጅቷ ጉዳይ ባትወጣ ነው ።”

“እኔ በደንብ ነው የማውቅህ ፡ ግን ለእነዚህ ሰዎች ክብር ስል አልቃወምህም ። ልጅቷን አምጡ ፡ ሃሳቧን በመጀመሪያ ብናውቅ የሚሻል አይመስላችሁም?” አለ ነጭ ለባሹ ።

“ምን ማለትህ ነው ነጭ ለባሽ?” አለ ሰዒድ በቁጣ ሞልክ ።

“ሰዒድ እኔ ይህና አድርጌ ነው የማውቅህ ፡ አንተ ልጅቷን አትፈልግም ። መጠለያም ልታገኝላት አትችልም ። አንተም ራስህ ብትሆን መጠለያ ለማግኘት ብዙ ጥረት ያስፈልግሃል ። ግን ለርህራሄና ለፍትህ ሲባል እንድታያት ይደረጋል ። ልጅቷን አምጧት” አለ ነጭ ለባሹ ።

“ምነው እናቷንም ብታመጪት የሁለቱ ሰዎች ዓይኖች እንዲገናኙ የገሀነምን የሚስጥር ሚስጥር ለማየት እንዲቻል ለሷ መጥረቢያና መዶሻ ያሻታል—” አለ ሰዒድ በሆዱ ።

ዓሊሸ ልጅቷን ለማምጣት ቆም አለ ። የእግር ኮሽታ ሲሰማ የሰዒድ ልብ ትርታ ክፉኛ መምታት ጀመረ ። ወደ መዝጊያው በጉጉት እየተመለከተ የውስጥ ከንፈሩን ነከሰ ። በከባድ የፍቅርና የናፍቆት ስሜት ውስጥ ወድቆ ሳለ ልጅቷን ዓሊሽ ታቅፎ ድንጋጤ በተሞላባቸው ዓይኖቿ ብቅ አለች። ልክ አንድ ሺህ ዓመት ስትጠበቅ የቆየች ያህል የሰዒድን ልብ ሰቅላ ። ግራም የሆነ ነጭ ቀሚስና በሂና ያጌጡትን የእግር ጣቶቿን በሚያሳይ ነጭ ሰንደል ጫማ አሸብርቃለች ። ፊቷ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠይም ፡ ወጉሯ ጥቁር ወደ ግንባሯ የወረደ ፡ ዓይኖቿ የለውዝ ቅርፅ ያላቸው ይቺው ውብ ልጅ በመገረም አመለካከት ዓይኖቿን በዚያ በነበሩት ላይ ሁሉ እያመላለሰች ግራ ቀኙን ማየት ጀመረች ። በተለይ ሰዒድ በጣም አተኩሮ ስለሚመለከታትና ሰዎችም ወደ እሱ ስለሚገፉት ሳይሆን አይቀርም በድንገት እግሮቿ በምንጣፉ ላይ እንዳለች ቀጥ ብለው ቀሩ ። ስውነቷን በሙሉ ወደ ኋላ ዘምበል አደረገች ። ዓይኖቹን ከእሷ ላይ ቢያሳርፍም ልቡ ግን ተሰበረ ። ምንም አልቀረውም የመጥፋት ስሜት አደረበት ። ልጁ ለመሆኗ የሚያባብሉት የለውዝ ቅርፅ ያላቸው ዓይኖቿና ረጂም ፊቷ ፡ ሰበር ያለ ረጂም አፍንጫዋ ከሱ ጋር ተመሳሳይ ከመሆናቸውም በላይ የደምና የመንፈስ ጥሪስ ቢሆን ቀላል ነው እኒዴ? እሱም ሊከዳ ይችላል ወይ? ይህ ሁሉ ማስረጃ እያለ እንዴት ወደ እሱ ቀረብ ኣድርጐ በደረቱ እስከ ዓለም መጨረሻ ሊታቀፋት አልቻለም?

"አባትሽ ነው እኮ አንቺ ሙሉ ልጅ" አለ ነጭ ለባሹ ቆጣ በማለትና ደንታ በሌለው አንደበት ።

"ባባን ጨብጪ" አለ ዓሊሽ የደስታም ይሁን የክፋት ምልክት በማይነበብበት ፊቱ ።

"እንደ አይጥ! ማንን ነው የምትፈራው ? አታውቅም ወይ ምን ያህል እንደምወዳት!" እጁን ዘረጋላት ለመናገር ግን አልቻለም ፡ ጉሮሮው ስለደረቀ ፈገግ በማለት ለማባበል ሞከረ ። ሰናእ አለ "እምብዮው" አለች ፡ ወደ ኋላዋ አፈገፈገች ፡ ከኋላዋ የቆመ ሰው ስላለ ለመሄድ አልቻለችም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጮኽ ብላ "ማ!ማ!" አለች ። ከኋላዋ የቆመውም ሰውዬ በማባበል "አባትሽን ጨብጪ" አላት ። ልጅቷም መቃወሟንና ለቅሶዋን አባባሰችው ።

"ረጋ በል እንጂ ፡ ልጅቷ እኮ አታውቅህም " አለ ነጭ ለባሹ ።

"እወስዳት ይሆናል" አለ ሰዒድ ተስፋ በመቁረጥ ከለቀቃት በኋላ መቀመጫውን በማስተካከል በቁጣ መልክ ። ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ።

"መጀመሪያ አንተ መንፈስህን ረጋ አድርግ" አለ ቢያዛ ።

"ወደ እኔ መመለስ አለባት" አለ ሰዒድ ።

"ውሳኔውን ለዳኞች ተወው" አለው ነጭ ለባሹ በቁጣ አነጋገር ። ወደ ዓሊሽ ዞር ብሎ እየተመለከተ ።

"ትክክል ነው እኔ በጉዳዩ የሚያገባኝ ነገር የለም ፡ እናቷ ግን በሕግ ካልሆነ በቀላሉ አትለቃትም" አለ ዓሊሽ ።

በሰዎች ዓይኖች ላይ የመገረምና የማሽሟጠጥ ሁኔታ ይታይ ነበር ። ሰዒድ ወህኒ ቤቱ ይህን ያህል ጉዳት ያደረሰበት አልመሰለውም ነበር ። አሁን ግን ተረዳ ። "ነይ ሰ—ሰኑዬ" አለ በማቆላመጥ ። የእሷን እምቢታ በፀጋ ሊቀበለው አልቻለም ። ብድግ በማለት ወደ እሷ በማዘንበል ለመያዝ ሞከረ ። ጩኸቷን ለቀቀችው ።

"እምብዬው" ... አለች ።

"እኔ ባባ ነኝ" አለ ።

ዓይኖቿን ወደ ዓሊሽ በማዞር በመገረም አየችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዒድ በመደጋገም "እኔ ባባ ነኝ ፡ እኔ ነኝ ባባሽ ነይ ወደ እኔ ።" ይበልጡኑ ወደ ዓለሽ አፈገፈገች ። ወደ እሱ በ:ንይል ሳብ አደረጋት ፡ ጮኸች ፡ ወደ ደረቱ ታቀፋት ፡ እያለቀሰች ገፈተረችው ። አፍዋና ጉንጮቿን ለመሳም አልቻለም ። በንዴት ያለ ርህራሄ እጆቿን እያመናጨቀች ሳለች እንደም ንም ብሎ እጇን ለመሳም ቻለ ። "እኔ ባባ ነኝ አትጥሪ፡ እኔ ባባ ነኝ" አለ ። የወጉሯ ጠረን ከእናቷ ጋር ተመሳሳይነት ስለነበረው መንፈሱን አሸበረው ፡ የናቷንም ከሀዲት አስታወ ሰውና የሰውነቱ ህዋሳቶች ቀጥ ያሉ መሰለው ።

"በመጀመሪያ ጊዜ እንደተናገርኩት ሁለተኛ የማያዳ ግም አንድ ቃል ብቻ ነው እሱም ፍርድ ቤት ነው" አለ ነጭ ለባሹ ።

ሰዒድ ብዙ የረሳቸው ጉዳዮች ትዝ አሉትና በቁጣው ከቀጠለ ከሌላ የዕብደት ደረጃ ሊደርስ ስለሚችል ስሜቱን ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል መቆጣጠር ጀመረ ። "በፍርድ ቤት እሺ" አለ አንጸራዊ በሆነ እርጋታ ።

"እንደምታየው ልጅቷ በእንክብካቤና በምኞት ነው ያለችው" አለ ቢያዛ ።

"አንተ በመጀመሪያ ለእንጀራህ ፡ ለመተዳደሪያህ የሚሆን ትክክለኛ መንገድ ፈልግ" አለ ነጭ ለባሹ በማሾፍ ።

"እሺ ይህ አሁን ያላችሁት ሁሉ ሀቅ ነው እኔ በበኩሌ የማዝንበት አይደለም ። ጉዳዩን እንደገና አጤነዋለሁ ፡ ለእኔም የሚሻለኝ ያለፈውን መርሳት ፡ሥራም መፈለግ ለልጅቷ ጥሩ ቦታ በተገቢው ጊዜ ማዘጋጀት ነው ።" አለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዒድ ራሱን በበለጠ በመቆጣጠር ።

በድንገት ዝምታ ሰፈነ ። ሰዎችም በመተያየት ትክክል ነው? አይደለም? በማለት እርስ በርሳቸው ተያዩ ።

“ጨርሰናል?” አለ ነጭ ለባሹ የእጅ መቁጠሪያውን በእጁ እየጠቀለለ ።

“እሺ ነገር ግን መዕሐፎቹን እፈልጋለሁኝ” አለ ሰዒድ።

“መፃሕፍቹን?! አሰ ዓሊሽ ።

“አዎ!” አለ ሰዒድ ።

“አብዛኛዎቹ በሰናእ እጅ ወድመዋል ፡ የቀሩትን አመጣልሃለሁ” አለ ዓሊሽ በቁጣ መልክ ።

ዓሊሽ ትንሽ ቆየት ብሎ በርከት ያሉ መዕሐፎችን ታቅፎ መጣ ። በክፍሉ መካከል አስቀመጠው ።

ሰዒድም መፃሕፍቹን አንድ በአንድ እየተመለከተ ፡ “እርግጥ ነው አብዛኞቹ ጠፍተዋል” አለ በሀዘን መልክ ።

“ይህን ሁሉ ዕውቀት ከየት ነው ያግኘሽው?” አለ ነጭ ለባሹ በማሽሟጠጥ ። አያይዞም ከምትሰርቃቸው ነገሮች መዕሐፎችም ትሰርቅ ነበር ማለት ነው?” ሲል ጠየቀው ። ንግግሩን በመቀጠል ፡ ውይይቱ ማለቁን እያበሰረ ። ሁሉም ፊገግ አሉ ። ሰዒድ ግን ኮስተር ብሎ መዕሐፎችን መሸከም ጀመረ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

—2—

ሰዒድ በጀበል መንገድ አድርጎ ምንጊዜም በሩ ክፍት ወደሆነው ቤት ለመሄድ አሰበ ። በሙቀጠም ኮረብታ ስር ብዙ አስደሳች ትዝታዎች የያዘው የደራሳ ቀበሌ ይገኛል ። አሸዋማው መሬትም በአጋሰስ ተጨናንቋል ። ህፃናትም ይፈነድቃሉ ። ሰዒድም በደከምና በውስጣዊ ንዴት ምክን ያት ቁና ቁና እየተነፈሰ ዓይኖቹ አለማሰለስ በፈገግታ መልክ ቤት ህፃናትን ይመለከታሉ ። በርከት ያሉ ሰዎች ግን ከጠራራ ፀሐይ ለመራቅ ሲሉ በኮረብታው ግርጌ ተጠልለዋል ።

ምን ጊዜም በሩ ክፍት ወደሆነው ቤት መግቢያ ሲደርስ ቆም ብሎ "ለመሆኑ መቼ ነበር ለመጨረሻ ጊዜ ይህን መግቢያ የተሻገርኩት?" ሲል ራሱን ጠያቀ ። ቤቱ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ከእነዚያ በአዳምና ሔዋን ጊዜ ከነበሩ ቤቶች በምንም ዓይነት አይለይም ። የሚያስገርም ቤት ነበር ። በስተግራ በኩል በዚህ ትልቅ ሰፊ ግቢ ከጭንቅላቱ ጐበጥ ያለ አንድ የዘንባባ ዛፍ ይገኛል ። በጣም የሚገርመው በዚህ ቤት አንድም የሚዘጋ በር የለም ። የልቡ ትርታ በፍጥነት መታ ። ሩቅ ወደሆነው አስደሳች የልጅነት ዘመን ሕልም ፡ የአባት ፍቅርና መንፈሳዊ ወደሆኑ ትዝታዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

ወሰደው ። አዕምሮውን ወደኋላ መለስ በማድረግ በግዚው ውስጥ የነበሩት ሰዎች እየተወዛወዙ ያደርጓቸው የነበሩትን መንፈሳዊ ዐሎቶች ባይነ ሕሊናው አስተዋለ ። ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትም ዐሎትና ሙገሳ የለበጣ ሳይሆን ጥልቅ ከሆነ ስሜትና ከንፁሕ ልቦናቸው የሚመነጭ ነበር ። "እይ! ስማ! ተማር! ልብህንም ክፈት" አባቱ አዘውትረው እንዲህ ይሉት ነበር ። ለሱም ከፍተኛ ደስታ ይሰማው ነበር ። እንዲሁም ሌላ ደስታ የሚሰጠው መዝሙሮችን መዘመርና ሻይ መጠጣት ነበር ።

ከዚህ ላይ ሼክ አሊ በሃሳቡ መጡበት በመገረም "ምን ይመስሉ ነበር?" አለ ። በክፍሉ ውስጥ አንድ የሚሰግድ ሰው ስግደት መጨረሱን አወቀ ። በዚሁ ጊዜ ሰዒድ ፈገግ በማለት መጽሐፎቹን ተሸክሞ ወደ ክፍሉ ሹልክ ብሎ ገባ ። ሼኩም እግራቸውን አጣጥፈው ከመስገጃው ምንጣፍ ተቀምጠው በፀሎት ተውጠው አገኘ ። የድሮዋ ክፍል ምንም ዓይነት ለውጥ አይታይባትም ። የለሌን ምንጣፎች በአዳዲስ ምንጣፎች ተተክተዋል ። የሼኩም መተኛ ፍራሽ በምዕራብ በኩል በሚገኘው ግድግዳ እጠገብ እንደተቀመጠ ነው ። ከመስኮት በኩል የፀሐይ ጮራ ከሰዒድ እግሮች ላይ አረፈ ። ሌሎች የክፍሉ ግድግዳዎች ግማሹን ያህል በመፅሐፍ መደርደሪያ ዎች ተሸፍነዋል ። የዕጣኑ ሽታ ክፍሉን ልክ ድሮ እንደሚያስታውሰው ለብዙ ዓመታት ሳይለወጥ የተቀመጠ አስመስሎታል ። መፅሐፎቹን በማስቀመጥ ወደ ሼክ ተጠጋ ።

"ሰላም ለእናንተ ይሁን አለቃዬና ጌታዬ"

t.me/OLDBOOKSPDF

ሼኩም ዐሎታቸውን ፈጽሰው ሟንቅላታቸውን አቀኑ። ፊታቸው ከሲታ ቢሆንም ሕያው ነበር ። ጢማቸው ነጭ እንደ ፈሊታ የሚያበራ ፡ በሟንቅላታቸው ብራማ መልክ ያለው ክር የተሸለመች ነጭ ኮፍያ ለብሰዋል ። ሼኩ ለሰማንያ ዓመታት ያህል ይሆን ዓለም ባዩበትና የወዲያኛው ንም ዓለም በፈሊፍታ በተመለከቱበት ዓየኖቻቸው ተመለከቱት። ዓይኖቻቸውም ግርማቸውን ፡ አርቆ አስተዋይነታቸውና ማራኪነታቸውን አላጡም ። ሰዒድ እጃቸውን ለመሳም ጐንበስ ሲል ከውስጣዊ አንጀቱ የመጡ እንባዎች ለአባቱ የልጅነቱ ተስፋዎችና የድሮው ንፁህ ሰሞነው ትዝታዎቹ እርግፍ እርግፍ አሉ ።

ሼኩ ለሰላምታው መልስ በመስጠት የድሮው ድምፃቸው በሚመስል "ሰላምና የአላህ ርህራሄ በአንተላይ ይሁን" አሉ ።

ለመሆኑ የአባቱ ድምፅ ምን ይመስል ነበር? የአባቱ ፊት ታየው ። ከንፈሮቹም ሲንቀሳቀሱ አየ ። ዓይኖቹ የጆሮቹን አገልግሎት ሥራ እንዲሠሩ ሞከረ ። ነገር ግን ድምፅ ጠፋ ። እነዚያ የሼኩ ተከታዮች የመንፈሳዊ "ዚክር" እየተወዛወዙ "ጌታዬ መልዕክተኛው ሙሐመድ ከበርህ ላይ ቆሟል!" እያሉ በጣዕመ ዜማ ሲዘምሩ የነበሩት በአሁኑ ጊዜ የት ይሆኑ?" አለ ። ሰዒድ እግሮቹን እጥፍጥፍ አድርጎ ከሼኩ ፊት ለፊት ከምንጣፉ ላይ ተቀመጠ ።

"የርስዎን ፈቃድ ሳልጠይቅ ተቀምጫለሁ" አለ ። "እኔ እንደማስታውሰው እረስዎ እንደማይታወሙ ይገበ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኛል ።" ሼኩ ፈገግ የሚሉ መስሎ ተሰማው ። ሆኖም ከንፈሮቻቸው ተገጣጥመዋል ። ምንም ዓይነት ፈገግታ አይታይም ። ለመሆኑ ሼኩ ያስታወሱት ይሆን?

"ይቅርታ አድርጉልኝ በዚህ ሁኔታ ወደ ቤትዎ በመመጣቴ በዚህ ዓለም ከቤትዎ በስተቀር ሌላ ቤት ስለሌለኝ ነው" በማለት ሰዒድ ተናገረ ።

ሼኩ አንገታቸውን ወደ ደረታቸው ደፉ ። "አንተ የምትፈልገው መጠለያ ነው ልብ አይደለም" አሉ በዝቅተኛ ድምፅ ።

"ዛሬ ቀን ነው ከወህኒ ቤት የወጣሁት" አለ ሰዒድ በረጅሙ በመተንፈስ ምንም እንዳልገባው በመምሰል ።

"ወህኒ ቤት!" ሲሉ ለጆሮ በጮላ የድንጋጤ ዓየነት ድምፅ ጠየቁት ሼኩ ዓይኖቻውን በመፈፈን ።

"እውነት ነው እርስዎ ለአሥር ዓመት ያህል አላዩኝም። በዚህ ጊዜ ውስጥ ብዙ አስገራሚ ነገሮች ተፈጽመዋል። ከእርስዎ አንዳንድ ተከታዮችም እኔን ከሚያውቁኝ ሳትሰሙት አትቀሩም "

"ብዙ ነገር እሰማለሁ። ግን ምንም እንደማልሰማ ነው" አሉ ሼኩ ።

"ያም ሆነ ይህ እኔ ሌላ ሰው መስዬ በተጭበረበረ ሁኔታ ከእርስዎ ፊት ለመቅረብ አልፈለኩም ። ስለዚህ ነው ዛሬ ቀን ከእስር ቤት ወጣሁ ብዬ የምገልፅልዎት"

"አንተ ከእስር ቤት ገና አልወጣህም" አሉ ጭንቅላታቸውን በቀስታ እያወዛወዙ ዓይኖቻቸውን ከፊት እያደረጉ

t.me/OLDBOOKSPDF

በሐዘን መልክ ።

ሰዒድ ፈገግ በማለት "ይህ አንጋፊር የድሮ ጊዜ አንጋፊር ነው ፡ ሁለት ትርጉም ያለው።" አለ በዐሳቡ ።

"ጊታዩ ከመንግሥት ወህኒ ቤት በስተቀር ማንኛውም ወህኒ ቤት ይቻላል" አለ ሰዒድ ።

"ከመንግሥት ወህኒ ቤት በስተቀር ማንኛውም ወህኒ ቤት ይቻላል" አሉ ሼኩ ድምፃቸውን በመቀነስ ሰዒድ የተናገረውን በመድገም ።

"ጊታዩ ያስታውሰኛል" አለ ሰዒድ እንደገና ፈገግ በማለት ከሼኩ ጋር ስመግባባት ተስፋ ከቆረጠ በኋላ ።

"ስለ አሁኑ ሰዓት ብቻ ተናገር"

ሰዒድ ሼኩ እንዳወቁት አይጠራጠርም ። ስለዚህ በይበልጥ በራሱ በመተማመን እንዲህ ሲል ጠየቀ ።"አባቱን ነፍሱን ይማር ዓም ማህራንስ ያውቁታል?"

"ምህረት ለሁላችንም" አሉ ።

"የድሮ ጊዜ እንዴት አስደሳች ጊዜ ነበር!" አለ ሰዒድ።

"ለአሁኑም ጊዜ እንዲሁ ማለት ትችላለህ" አሉ ሼኩ ።

"ነገር ግን ..."ብሎ ሰዒድ ንግግሩን ሳይጨርስ

"አላህ ለሁላችንም ምህረቱን ያውርድልን" አሉ ሼኩ የሰዒድን ንግግር በማቋረጥ ።

እኔ እኮ የምለው ዛሬ ነው ከወህኒ ቤት የወጣሁት"

"የአላህ ፈቃድ ስለሆነ ነው በዚህ ሁኔታ ላግኝህ የቻልኩት" አሉ ። ጭንቅላታቸውን በአዲስ ጉልበት በማንሳት ለመጥፎ ነገር ፈገግ እንደሚሉ በመምሰል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደማትተባበሩኝ ሆኖ ተሰማኝ ። ሆኖም በገሃ ፈተዬ ወደዚሁ የዕጣን ሽታ ወዳለውና ወጥታ ወዳልሰፈነበት ቦታ ለመምጣት ተገደድኩ ። ምክንያቱም ብቸኝነት የሚያጠቃው መጠለያ የሌለው ከዚህ የተሻለ ሌላ ነገር ማድረግ አይችልም" ካለ በኋላ በሃሳቡ ለሸኩ እንዲህ አለ ። "ጌታዬ እኔ አውን የመጣሁት የራሴ ልጅ አባቱ አይደለህም ካለችኝ በኋላ ነው ።

"አላህ ሚስጢሩን ስትናንሽ ፍጥሮቹ ይገልጽላቸዋል" አሉ ሸኩ በችግር እየተነፈሱ ።

"እኔ ለራሴ እንዲህ አልኩኝ" አላህ ዕድሚያቸውን ከቀጠለላቸው የቤታቸው በር ክፍት ሆኖ አገኘሁለሁ አልኩ" አለ ሰዒድ ስለ መጣበት ሲገልጽ ።

"የሰማይን በርስ እንዴት አገኘህው?" አሉ ሸኩ በእርጋታ ።

"እኔ በዚህኛው ዓለም መጠለያ ቤት የለኝም ። ልጂም ካደችኝ ። ስለሆነም ስለሰማይ በር ማሰብ አልችልም"

"አንተና እሷ እንዴት ትመሳሰላላችሁ!"

"በምን በኩል ጌታዬ?"

"አንተ የፈለግህው መጠለያ ብቻ ነው መልስ አይደለም"

"አባቱ ችግር ሲገጥመው ወደ እርስም ይመጣ ነበር ። እኔም ስለዚሁ ነው የመጣሁት" አለ ሰዒድ ሞንቅላቱን በእጁ አስደግፎ ።

"አንተ የምትፈልገው መጠለያ ነው ሌላ ነገር አይደለም"

t.me/OLDBOOKSPDF

“መጠለያ ብቻ አይደለም ከዚሁ የበለጠ ነው የምፈልገው ። አላህን ልጠይቀው የምፈልገው በእኔ እንዲደሰት ነው” አለ ። ሼኩ እንዳወቁት በመተማመን በመልሳቸውም እንዳልተደሰቱ በመግለፅ ።

“አያሳፍርህም ወይ አላህ እንዲደሰትብህ የምትፈልገው አንተ ራስህ በእሱ ያልተደሰትክ?” አሉ በመገረም የአንዲት መንፈሳዊ ሴትን ጥቅሶች በማንበብ ።

በዚህ ጊዜ ከቤቱ ወጣ ብሎ በሚገኘው ክፍት ቦታ አህያ ሲጮህ ተሰማ ። ወደ መጨረሻው በሰለለና እንደማልቀስ በሚመስል ድምፅ የአህያው ጩኸት አበቃ ። እንዲሁም በሌላ ቦታ ደግሞ በጣም አስቀያሚ በሆነ ድምፅ አንድ ሰው “ዕድሌና ሀብቴ የት ደረሱ?” እያለ ይዘፍን ነበር ። ይህ ድምፅ ለሰዲድ አንድ ትዝታ አመጣበት ። አባቱ ከዕለታት አንድ ቀን “እንቆቅልህ ምን ያውቅልህ” እያለ ሲጫወት “ምነው ልጄ ወደ መንፈሳዊ ሼኩ ቤት እየሄድን እንደዚህ ያለ ጨዋታ መጫወት ጥሩ ነው ወይ?” ብለው ያበረከቱለትን ምክር ያስታውሳል ። ሌላ ትዝ ከሚሉት ነገሮች መካከል አንድ ጊዜ አባቱ በዐሎት ላይ እንዳሉ ልዩ የሆነ ድምፅ ማሰማታቸው ፣ ዓይኖቻቸውም እንደመጥፋት ብለው ድምፃቸውም ማጉርን ጉና ላብም በግንባራቸው ሲንጠፈጠፍ መመልከቱ ዛሬም ትዝ ይለዋል ። ይህ ሁሉ ትዝታ ዛሬ ከሀዲት የፈፀመችበትን የልጇን እናት ከመተዋወቁና በፍቅሯ ከመያዙ በፊት ነበር ።

የሼኩ ዓይኖች ተጨፍነው እንቅልፍ ሸለብ ያደረጋቸው ይመስላል ። ሰዒድም ቦታውንና አካባቢውን ስለተለማ

t.me/OLDBOOKSPDF

መጄው ይመስላል የዕጣኑ ሽታ ምንም ዓይነት ስሜት አላሳደረበትም ። ከዚህ ላይ አንድ ሃሳብ መጣበት ። እሱም አንድ ነገር መልመድና አቅልሎ መመልከት ወይም አለመጠራጠር ከስንፍና ተለይቶ የማይታይ እንዲያውም ላልታሰበ ነገር አሳልፎ የሚሰጥ ደንታ ቢስነት መሆኑን ተረዳ ። ይህም እሱ ራሱ በሰዎች ላይም ያሳደረው ከንቱ ዕምነት ነበር ለደረሰበት ስቃይና ከሀዲት እንዲሁም ዕድሜ ልኩን ላጠራቀመው ሀብት በዋዛ መጥፋት ምክንያት የሆነው ።

"አሁንም እንደ ድሮው "ዚክር" ታደርጋላችሁ ወይ?" አለ ሰዒድ ሼኩን ከእንቅልፋቸው ለመቀስቀስ እንደፈለገ ሰው ። ሼኩም መልሰ ባለመስጠታቸው ተጠራጠረና እንደገና እንዲህ ሲል ጠየቀ ።" እኔን ከዚህ ቤትም አያሰተናግዱኝም እንዴ?"

ሼኩም "በእኔና በአንተ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም እኩል ነን" አሉ ዓይናቸውን ከፈት በማድረግ ።

"እርስዎ እኮ የቤቱ ጌታ ነዎት!"

"የቤቱ ጌታ ከሆንኩኝ በደስታ አስተናግድሃለሁ ለማንኛውም ፍጡር እንደሚደረግ ሁሉ አሉ" ሼኩ በደስታ መልክ። ሰዒድ ፈገግ አለ ። ሼኩ ግን ንግግራቸውን በመቀጠል ፡ "እኔ ግን ምንም ነገር የለኝም" አሉ ።

ከሰሌኖቹ ላይ አርፎ የነበረው የፀሐይ ጮራ ወደ ግድግዳዎች አፈገፈገ ።

ይኸ ቤት የአባቱ ቤት ስለነበረ የኔም ቤት ነው ፡ የማንኛውም ሰው ቤት ስለሆነ እርስዎም ጌታዬ ምስጋና

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚገባዎት ነዎት” አለ ሰዒድ ።

“አላህ ሆይ አንተን ለማመስገን ስለሚያቅተኝ አንተም እንደምታውቀው በእኔ ስም ራስህን አመስግን ፡ አንዳንዱ አመስጋኞች እንዳሉት ሁሉ” አሉ ሼኩ ።

“እኔ በጎ ቃል ለመስማት ነው የምፈልገው” አለ ሰዒድ በትህትና ።

“አትዋሽ” አሉ ሼኩ በወቅሳ መልክ ።

ሼኩ ጭንቅላታቸውን ገንበስ ሲያደርጉ ጢማቸው በደረታቸው ላይ አረፈ ። በዝምታ ተዋጡ ። ሰዒድ በትዕግሥት ጠበቃቸው ። ወደ ኋላ ተለጥጦ ጀርባውን ወደ መጽሐፎቹ መደርደሪያ በማስጠጋት የሼኩን አስደሳች ትርዒት አተኩሮ መመልከት ጀመረ ። “የምረዳዎት ነገር አለ?” ብሎ ጠየቃቸው ።

ምንም ዓይነት መልስ አላገኘም ። አሁንም በትዕግሥት ጠበቃቸው ። በዚህ መሀል ጉንዳን በፍጥነት ወደ ተጣጠፉት ሰሌኖች ሲዘምት ተመለከተ ።

ሼኩ በድንገት “ ፡ አሁኑኑ (ወዱእ) አድርግ ፡ ታጠብና ቁርዓንን አንብብ”

ሰዒድ ግን ሼኩ የሚናገሩትን ሳይሆን የነበረበትንና ያጋጠመውን አሳዛኝ ሁኔታ ነበር በአዕምሮው እያመላለሰ የሚያዳምጠውና የሚናገረው ። ሁለት የተለያዩ የሁለት ዓለም ሰዎች!

“እኔ እኮ ዛሬ ቀን ነው ከእሥር ቤት የወጣሁት ስለዚህ አልታጠብኩም” አለ ሰዒድ ።

“ታጠብና የቁርዓን መጽሐፍ ይዘህ አንብብ”

t.me/OLDBOOKSPDF

“ልጄ አባትነቴን ካደች ። እንደ ሰይጣን ከእኔ በራ ሄደች ከዚህ በፊት እናቷ ካደችኝ!” አለ ሰዒድ ግራ እንደተጋባ ሰው ።

“ታጠብና አንብብ” አሉ ደግመው ።

“ባለቤቱ እኮ አንድ እርኩስ ፡ የእኔ አገልጋይ ፡ የእኔ ተማሪ ፡ ከእግሬ ሥር ወድቆ እንደ ውሻ ይተሻሸ የነበረ ፡ መታሠሬን ምክንያት በማድረግ ፍቺ ጠይቃ ይህንን እርኩስ አገባች” አለ ።

“ታጠብና አንብብ ነው የምልህ!”

“ግንዘቤን ፡ ንብረቴንና ቤቱ ውስጥ የነበሩ ውድና ክቡር ዕቃዎች በሙሉ ዘርፎ አሁን የናጠጠ ከበርቴ ሆኗል ። የሠፈሩ እርኩሶች በሙሉ የሱ ተከታዮች ሆነዋል”

“ታጠብና አንበብ!” አሉ በቁጣ ።

“በፖሊስ ጥረት አይደለም የተያዝኩት ፡ ፈዕሞ እንደ አመሌ ለማምለጥ እችል ነበር ። ውሻው ከውሻዋ ጋር በመመሳጠር ስለ ጠቆመብኝ ነው ። እንዲህ እንዲህ እያለ ሰቆቃዬ ተከታተለብኝ በመጨረሻም ልጄ ከዳችኝ”

“ታጠብና አንብብ” ከተጻፈውም የሚከተለውን የቁር ዓንን ጥቅስ አስታወሰ ። “በላቸው ፡ አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ ፡ አላህ ይወዳችኋልና” በማለት እንዲሁም “እኔ ለራሴ መርጨሀ አለሁ” የሚለውን ከጠቀሱለት በኋላ አያይዘው “ፍቅር ማለት እሱ አላህ ያዘዘውን መከተል ፡ የጠላውን የመጥላት ፡ ፍርዱንና ውሳኔውን በጥሞና መቀበል” የሚለውን አነጋገርም ሁል ጊዜ ማሰብና

t.me/OLDBOOKSPDF

ማሰላሰል አለብህ” አሉት ።

ሰዒድ መልስ አልሰጣቸውም ። ነገር ግን ጥቅሱን በአዕምሮው ያመላልስ ጀመር ። ይታየኛል አባቱ ይሀን ቃል ሲሰሙ ሞንትላታቸውን በማወዛወዝ ደስታቸውን ይገልጻሉ። እኔንም በፈግግታ እየተመለከቱ ስማ ፡ ተማር የሚሉኝ ይመስለኛል ። ማንም ሰው ሳያየኝ ከዘምባባው ዛፍ ወጥቼ ወይም ድንጋይ በመወርወር የተምርን ፍሬ ለማውረድ ያደረግሁት ጥረት ሁሉ ይታየኛል ። ትዝ ይለኛል ። ከሼኩ ተከታዮች ጋርም ጣዕመ ዜማ እያሰማን ስንኖር አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ በጂዛ ከሚገኘው የተማሪዎች ሆስቴል ስመለስ ዘምቢል ተሸክማ ወደ እኔ ስትመጣ አየኋት ። በጣም ቆንጆ ማራኪ. ብትሆንም የኅሊትን ደስታዎችና የሲኦልን ስቃዮች በድብቅ በራሷ አጣምራ የያዘች ስለሆነ ሁለቱንም ለመቅመስ የተወሰነብኝ ፍርድ ያን ጊዜ ነበር ። በማለት ባለፈ ሕይወቱ ተከዘ ።

የመጨረሻው ወርቃማው የዐሐይ ብርሃን ከመስኩ ወደ ኋላ እያፈገፈገ ሄደ ። “ረጅም ሌሊት እየጠበቀኝ ነው ። የመጀመሪያው የነፃነት ለሊት በብቸኝነት ከነፃነቱ ጋር ላሳልፈው ወይም ከወዲያኛው ዓለም ገብተው ከሰመጡት ፡ የእግዚአብሐርን ቃላት ከሚደጋግሙት ከሼኩ ጋር ወደ ሲኦል የተጠጋ እንደእኔ ያለ ሰው ግን የሼኩንና የነዚሀን ቃላት ምንነት ለመረዳት አይችልም ። ግን ምን ላድርግ ሌላ መጠለያ የለኝ?” እያለ በሀሳብ ያብሰለስል ጀመር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 3 —

ሰዒድ ሌሊቱን ካደረበት ከሼክ አሊ ቤት ትንሽ ራቅ ብሎ የ(አል ዛህራን) ጋዜጣ ገፆችን ሲያገለባብጥ የረዑፍን ፅሑፎች አገኘ ። "ረዑፍ ፅሑፎችን ለመፃፍ የሚጠቀምባቸው ምንጮች ምን ይሆኑ?" አለ በሃሳቡ ። ካነበባቸው የረዑፍ ፅሑፎችም ስለ ሴቶች ፋሽን ፡ ስለ ድምፅ ማጉያዎችና ስለ አንዲት ስሟ ላልተገለፀ ሚስት አቤቱታ መልስ መስጠት ነበር ።

"ስለ ሴቶች ፋሽን ፡ ድምፅ ማጉያዎች ፡ መልስ ላልታወቀች ሚስት! የሚሉት በእውነት ጥሩ አስተያየቶች ናቸው ። ግን ረዑፍ ባሁኑ ጊዜ የት ይኖር ይሆን?" ሲል ራሱን ጠየቀ ። ስላለፈው ጥሩ ጊዜ ትዝ ብሎት በተለይም በተማሪዎች ሆስቴል በሚኖሩበት ወቅት የነበረው አስተዋዩና ግልፅ ልብ የነበረው ረዑፍ ለትግል የሚጋብዙ ጥልቀት ያላቸው ፅሁፎችን ሲፅፍ እንደነበር አስታውሳለሁ ። ታዲያ ያንን ፅኑ ህዝባዊ አላማውን አስትቶ ዛሬ እንዴት ቢለወጥ ነው ስለ ተራ የሴቶች ፋሽንና የድምፅ ጉዳዮች መፃፍ የጀመረው ። ማን ያውቃል በኔ ላይ የደረሰው ዓይነት ምስጢር በእርሱም ላይ ተከስቶ ይሆናል ። ማን ያውቃል ነበዊያና

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓሊ ሽ ፊታቸውን እንዳዞሩብኝ ፡ ትንሿ ልጅም እኔን እንደካደ ችኝ ዓይነት እርሁም ከሀደት ፈፅሞ ይሆናል ። ስለዚህ በምንም ዓይነት ረዐፍን ማግኘት አለብኝ ። ምንም እንኳ ሼኩ ከሰሌን ምንጣፍ በላይ የሚነጠፍ አንድ ፍራሽ እንድተ ኛበት ቢሰጡኝም ቅሉ ገንዘብ በጣም አድርጐ ያስፈልገኛል ። እንደገና አዲስ ህይወት መጀመር አለብኝ ። መምህር ረዐፍ አንተ ከሼኽ አሊ በምንም አታንስም ። በዚህ በማያስተማ ምን ዓለም ያለኸኝ አለኝታ አንተ ብቻ ነህ" ።

በአል ዛህራ ጋዜጣ ማተሚያ ቤት በመዓሪፍ አደባባይ ትንሽ ቆም አለ ። ትልቅ ህንፃ ነው ። ጥቃት ለመፈፀም አመቺ አይደለም ። እነዚህ በጋጋታ የቆሙ መኪኖች ዓይኖቻቸውን አፍጥጠው ልክ እንደተቀጠረ ዘበኛ ይህን ትልቅ ህንፃ ይጠብቃሉ ። የማተሚያ ቤቱ ድምፅ በህንፃው ምድር ቤት መስኮት ሲሰማ ልክ በእንቅልፍ ልቡ እንደሚያነበንብ ሰው ይሰማ ነበር ። ወደ ህንፃው ከሚገቡት በርከት ያሉ ሰዎች ጋር አብሮ ገባ ። ወደ መረጃ ክፍሉ ሲደርስ ቆም ብሎ ፡

"መምህር ረዐፍን እፈልጋለሁ" አለ በሚያስደነግጥ ድምፅ ።

"አራተኛ ፎቅ" አለው የመረጃው ክፍል ሠራተኛ የሰዓድን ደፋርና ቀላ ያሉ ዓየኖችን በንቀት መልክ ከተመለ ከተ በኋላ ።

እሱም ወደ ላፍቱ በፍጥነት አመራ ። ከብዙ ሰዎች መካከል የተለየ ፍጡር መስሎ ታየ ፡ ሰማያዊ ሙሉ ልብሱንና ላስቲክ ጫማውን እንዳደረገ ዓይኖቹ በድፍረት ሲመለከቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከቆሙት መካከል አንዲት ሴት አየ ። በልቡ ነበቂያንና ዓሊሽን አወገዘ ። “ወዮላችሁ” አላቸው ።

ከአራተኛው ፎቅም እንደደረሰ ተላላኪው እንዳያቆመው በመፍራት ወደ ፀሀፊው ቢሮ ፈጠን ብሎ ገባ ። የከፍሉም ትላልቅ ረጃጅም ግድግዳዎች ከመስተዋት የተሠሩ ከመሆናቸውም በላይ ወደ ዋናው መንገድም ትይዩ ናቸው ። ለእንግዳ መቀመጫ የሚሆን ወንበር ግን የለበትም ።

የረዑፍ ፀሐፊ በስልክ ከአንድ ሰው ጋር ሲነጋገር “መምህር ረዑፍ ከጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ጋር ስብሰባ እያደረገ ስለሆነ ከሁለት ሰዓት በፊት መምጣት አይችልም” ሲል ሰዒድ ሰማና በሆዱም በእርግጥ ረዑፍ ልዩ ፍጡር ሆኖ ተሰማው ። ሆኖም በደንታ ቢስነት ቆም ብሎ በዚያ የነበሩትን ሰዎች በሚያስፈሩ ዓይኖቹ እየተመለከተ እነሱን ለመቋቋም እንደሚፈልግ ዓይነት መስሎ ይታይ ነበር ። ድሮ ቢሆን ኖሮ እንደ እነሱ ያሉትን ሰዎች የሚመለከታቸው ለማጥፋት ነበር ። “ረዑፍን ከዚህ ለማነጋገር አመቺ አይደለም ። ይህ ቦታ የጥንት ጓደኞቹ የሚገናኙበት ቦታ አይደለም። ረዑፍ እንደማየው ከሆነ ትልቅ ሰው ሆኗል ማለት ነው። ቢሮው ለዚሁ በቂ ማስረጃ ነው ። ከአሁን በፊት በሀብረተሰቡ ዘንድ ብዙም የማትታወቅ ግን ለነፃነት ድምጿን አጉልታ የምትከራከር አልነዚር የምትባል የአንዲት ትንሽ መፅሔት አዘጋጅ ነበር ።

“ለመሆኑ አንተ ረዑፍ ሁኔታህ እንዴት ነው? እንደ ነበዊያ ተቀይረህ ይሆን? እንደ ሰናእም ገሸሽ ትለኝ ይሆን?”

t.me/OLDBOOKSPDF

በማለት ከራሱ ጋር ከተሟገተ በኋላ እራሱን መልሶ ወቀሰው። "እንደዚህ ያለ መጥፎ ሃሳቦችን ከአዕምሮህ ማስወገድ አለብህ ። መምህር ረዐፋ ጥሩ ዓይኖና ለነፃነት ትግል የተመዘዘ ሰይፍ ነው ። ምንም እንኳን የክፍሉ ሁኔታ የሚያስፈራራ ቢሆንም ፡ ዕውቅቶም ግራ የሚያገቡ ቢመስሉም፡ የፀሐፊዎቹ ግርማ ሞገስ አስደንጋጭ ቢሆንም ፡ ረዐፋ የሚለወጥ አይመስለኝም ። ይህ ግርማ ያለው ቦታ አንተን ለመሳም ባያስችለኝም ያንተን አድራሻ በስልክ ማውጫው ፈልጌ መኖሪያ ቤትህን ለማግኘት እችላለሁ" አለ በሀሳቡ ነገሮችን እያበጠረ ።

በውርጭ ከረጠበው ሳር ላይ በአባይ ዳርቻ ናይል ጐዳና በሚባለው ተቀምጠ መጠባበቅ ጀመረ ። ከዋክብቶች ኩል በመሰለው ሰማይ ብልጭ ድርግም ይላሉ ። አስደሳች የሆነው የአየር ሽውታ በጣም ከባድ ከሆነ የበጋ የቀን ፀሐይ በኋላ በአካባቢው ነፈሰ ። ዓይኖቹ ከ19ቱጥር ቪላ ላይ አርፈዋል ። አንድም ጊዜ ከማየት አልቦዘኑም ። እጆቹን ከጉልበቱ በማጣመር ለጥቁር አባይ ጀርባውን በመስጠት በጣም አስገራሚ የሆነውን ቪላ በማድነቅ ያስተውላል ። በሶስት አቅጣጫ በኩል ክፍት ሲሆን በአራተኛ አቅጣጫ በኩል ደግሞ የአትክልት ቦታ አለ ።፡ ዛፎቹ ይህችን ነጭ ቪላ ከበዋት ልክ የሚያሾከሹኩ ሰዎች ይመስላሉ ። እንደዚህ ያለው ትርጓሜ በድሮ ጊዜ የተለመደ ነበር ። በአሁኑ ጊዜ ግን እንደ ብርቅ ነው የሚቆጠረው ። "ለመሆኑ ረዐፋ እንዴት ከዚህ ለመድረስ ቻለ? በምን ዓይነት ሁኔታ? በዚሁ በአጭር ጊዜ! የታወቁ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሌቦችም ቢሆኑ እንደነዚህ ያሉትን ንብረቶች ለማፍራት አያልሙም ። በእውነቱ እኔም ብሆን እንደዚህ ያሉትን ቪላዎች ለማየት አልሞክርም ነበር ። እቅድ አውጥቼ ለማጥቃት በምፈልግበት ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር ። ለመሆኑ በእንደዚህ ዓይነት ቦታዎች ወዳጅነት ሊኖር ይችል ይሆን? ረዐፍ በእርግጥ ከባድ ሚስጥር ነህ ። ሚስጥርህን መግለፅ አለብህ ። ። ዓሊ በጥረቱ በዕድሜ ልኬ ያፈራሁትን ንብረት ሲዘርፈኝ እያናድድም እንዴ?" አለ በሀሳቡ ።

ሰዒድ ፀጥ ብሎ በቪላው በር ፊት ለፊት ወደሚገኘው መኪና ማቆሚያ አመራ ። ዘበኛው በሩን ሲከፍት በፍጥነት ከመኪናዋ ፊት ለፊት ትንሽ ጐንበስ በማለት ባለመኪናው እንዲያየው ቆመ ። ነገር ግን በዚያ በጨለማ ሊያውቀው አልቻለም ። በጐረናው ድምፅ ጮኽ ብሎ "መምህር ረዐፍ እኔ ሰዒድ ማህራን ነኝ!" በማለት ማንነቱን ገለፀ ። ባለመኪናውም የሰውየውን ጭንቅላት በመኪናው መስኮት ከተመለከተ በኋላ ረጋ ባለ ድምፅ "አ! ሰዒድ" አለ ።

ሰዒድ ፊቱን በትክክል ለማየት ባይችልም አነጋገሩ የሚያበረታታ መሰለውና ለጥቂት ጊዜ የመኪናው በር ሳይከፈት ፀጥታ ሰፈነ ። የመኪናው በር ተከፈተ ፡ "ና ግባ" የሚል ድምፅም ሰማ ።

ሰዒድም "ጥሩ ፡ ቀና ጅምር ነው ረዐፍ ያው የድሮው ረዐፍ ነው ። ምንም እንኳ በመስተዋት የተከበበ ዐሀፊምና የሚያስገርም ቪላ ቢኖረውም ረዐፍ ያው የጥንቱ ነው" እያለ ሲያስብ ረዐፍ መኪናዋን የቫዮሊን ቅርፅ ወዳለው ጋራጅ

t.me/OLDBOOKSPDF

አስጠጋ ።

“ሰዒድ እንደምን አለህ? መቼ ወጣህ?”

“ትናንት”

“ትናንት?”

“አዎን ። ወዳንተ መምጣት ነበረብኝ ግን አንዳንድ አስቸኳይ ጉዳዮች ስላጋጠሙኝ እረፍትም ያስፈልገኝ ስለነ በር በሼክ አሊ ቤት አሳለፍኩኝ ። ታስታውሳቸዋለህ?” አለ ከመኪናው ወርደው ወደ ቪላው መግቢያ ሲያመሩ ።

“በደንብ ነው የማስታውሳቸው ። እንደ ያባትህ ሼክ የነበሩ አይደሉም?” ከአንድ ጊዜ በላይ ከእንተ ጋር በመሆን አብረን ዘምረናል አሸብሽበናል ። በጣም አዝናኝ ነበር ። የሼኽ ተክታዮች ሲዘምሩና ሲያሸበሽቡ ያስደስተኝ ነበር” አለ ረዐፍ ።

ሠራተኛው የሳሎን ቤቱን መብራት አበራ ። የሰዒድ ዓይኖች ዋገቱ ። በመብራቶቹ አስገራሚነትና ብዛት ተደ ነቀ። በየግድግዳው የተሰቀሉት መስታወቶች የክፍሉን ብር ሃን በእጥፍ እንዲጨምርና እንዲያንፀባርቅ አደረጉ ። በክፍሉ የነበሩት ታሪካዊ ዕቃዎችና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ቅርሶች ከጨለማ ወደ ብርሃን የወጡ መሰሉ ። የክፍሉ ጣሪያ በጣም የተዋበ ከመሆኑም በላይ ወንበሮቹና ጠረጴዛዎችም ቢሆኑ ዓይን የሚማርኩና ምኞት የሚሰጡ ናቸው ። ወለሉም በሚያስገርሙ ምንጣፎች የተዋበ ነው ። በመጨረሻ የሰዒድ ዓይኖች በመምህር ረዐፍ ሙሉና ክብ ፊት ላይ አረፉ ። ይህን ፊት በጣም አድርገው የሚወደው ነበር ። ለረጂም ጊዜ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይመለከተው ስለነበር አጥንቶታል ። ሰዒድ አለፍ አለፍ እያለም በጨረፍታ አንዳንድ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች ይቃኛል ። ወደ አትክልት ቦታ ትይዩ የሆነውን የበረንዳ በር ሠራተኛው እየከፈተ መጋረጃውን ሲገልጥ ሰዒድ የረዑፍን ፊት ያጠና ጀመር ። ክፍሉንም በድንገት ከዛፎችና ከአበባዎች የመጣ ግሩም የሆነ አስደሳች መዓዛ ያለው ሽታ አወደው። ሰዒድ በጣም አድርጐ ሞንቅላቱን አዞረው ። በዚህ ላይ የረዑፍን ፊት ሲመለከት ከውሩሬው የተነሳ ሊፈርጥ የደረሰ መስሎ ታየው ። ተገረመ ። ይሁንና ምንም እንኳን መልኩ በድሎት ቢለወጥም ከድሃ ቤተሰብ ተወልዶ ለዚህ የበቃው ረዑፍ ዛሬም ቢሆን ደፍጣጣ አፍንጫውንና ትልቅ አገጩን ማግኘት ሊለውጣቸው አልቻለም ። ለመሆኑ ይህ የመጨረሻ ተስፋዬና ድጋፍ ይሰጠኛል የሚለው ፍጡር ቢወድም በዚህ ዓለም ምን ዓይነት መጠለያና ድጋፍ ለማግኘት ይችላል?

ረዑፍ በረንዳው አጠገብ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠ። ሰዒድንም በጣም ምቾት ባለው በአስገራሚ ቅርፃ ቅርፆች ባጌጠው ተንቀሳቃሽ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ጠቆመው ። ሰዒድም እንዳመሉ ሳያመነታ በማድ የለሽነት ተቀመጠ ።

“እሄን ፍለጋ ወደ ጋዜጣ ክፍል መጥተህ ነበር?” አለ ረዑፍ እግሮቹን በመዘርጋት ።

“አዎን ግን ለመገናኘት አመቺ ቦታ እንዳልሆነ ተረዳሁ!”

“አዎ የጋዜጣ ሥራ ምንም ዕረፍት ስለማይሰጥ ቀኑን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሙሉ በሥራ እንደተጠመድን ነው ። ለመሆኑ ብዙ ጠበቅህ ወይ? አለው ።

"የአንድ ሰው ዕድሜ ያህል!" አለ ፈገግ ብሎ ።

ረዑፍ እንደገና ሳቀና ከእለታት አንድ ቀን መቼም ይሆን ጐዳና ሳታውቀው አትቀርም?"

"እም ይህና ደንበኞች ነበሩኝ ። የደንበኝነት ፋድልን ቪላ በጐበኘሁበት ጊዜ በአሥር ሽህ ብር ነው የወጣሁት ። ከፊልም ተዋኒያኗ ከሞኪብ ቪላ ደግሞ ብርቅ የሆኑ በሁለት ጆሮዎች የሚደረጉ አልማዞች አግኝቼአለሁ" አለ ሰዒድ ሳቅ እያለ ።

ሠራተኛው የመጠጥ ጠርሙሶችንና ሁለት ብርጭቆዎችን የያዘውን ተሽከርካሪ ፡ አንድ አነስተኛ ባለ ወይን ጠጅ ቀለም ፡በበረዶ የተሞላ ዕቃ እንዲሁም ፖም ፡እንደ ፒራሚድ የተደረደሩትን ሳህኖች ። የተለያዩ አፕፊቲሮችን የያዙ ጠርሙሶችና ውሃ የተደረገበት ብራማ ጀበና ይዞ መጣ ። ረዑፍ ሠራተኛው የሚያስፈልገውን ነገር ካቀረበ በኋላ እንዲሄድ ጠቆመውና ሁለቱን ብርጭቆዎች በውስኪ ሞላው። አንዱን ለሰዒድ ሰጠ ፡ ሌላውን ከፍ አድርጐ በማንሳት "ለነዓነትህ" በማለት ከሰዒድ ብርጭቆ ጋር አጋጨ ።

ሰዒድ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረጋት ። ረዑፍ ግን በከንፈሮቹ መካከል አድርጐ ፉት አለና " ሰዒድ ለመሆኑ ልጅህ እንደምን አለች? ሳልጠይቅህ ረስቼ ለምንድነው ሼክ አለ. ቤት ያደርከው?" አለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ትዳሬ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ያወቀ አልመሰለ ኝም ። ግን ልጄን ያስታውሳታል" አለ በሀሳቡ ። ሰዓድ በዝርዝር ስለ ደረሰበት ስቃይ ካስረዳ በኋላ "ትናንት የአል-ሰይረፊን የእግር መንገድ ጐበኘሁ ። ከዚያም እንደጠበቅሁት አንድ ነጭ ለባሽ ይጠብቀኝ ነበር ። ልጄም ከዳችኝ ። ጨክችብኝም" ብሎ ሳያስፈቅድ ሌላ ብርጭቆ ቀድቶ ጠጣ ።

"ይህ የሚያሳዝን ታሪክ ነው ፡ ግን ልጅህ በዚህ አትወቀስም ፡ አሁን ልታውቅህ አትችልም ፡ ወደፊት እያደገች ስትመጣ ታውቅሃለች ፡ ትወድህማለች" አለው ።

"እኔ በሷ ዘር ምንም እምነት የለኝም"

"አሁን አንተ እንደዚህ ትላለህ?" ነገ ምን እንደምትል ማን ያውቃል? ሀሳብህን ራስህ ትቀይር ይሆናል ። ይህ በዓለም ያለ ነገር ነው" አለው ።

ስልክ ተደወለ ። ረዐፍ ወደ ስልኩ አመራ ። መነጋገሪያ ውን አንስቶ ትንሽ ካዳመጠ በኋላ ፊቱ ፈካ አለ ። ስልኩን አንስቶ ወደ በረንዳ ወሰደው ። ሰዓድ ከመጀመሪያ ጀምሮ በዓይኖቹ ትክ ብሎ ይከታተለው ስለነበር ተናጋሪዋ ሴት መሆኗን አወቀ ። "ይህ ፈገግታና ወደ በረንዳ ጉሮ ለሴት ብቻ መሆን አለበት ። ለመሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ ገና ወንደላጤ ነው ማለት ነው?" ካለ በኋላ በሃሳቡ "ጐን ለጐን ተቀምጠን መጠጥና ውይይት መለዋወጥና ይህንን የመሰለ ግንኙነት ሊደገም አይቻልም" የሚል ስጋት አደረበት ። ለምን እንደሆነ ስላላወቀው ደበረው ። ይህ የዛሬ ጉብኙቱ አለ ዕቅድ በየመንገዶች እንደሚያደርጋቸው የማጥቃት ዘመቻ መስሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

ታየው ። ይህንንም ውስጣዊ ስሜቱ ያረጋግጥለታል ። ረዑፍ ዛሬ ሳይወድ እንደተቀበለው አይጠራጠርም ። ብዙም ሳይቀየር አልቀረም ፡ ከድሮው ረዑፍ ጥላው ብቻ ነው የቀረው ። ሰዒድ የረዑፍን በድንገት መሳቅ ስማና ሳቱም በበረንዳው ሲያስተጋባ ይበልጡን ደበረው ። ስሜቱም ተቀየረ ። ቀስ በለ አንድ ፖም አንስቶ መግመጥ ጀመረ ። አንድ ነገርም ትዝ አለው ። ህይወቱ ከዚህ በስልክ እየሳቀ ከሚነጋገረው ሰው ሃሳብ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆኑን ። ግን ረዑፍ ይህን ሃሳብ ቢከድስ ምን መደረግ ይኖርበታል? ለዚሁ ከፍተኛ ዋጋ መክፈል አለበት ።

ረዑፍ ከበረንዳ ተመልሶ መጣ ። ስልኩንም ከቦታው አስቀመጠው ። ደስ እያለው ተቀመጠ ። "እንኳን ለነዓነት በቃህ ፡ ነዓነት የተከበረ ዕንቁ ነው ። ምንም ነገር የነዓነትን ያህል ዋጋ ያለው ሊኖር አይችልም ።" አለ ከፊቱ ከቀረበው ስጋ አንስቶ እየበላ ። ሰዒድም ንግግሩን በደንብ የሰማ በማይመስል ሁኔታ እውነት መሆኑን ጭንቅላቱን በማወዛ ወዝ አረጋገጠ ።

"አሁን ከእሥር ቤት ወጥተህ ሌላ አዲስ ዓለም ውስጥ ገባህ?" ሁለቱን ብርጭቆዎች ሞላቸው ። ሰዒድ ግን የቀረበለትን ምርጫ ምግብ እያማበሰበሰ አትኩሮ ጓደኛውን ረዑፍን አስተዋለ ። የጥላቻ ስሜት የሚመስል ከፊቱ ተመለከተ ።

"ከልቡ የሚወድህ ከመሰለህ ዕብድ ነህ ማለት ነው ። ከአንተ በላይ መሆኑን እወቅ ። ይህም ለጥቂት ጊዜ ነው ። እንደ ውሀ ተኖ ይጠፋል ። ማንኛውም ከህደት ቀላል ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን ከህፃንነት ዓለም ጀምረህ ከምታውቀው ፡ ብዙ ምስጢርና ሀሳብም አብረኸው የተካፈልከው ረዑፍ እንኳን ከዳተኛ ከሆነ ከእንግዲህ በዓለም ላይ ምን ዓይነት ዕውነትና መተማመን ሊኖር ይችላል ?" አለ ሰዒድ በሆዱ ።

ረዑፍ በቻይና ዓይነት ቅርፃ ቅርፅ ተውባ ከተሠራችው ትንሽ ሳጥን ውስጥ ሲጋራ እያወጣ እንዲህ አለ ።

"ሰዒድ ጓደ ማንኛውም ህይወታችንን ሊያበላሽና ሊያሰናክል የሚችል በአሁኑ ጊዜ ፈጽሞ ተውግዷል"

በእሥር ቤት እንሰማቸው የነበሩ ዜናዎች በጣም አስደንግጠውን ነበር ። ማን እንደዚህ ያለ ሲሳይ ያገኛል ብሎ ያምን ነበር?" አለ ሰዒድ አፉ በምግብ ተወጥሮ ፈገግ በማለት። "ጦርነት አበቃ ማለት ነው?" አለ ሰዒድ ።

"የተኩስ ማቆም ስምምነት ይደረግ ማለቱ ነው! ማንኛውም ትግል ተስማሚ የሆነ መስክ አለው" አለ ረዑፍ ።

"ይህ አስደናቂ የሆነ ሳሎን ቤት ፈረስ የሚያስጋልብ ትልቅ መስክ አይደለም እንዴ?" አለ ሰዒድ አካባቢውን በዓኖቹ እየቃኘ ሳያስበው በድንገት ስለተናገረ ይቅርታ እየጠየቀ ፡ በጓደኛው ዓይኖች ቀዝቃዛ አመለካከት ተመለከተ።

"አንደበትህ ጨዋነት አያውቅም ማለት ነው ምን ማለትህ ነው?" አለ ረዑፍ በሰለለ ድምፅ

"ማለቱ እኮ አርአያነት ያለው ግሩም ነው"

"መዘላበድ የማይረባ ነገር ነው ። ምን እንደምታስብ በግልፅ ተናገር ፡ እኔ ደህና አድርጌ እንደማውቅህ አንተም

t.me/OLDBOOKSPDF

በደንብ ታውቃለህ?" አለ ረዐፍ ግንባሩን በመከስከስ ግልፅ በሆነ ጥላቻ ።

"እኔ ፈፅሞ መጥፎ ነገር አላሰብኩም" ሲል መለሰ ሰዒድ ጥፋቱን ለመሸፋፈን እንደሚፈልግ ሆኖ ።

"አንተ ዘወትር ማሰብ ያለብህ እኔ በላቤና በድካሜ የምኖር መሆኔን ነው" አለ ረዐፍ ።

"ይህ ትክክል ነው ። ማንም ሰው አይጠራጠርም ። በእግዚአብሔር ይሁንብህ እስከዚህ ድረስ አትናደድ ።" ረዐፍ ሲጋራ አውጥቶ በንዴት ማጨስ ጀመረ ። ዐጥቶም ሰፈነ ።

"እንደምታውቀው ገና የእሥር ቤቱ ትዝታ ስላለቀቀኝ ስነ ስርዓትም ሆነ የአነጋገር ስልት እንደገና ለመማር ረጅም ጊዜ ይጠይቃል ። አትርሳ አእምሮዬ እየዞረብኝ ነው ልጂ ከከዳችኝ በኋላ" አለ ሰዒድ መብላቱን ለማቆም እየተገደደ ፡ ይቅርታ ጠያቂ በመምሰል ።

ረዐፍ ይቅርታ ያደረገ ይመስል ቅንድቡን በአምንታ ወደ ላይ በማድረግ ከእሱ ፊትና ከተደረደረደው ምግብ ለመብላት ፈቃድ የሚጠይቁ የሚመስሉት የሰዒድን ዓይኖች ካስተዋለ በኋላ "ብላ" አለ ።

ሰዒም ምግቡን ጨርሶ ጠራረገው ። ስለተፈጠረው ችግር ምንም ዓይነት ስሜት አልነበረውም ።

"ሁኔታህ ከስር መሰረቱ መቀየር አለበት ። ስለ ወደፊት ዕድልህ ምን አስበሃል?" አለ ረዐፍ ውይይቱን ለማቋረጥ እንደሚፈልግ ሰው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ያለፈው ታሪኬ ስለ የወደፊት ዕድሌ እንዳስብ አያደር ገኝም ” ሰዓድ ሲጋራውን እያቀጣጠለ ።

“እኔ እንደሚመስለኝ በዚህ ዓለም ሴቶች ከወንዶች ይበዛሉ ። ስለዚህ በአንድ ሴት ክህደት ብዙ አትጨነቅ ። ልጅህ እንደሆነች አንድ ቀን ታውቅሃለች ። ታሪቅርህማ ለች። አሁን የሚያስፈልግህ የምትተዳደርበት ሥራ መፈለግ ብቻ ነው” አለ ረዐፍ ።

“በእሥር ቤት ሳለሁ የልብስ ስፌት ተምሬ አለሁ” አለ ክፍሉ ውስጥ ወደሚገኘው ማሬኪና እንቅልፍ የያዘው ወደ ሚመስለው የቻይና ጣዖት ሐውልት እየተመለከተ ።

“የስፌት ሱቅ ለመክፈት ትፈልጋለህ ?” አለ ረዐፍ በመገረም ።

“ፈፅሞ አላድርገውም!” አለ በእርጋታ መልክ ።

“እሺ ምን ለማድረግ ነው የምትፈልገው?”

“እኔ በህይወቱ አንድ ሥራ ብቻ ነው በደንብ መሥራት የምችለው” አለ በመጥፎ አመለካከት ።

“ምን ማለትህ ነው ወደ ሌብነት ልትመለስ?” አለ በመረበሽ ።

“እንደምታውቀው ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኝ ሥራ ነው.”

“እንደምታውቀው ! ከየት ነው የማውቀው?” አለ ረዐፍ በክፉ ዓይኖቹ እየተመለከተው ።

“እስከዚህ ድረስ መናደድ የለብህም ፡ ለማለት የፈለ ከት ድሮ እንደምታውቀው ማለቱ እንጂ አሁን አይደለም”

t.me/OLDBOOKSPDF

“ረዐፍ የሰዒድን አባባል የተቀበለው በመምሰል ካንገቱ ደፋ አለ ። ፊቱ ግን ሲበራ አልቻለም ።

“ሰዒድ ዛሬ እንደ ትናንት አይደለም ። ሌባ ሆነህ ጓደኛዬም ነበርክ ። አንተ በምታውቀው ምክንያት ዛሬ ግን ትናንት አይደለም ። ወደ ሌብነት ዓለም ከተመለስክ ሌባ ብቻ ነው የምትሆነው ። ጓደኛ አይኖርህም ማለቱ ነው!” አለ ረዐፍ ንግግሩን ለማቋረጥ እንደሚፈልግ ሰው ።

ሰዒድ በረዐፍ አነጋገር በመቀየም ከተቀመጠበት ብድግ ካለ በኋላ ስሜቱን በመግታት እንደገና ተቀመጠ ።

“እሺ ለእኔ የሚስማማ ሥራ ፈልግልኝ” አለ ሰዒድ ረጋ ብሎ ።

“የሆነ ሥራ ተናገረ እኔ እየሰማሁህ ነው” አለ ረዐፍ ።

“ከአንተ ጋዜጣ በጋዜጠኝነት ብሰራ ደስ ይለኛል! እንደምታውቀው በአንተ ጥቆማ በርከት ያሉ መዕሐሮችን አንበሌአለሁ ። ስላለኝ በቂ ዕውቀትና ጉብዝናዬም መስክረህ ልኛል” አለ ሰዒድ በማሾፍ ።

“ለቀልድ ጊዜ የለንም ። አንተ የአባባሩን ስልት አታውቅም ። ግና ትናንት ነው ከወህኒ ቤት የወጣኸው ፡ ጊዜዬን በከንቱ ነው የምታጠፋው” አለ ረዐፍ ራሱን በንዴት በማወዛወዝ ።

“እንዲህ ከሆነማ የማይረባ ዝቅተኛ ሥራ መምረጥ አለብኝ ማለት ነው?”

“ዝቅተኛ ሥራ የሚባል ነገር የለም ። የሚያስከብር ሥራ እስከሆነ ድረስ” ሰዒድ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት

t.me/OLDBOOKSPDF

አደረበት ። ዓይኖቹን በዚሁ በሰፊው ሳሎን ያመላልሳቸው ጀመረ ። "እንዴት ጥሩ ነው ሀብታሞች በድህነታችን እንድንኖር ሲመክሩን! እርግጠኛ ነኝ ከጊዜህ ብዙ እንደወሰ ድኩ" አለ ሰዒድ በእርጋታ ።

"አዎ እኔም ብዙ የሥራ ጫና አለብኝ" አለ ረዑፍ በግልፅነት እንደ ግንቦት ፀሐይ በጠራ አነጋገር ።

"ስለተደረገልኝ መስተንግዶ ፡ የራት ግብዣና ርህራሄ አመሰግናለሁ ።"

"ለጊዜው ለችግር ማቃለያ እንዲሆንህ እንካ ይችን ተቀበለኝ ። ይቅርታም አድርግልኝ በሥራ ጫና ተጠምጀለሁ ስላልኩህ ሌላ ጊዜ እንደዛሬ ማታ ነፃ ሆኜ ልታገኘኝ አትችልም" አለ ረዑፍ የገንዘብ መያዣውን ቦርሳ በማውጣት ሁለት ባለ አምሳ ብር ኖት በመስጠት ።

"እግዚአብሔር ሀብትህን ይጨምርልህ" አለ ሰዒድ ገንዘቡን በደስታ እየተቀበለ ሞቅ ባለ አጨባበጥ ከጨበጠው በኋላ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

—4—

“የረዑፍ ገዕታ·ና ማንነት በገሀድ እየታ·የ ነው ። የበሰበሰ ሬሳ ምድር የምት·ተፋ·ው ሰው ይመስላል ። የድሮው ረዑፍ ግን የለም ። እንደ ትናንት እንደ ነበዊያ ፍቅርና እንደ ዓሊሽ ታ·ማኝነት ጠፍቷል ። ስለዚህ በጣፋጭ ቃላቶቹ መታ·ለል የለብኝም ። መርዛም ፈገግታ·ምችን ፡ ለይስሙላ ቸርነቱም ልግስናው·ም ቢሆን ከልብ የመነጨ ሳይሆኑ ራስን ለመከላከልና ጋጢአትን ለመሸፈን የሚደረጉ ናቸው ። በዚህ ምክንያት ብቻ ነው ወደ ቤቱ እንድገባ ያደረገው ። በጣም ይገርማል እርሱ ራሱ በያዝከ·ት የሌብነት ሥራ እንድገፋበት ሲያበረታ·ታ·ኝ ኖሮ ሃሳቡን በኔ ላይ ካሠረፀ በኋላ ዛሬ እኔ እንደዚህ ሆኜ ቢያየኝ የድሮ ዕምነቱንና አመለካከቱን ለው·ጠ ተስፋ·ዬን አመንምኖ እንደማይተዋወቅ አዲስ ሰው ይሁን ብኝ? ለፈፀመብኝ በደል የመ·ቀጠም ተራራ ተደርምሶ ቢቀብ ረው አንኳን ሊያረካኝ አይችልም” አለ ሰዒድ በሃሳቡ ። በጣም አድርጌ ነው የምገረመው ። ለመሆኑ አንተ ራስህ ታ·ምናለህ ወይ? ህሊናህስ ቢሆን አይወቅስህም ማለት ነው? በመስተዋቶችና ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው የታሪክ ቅርሶች በተዋበው ቤትህ ውስጥ እንደገባህ ሁሉ ወደመንፈስህም

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠልቁ ለመግባት ብችል ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር ። ግን እርግጠኛ ነኝ ፡ መንፈስህም ሆነ ሀሊናህ በክህደት የተበከለ ስለሆነ አንተ ከዓሊሸና ነበዊያ በምንም አትሻልም የነሱ ሌላ ገፅታ ነህ ። እያለ በሀሳቡ ሲያጉላላ አንድ ነገር ትዝ አለው ።

የዛሬን አያድርገውና ዓሊሸ በአልሰይረፌ መንገድ በሚገኘውና የራሴ ቤት በነበረው "ከሱ ለመገላገል ለፖሊስ መጠቆም አለብኝ ብሎ ሊያስይዘኝ ሲናገር የልጄ እናት ግን እየሰማች ዝም አለች ። ያቺ ሴት እኔን በፍቅርህ ሞቼአለሁ አንተ የወንድ መጨረሻ ነህ እንዳላለች ሁሉ ። እኔ ወንዱ ሰይጣንም ቢመጣ ሊከበኝ በማይችለው በአልሰይረፌ መንገድ ውርደት ደረሰብኝ ። ተከበብከኝ ፡ ተደበደብከኝ ፡ ዱላም ጥፊም በየአቅጣጫው እንደውርጅብኝ ወረደብኝ ። ረዐፍ አንተም ብትሆን ከዓሊሸ የከፋህ ካልሆንክ አትሻልም ፡ ይበልጡኑ ያንተ ወንጀል ከባድ ነው ። ምክንያቱም አንደኛ የተማርክ ስለሆንክ ፡ ሁለተኛ በጣም ወዳጄና አስተማሪዬ ስለነበርክ ነው ። አንተ ነህ ለእሥር ቤት ያበቃኸኝ ። አንተ ግን በብርሃንና በመስተዋት የሚያንፀባርቅ ከፍተኛ ቪላ ውስጥ ሆነህ ትፈነጥዛለህ ። ስለ ሀንፃዎችና ደሳሳ ቤቶች ታስማቸው የነበሩትን ጥቅሶች ረሳህ እንዴ? እኔ ግን ምንም ቢሆን አልረሳቸውም !"

ከረዐፍ ቪላ አጠገብ የአባስ ድልድይ በሚባለው ከአንድ በድንጋይ ከተሰራ መቀመጫ ላይ አረፍ ብሎ ስለ ቦታው ማጥናትና መጠራጠርም ጀመረ ። "የሚሻለው አሁኑኑ ብፈፅመው ነው" አለ በጨለማ ። ድምፁን አጉልቶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልክ ንግግር እንደሚያደርግ ሰው ። "ረዐፍ በቂ ጊዜ ሳያገኝ ከድንጋጤው ሳይወጣ ፡ አዕኑኑ ፡ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ማመንታት አያስፈልግም" የሚል ሀሳብ መጣበት ። "መያው ያው ያንተው ነው ። ተግባሩም ሀጋዊ ነው ። በተለይ በረዐፍ ላይ የዚህ ሀሳብ ደጋፊ ከሆነው ሲፈፀም" በማለት እራሱን በራሱ አደፋፈረ ።

"እነዚህን እርኩሶችን ካስወገድኩኝ በኋላ በዚህ ዓለም ለኔ የሚሆን መደበቂያ ቦታ አላጣም ። ያሰፈሙን የእነ ነበሚያን ፡ ዓሊሽንና ረዐፍን ከህያት በመርሳት በዚህ ዓለም ለመኖር እችላለሁ ወይ? ብችል ኖሮ ብዙ ችግሮች በተቃለሉልኝ ነበር ። ጥሩ የህይወት ዘመን ለመኖር ከመቻሌም በላይ ከስቅላትም እድን ነበር ። ነገር ግን ሂሳቤን ሳላጣራ ምን ዓይነት ኑሮ ለመኖር ይቻላል ያሰፈሙንም ለመርሳት የማልችልበት ምክንያት አለኝ ። ይኸውም ያለፈ ሳይሆን እሁን ያለ በመሆኑ ነው ። የዛሬ ምሽት የጀብደኝነት ሥራዬን መጀመሬን የማበስርበት ምሽት ነው ። በጣም ጠቃሚ የሆነ ጀብዱ ይሆናል ።"

ጥቁር አባይ ልክ እንደ ጨለማ ጥቁር ማዕበሎችን ይዞ ከአንዳንድ ጐዳናዎች ባለ አነስተኛ መብራቶች የወሰደውን ብርሃን መልሶ በሚያንፀባርቅበት አቅጣጫ ጉሀውን ቀጠለ። አካባቢው እረጭ ፡ ጭጭ ብሏል ። ጐህ ሊቀድ ሲቃረብ ከዋክብቶችም ወደ ምድር እየተቃረቡ ሲመጡ ሰዓድ ከተቀመጠበት ብድግ አለና ቀጥ ብሎ ቆመ ። በጥቁር አባይ ዳርቻ በቀስታ ዓላማ ወዳደረገው ቦታ አመራ ። መብራቶችን ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገን በመተው ፍጥነቱንም በመቀነስ እንዳለ በሶስት በኩል ክፍት የሆነው ቪላ ወለል ብሎ ታየው ። መንገዱን በንቃት ተቆጣጠረ ። መሬቱን ፡ የአጥር ግንቡን ፡ የአባይ ዳረቻዎችን ከቃኘ በኋላ ወደ ቪላው ትክ ብሎ ተመለከተ ። ቪላው ዓይኖቹን የጨፈነ ይመስላል ። ዛፎችም አጋንንት መስለው ዘብ ቆመዋል ። ከሀያትም ከቤቱ ውስጥ ፀጥታ በሰፈነበት ተኝታለች ። ጠቃሚ የሆነ ሀብት የሚገኝበት ከመሆኑም በላይ ሰረጂም ጊዜ የማታለልና የከሀያት አመርቂ መልስ ጀብደኝነት ብቻ ነው የሚሆነው ።

ገዳናውን ረጋ ብሎ ሳያመነታ ፡ ቀኝ ግራ ሳይል አቋረጠና ወደ አጥሩ ግንብ ሲያመራ ከፊቱ የሚገኙትን ነገሮች በጥንቃቄ አጤነ ። ቦታው ነፃ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በቅፅበት የፅጌረዳና የጃስሚን አበቦች ወደሚገኙበት አፀድ ውስጥ ገባ ። ፀጥ ብሎ ቆመ ። ከባለቤቱ በስተቀር ሌላ ውሻ ቢኖር በአፁኑ ሰዓት ከፍ ያለ ጩኸት ባሰማ ነበር ነገር ግን ምንም ዓይነት ሹክሹክታም አይሰማም ። ረዑፍ ያንተ ተማሪ ካለህ ሃብት ትንሽ ለመቀነስ ወዳንተ እየመጣ ነው ። ሰውነቱን ቀለል በማድረግ ግንቡን ዘሎ በተሞላበት በእግሮቹ ጣቶች እንደ ዝንጀሮ ሳይደናቀፍ መውጣት ጀመረ ። ሰውነቱን ባለው ኃይል በማንሳት የአጥሩ ሹል ብረቶች ሳይነኩት ዘሎ ከአፀዱ ውስጥ ገባ ። እግሮቹ በዛፍ ቅርንጫፎች ስለተጠላለፉ ትንፋሹን ለመመለስ ትንሽ ቁጭ ብሎ እንደገና ቆመ ። "ወደ ጣርያው ወጥቼ ከዚያ ቀዳዳ ቦታ ፈልጌ ወደ ቤቱ መግባት አለብኝ ። ነገር ግን ምንም ዓይነት መሣሪያ

t.me/OLDBOOKSPDF

አልያዝኩም ። የእጅ ባትሪም ሆነ ስለቤቱ ጥልቅ የሆነ ዕውቀትም የለኝም ። ነበሚያ ብትኖር ካሁን ቀደም እንደምታ ደርገው ልብስ እንደሚያጥብና እንደሚያሰጣ ሰው መስላ አካባቢውን በመሰለል መውጫና መግቢያውን በማጥናት ቅድመ ዝግጅት ታደርግልኝ ነበር ። እሷ በአሁኑ ሰዓት ከዓሊሽ ጋር ዓለሚን እየቀጨች ነው ! “ፊቱን ጠቆር በማድረግ እነዚህን መጥፎ ሀሳቦችን ለማባረር ሞከረ ። ወደ መፈት ቸኮንቃቂ ወረደ ። ከዚያም ወደ ቪላው ግንብ ተንሸቀቀ ። ከብዙ ጥረትና ፍለጋ በኋላም የቤቱን አሽንዳ አገኘ ። ጥበብ በተሞላበት ዘዴ አክሮባት እንደሚሠራ ሰው የቪላውን ግንብ መውጣት ጀመረ ። ዓላማው ወደ ጣራ ለመድረስ ነበር ። ነገር ግን አንድ ክፍት መስኮት ከእሱ ትንሽ ራቅ ባለ ቦታ አጋጠመውና ወዲያውኑ መሞከር አለብኝ አለ ። በእግሩ ነካ ቢያደርገው ብርግድ ብሎ ተከፈተ ። አዕምሮውን በመቆጣጠር እንደምንም ብሎ ወደ መስኮቱ ደረሰ ። ከዚያም ዘሎ ወደ ክፍሉ ገባ ። ማዕድ ቤት ሳይሆን አይቀርም ብሎ ገመተ ። ጨለማው በጣም አደናገረው ። ከብዙ ትግል በኋላም የክፍሉን በር አገኘ ። ወደ ውስጥ ገባ ሲልም የባሰ ጨለማ እንደሚያጋጥመው ገመተ ። የረዐፍ የገንዘብ መያዣ ቦርሳና አንዳንድ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ቅርሶችም እንደ ሀልም ሆነው ታዩትና ወደፊት መግፋት አለብኝ አለ ። በበሩ በኩል ግድግዳውን በእጁ እየዳሰሰ ሲሄድ ከየት አቅጣጫ እንደመጣ ያላወቀው የአየር ሽውታ ፊቱን ገረፈው ። አየሩ ከየት እንደሚመጣ ገረመው ። ወደ ግድግዳው ጠርዝ ሲደርስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠርዙን ተከትሎ ዞረ ። በድንገት አንድ ዓይነት መሰናከል አጋጠመውና አነስተኛ ድምፅም ሲሰማ ደንገጥ ብሎ ቆም አለ ። "የመስኩቱ መጋረጃ መክፈቻና መዝጊያ ሽቦዎች ሳይሆኑ አይቀርም" አለ ። ወደ ግቡ መድረሱን ሲያረጋግጥ በኪሱ የያዘው ክብሪት ትዝ አለው ። ክብሪቱን ከኪሱ በማውጣት ፋንታ ወደ መስኩቱ መጋረጃ ሽቦዎች መለስ ብሎ ድምፅ እንዳይሰጡ አስተካክላቸው ። ትንሽ ለማየት እንዲያስችለውም ክፍት ቦታ አደረገ ። ከወንበሩ ይሁን ወይም ካልታወቀ ሌላ ቋሚ ነገር ጋር በጋጭም ቅሉ እንደምንም አለፈው ። አንገቱን ቀና በማድረግ ድንግዝ ብርሃን ተመለከተ ። ቋሚ መብራት ሳይሆን አይቀርም የሚል ተስፋ ቢያድርበትም ቅዠት መሰይ ስሜት ተሰማው ። ከሩቅ ይታይ የነበረውም ብርሃን በጨለማ ተዋጠ ። ክብሪት አውጥቶ ለመጫር አሰበ ። በድንገት አንፀባራቂ የሆነ ብርሃን ከየአቅጣጫው በላዩ ላይ አረፈ ። ኃይለኛ ብርሃን ከመሆኑ የተነሳ ልክ እንደ ከባድ ቡጢኛ ለመዘረር የሚሰነዘር ምት የሚመስል ተሰማው ። ዓይኖቹ ሳይፈልግ ተዘጉ ። ሲከፍታቸውም ረዥም ትንሽ ራቅ ብሎ ቆሞ አየው ። ከፒጃማ በላይ ረጂም ጋውን ደርቦ ልክ ጭራቅ ይመስላል ። አንድ እጁን ከጋዋኑ ኪስ ከታል ፡ ኪሱም ተወጥሯል ። መሣሪያ የያዘ ይመስላል ። ትኩር ብሎ ሲመለከተው የሰዒድ የተሸነፈ ልብ ቀዝቃዛ ውሃ እንደተደፋበት ሆኖ ከንፈሮቹም ድርቅ ብለው ገጦመዋል ። ሰዒድም የሚመለከተው ነገር ቢኖር ጥላቻና ብስጭት ብቻ ነው ። ሁሉም ነገር ፀጥ አለ ። ፀጥታም በአስከፊነቱ ከወሀኒ ቤቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግንብ የባሰ ነበር ።

“ምንድነው? ምን ነካህ? እንዴት ፈጥነህ ተመለስክ?” የእሥር ቤቱ ኃላፊ በቀልድ መልክ እንዲህ ሳይለኝ አይቀርም እያለ ሰዒድ ሲያስብ

“ፖሊስ እንጥራ?” የሚል አስደንጋጭ ድምፅ ከበስተ ጀርባ ሰማ ። ሰዒድ ዞር ሲል ሶስት የረዑፍ ዘበኞች ቆመው ተመለከተ ። ረዑፍም ዝምታውን አቋረጠና “ወጣ በሉ ፡ ከውጭ ጠብቁ” አለ ዘበኞቹን ።

ሰዒድም ፊቱን ዘወር ቢያደርግ የረዑፍን ጭጋግ የመሰለውን ፊት አየ ። አስቀያሚ የሆነውን ድምፁንም ሰማ።

“በእኔ ላይ ያንተን ቅጥፈትና የሌብነት ዘዴዎች መሞከር ሞኝነት ነው ። እኔ ከሰር መሠረትህ ነው የማውቅህ፡ እንደተከፈተ መፅሐፍ ነው የማነብህ” አለው ። ሰዒድ መናገር አልቻለም ። ተስፋም እንደመቁረጥ እያለ ከደረሰበት አስደንጋጭ ሁኔታ ለመላቀቅ እየሞከረ ውስጣዊ ስሜቱ እንዲህ አለው” ትናንት ወደ ነበርክበት እሥር ቤት ትመለስ ይሆን?” አያለ በሀሳቡ ።

በደንብ ተዘጋጅቼ እጠባበቅ ነበር ። እንዲያውም የምትገባበትንም መንገድ አዘጋጅቼ ። ግን ግምቴ የተሳሳተ እንዲሆን ከልብ እመኝ ነበር ። ስላንተ የሚሰጥ ግምት እንዴት ይሳሳታል?” አለ ረዑፍ ቱማ በተሞላበት ስሜት ።

ሰዒድ ለአንድ አፍታ ዓይኑን ጨፈን ካደረገ በኋላ ከእግሩ ሥር ያለውን በሰም የሚያንፀባርቀውን ሳንቃ እያየ ከዝምታው ለመውጣት ሳይሞክር ዓይኖቹን ወደላይ አነሳ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ምንም ጥቅም የለህም ። ምንጊዜም ቢሆን ዋጋ የለህም፡ መጥፎ አሚሚት ነው የምትሞተው ። አሁን እኔ ጥሩ ነገር የማደርግልህ ለፖሊስ ነው የማስረክብህ አለ ረዐፍ የዓይኖቹን ሽፋሽፍት ላይና ታች በማርገብገብና ከንፈሮቹን ሸብስጭት በመምጠጥ ።

“ምን ፈልገህ ነው የመጣኸው?” አለ ረዐፍ ፡ በንዴል ዓይኖቹን እንደገና በመጨፈን ። አንተኮ እንደ ጠላት ነው የምታየኝ ። የእኔን በጐ ሥራ ሁሉ ረስተሃል ። በምቀኝነትና በጥላቻ ብቻ ነው የምትኖረው ። እኔ ያንተን ሃሳብ ከማንበብም ሌላ እንቅስቃሴህን በትክክል አውቃለሁ”

“እኔ ራሴ ሠርቤኛል ፡ ከእሥር ቤት ከወጣሁበት ጊዜ ጀምሮ ሠርቤኛል” አለ ሰዒድ በለሰለሰ ድምፅ ዓይኖቹን ወደ መሬት በማቀርቀር ።

“በውሸት እኔን ለማታለል አትሞክር ። አንተ የምታስበው እኔ ድሮ ከምንቅፋቸው ከበርቴዎች ከነበሩ አንዱስለሆን ኩኝ ነው ። ለዚህም ነው ጨለማን ለብሰህ ልትሰርቀኝ የመጣኸው”

“ይህ ትክክል አይደለም”

“ታዲያ ምን ለማድረግ ነው ቤቱን ሰርስረህ የገባኸው? ለምንድን ነው እኔን ለመስረቅ የከጀልከው?”

“እኔ የማውቀው ነገር የለም ። እኔ ትክክል አይደለሁም። አንተ ግን አታምነኝም!” በማለት ሰዒድ እያመነታ መለሰለት ።

“እውነት ነው አላምንህም ። ውሸታም መሆንህንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ራስህ ታውቃለህ ። የእኔ ምክር አላረካህም ። በምቀኝነትና በትዕቢት ተነሳስተህ በዕብደት እንደ አመልህ ወደእኔ መጣህ። ምናለ የፈለከውን አድርግ ወደ ወህኒ ቤት እንደገና ትሄዳለህ ።”

ድርጊቱን ያመነ በመምሰል “ይቅርታ አድርግልኝ አዕምሮዬ ገና ከእሥር ቤት እንደወጣና ከዚያ በፊት አንደነበረ ነው ያለው” ሲል ሰዒድ ለመነው ።

“ምንም ዓይነት ይቅርታ አላደርግልህም ። በአዕምሮህ የሚገላላው ማንኛውም የተንኮል ሃሳብ ሁሉ ስለእኔ መሆኑን በትክክል አውቃለሁ ። ስለዚህም አሁን ለፖሊስ አስረክብሀለሁ ።”

“እባክህ ይህን አታድርግ ለዛሬ አለፈኝ”

“እባክህ እያልክ የምትለማመጠው እሥር ቤት አይገባህም ማለት ነው?”

“እረ ይገባኛል ግን እባክህ የዛሬን ተወኝ ፡ ለዛሬ ማረኝ?” ረዐፍም ትንሽ ካመነታ በኋላ “ሌላ ጊዜ ከዚህ ካየሁህ እንደ ትንኝ ድምጥማጥህን ነው የማጠፋው” ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ሰዒድ በፍጥነት ለመውጣት ሲዘጋጅ ረዐፍ “ቁም አለው ።” ቀጥሎም “የሰጠሁህን ገንዘብ መልስ” በማለት ጮኸበት ። ሰዒድ አመዱ ቡን አለ ። እጁን ወደኪሱ አስገብቶ ሁለት ባለ አምሳ ብር ኖት አውጥቶ ሰጠው። ረዐፍም ተቀበለና “ሌላ ጊዜ ከዚህ እንዳላይህ” አለው ።

ሰዒድ በመጣበት መንገድ ወደ ጥቁር አባይ መመለስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጀመረ ። ነፃ መውጣቱን ማመን አልቻለም ። ዳሩ ግን ነፃ መውጣቱ ከሽንፈት ጋር ስለሆነ ቅር አለው ። የጐህ እርጥብ አየር እየተነፈሰ "የቤቱን ሁኔታ በደንብ ሳላጠና ፡ በቅርፃ ቅርፆች ያሸበረቁ ክፍሎችን ፡ በሰም የሚያንፀባርቁ ወለሎችን በማየት ብቻ እንዴት ሰተት ብዬ ገባሁና ለመያዝም በቃሁ" እያለ ይገረም ጀመር ። ሀሳቡን ሰብሰብ አድርጐ የጐህ ጨዛ በተንሠራፋበት መስክ ላይ እየተዝናና ስላጠፋው ማንኛውም ነገር ሁሉ ከሁለት ባለ አምሳ ብር ኖት ጭምር ራሱን አፅናና ። ጭንቅላቱን ወደ ሰማይ ብድግ በማድረግ የከዋክብቶች መብለጭለጭ ገረመው ። "እንዴት በዚሁ ሰዓት ፀሐይ በምትወጣበት ሰዓት ከዋክብቶች ያብለጨልጫሉ?" ዞሮብ ኛል መሰል አለ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 5 —

ከቡና ቤቱ የነበሩ ሰዎች በሙሉ ዓይናቸውን አፍጥጠው ከተመለከቱ በኋላ በቡና ቤቱ ባለቤትና ቦዩ መሪነት ብድግ ብለው "እንኳን ደህና መጣህ" የሚል የደመቀና አስደሳች አቀባበል አደረጉለት ። በሙሉ ከበቡት ፡ ታቀፉት ፡ ጉንጮቹንም ሳሙት ። ሰዒድ ማህራን ከእያንዳንዱ ጋር የእጅ ሰላምታ ተለዋወጠ ።

"አመሰግናችኋለሁ መዓሲም ታርዛን አመሰግናለሁ ፡ ጓደኞቼ በሙሉ" አለ ።

"መቼ ነበር ከእሥር ቤት የወጣኸው?" አሉት ።

"ከትናንት በስቲያ"

"እኛም በበዓሉ ዕለት ምህረት ይደረጋል ብለን ገምተን ነበር"

"ይመስገነው እነሆ ለዚህ በቅቻለሁ"

"ስለ ሌሎች የእኛ ሰዎችስ ?"

"ደህና ናቸው ፡ ጊዜውን ጠብቀው ይወጣሉ"

ለጥቂት ጊዜ አንዳንድ መሪዎች ከተለዋወጡ በኋላ መዓሲም ታርዛን ሰዒድን ወደራሱ አማዳሚ ወንበር ወሰደው። ሌሎችም ሰዎች ወደየቦታቸው እንዲሄዱ ካደረገ በኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኖ በሌሎ እንደገና ወጥ አለ ። ምንም የተለወጠ ነገር የለም ። ልክ ትናንት እንደተወው መስሎ ታየው ። ክብ የሆነው ክፍል በነበሰ የተሠሩ መጣሪያዎች ፡ ከእንጨትና ከቀርከሃ የተሠሩ ወንበሮች ። አነስተኛ ቁጥር ካላቸው ደንበኞች ፡ ከነዚህም መካከል አንዳንዶቹን የሚያውቃቸው በተለያዩ ቦታዎች ተቀምጠው ሻይ ይጠጣሉ ። ሀጋዊ ያልሆኑ ንግዶችም ይካሄዳሉ። በተከፈተው በርና በትልቁ መስኮት ትይዩ በሆ ነው አንድ ሰፊ ክፍት ቦታ መጨረሻ የሌለው የሚመስል ይታያል።

ፈለሳማው ድቅድቅ ነበር ። ምንም ዓይነት ብርሃን መሳይ ነገር አያታይም ። አልፎ አልፎ ከሚሰማው ንፋስ ከወጭ ከሚያመጣው የሳቅ ድምፅ በስተቀር ወጥታው አስፈሪ ነበር ። በዚህ ጊዜ አርከ የሆነ ንፀህና ንጹለኛ የበረሃ አየር በመስኩቱ በኩል መግባት ሲጀምር ሰዒድ ከቦዩ አንድ ብርጭቆ ሻይ ተቀብሎ ሳይቀዘቅዝ መጠጣት ጀመረ ። ወደ መዓሊም ታርዛን በማዘንበል "ሥራ እንዴት ነው?" ብሎ ጠየቀ ።

"በአሁኑ ጊዜ በሥራቸው ብቁ የሆኑ ሰዎች ማግኘት አስቸጋሪ ነው" አለ ታርዛን የታችኛውን ከንፈሩን በብስጭት በማጣመም ።

"ምን ማለትህ ነው ብቁ የሆኑ ሰዎች ስትለኝ?" አለ ሰዒድ ።

"በጣም ስንፎች ናቸው ፡ የመንግሥት ሠራተኞች ነው የሚመስለ·ት"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ሰነፍ ሠራተኛ ከከሀዲ ይሻላል ። ሙዓሊም ታርዛን እኔኮ በከሀዲ ምክንያት ነው እሥር ቤት ልገባ የቻልኩት” አለ ሰዒድ በንዴት መልክ ።

“እውነትህን ነው ? አይደረግም ?”

ሰዒድ ዓይኖቹን ወደ ታርዛን በማዞር “እስካሁን ድረስ አልሰማህም ማለት ነው ?”

ታርዛን ጭንቅላቱን በአሉታ በሀዘን መልክ ካወዛወዘ በኋላ ሰዒድ ወደ ታርዛን ጆሮ ጠጋ ብሎ “አንድ ደህና ሽጉጥ ያስፈልገኛል” ሲል አንሾካሾከለት ።

“ሌላም የምትፈልገው ነገር ካለ እኔ ዝግጁ ነኝ” አለ ታርዛን ።

“አይ ምንም ! ይቅርታ ብቻ ...” አለ ሰዒድ ቀሪውን ሻዩን ጭልጥ አድርጎ ጠጣና ። ወደ መስኮቱ አመራ ። ትንሽ ቆም አለ ። ጠንካራና ቀጫጫ ቁመናው ያማረ ፣ መካከለኛ የሆነው ሰዒድ ከዋክብትን በጠራው ሰማይ ላይ ሲመለከት እንደ በረሃ አሸዋ መስለው ታዩት ። ቡና ቤቱም በውቅያኖስ መካከል ያለ ደሴት ወይም በሰማይ ብልጭ ብልጭ የሚል አውሮፕላን መስሎ ታየው ። በኮረብታው ግርጌ ከሚገኘው ቡና ቤት ውስጥ የተቀጣጠሉት ሲጋራዎች ልክ እንደከዋክብት ያበራሉ ። ወደ ምዕራብ በሚገኘው አድማስ በኩል የዓባሲያ ቀበሌ ብርሃን ከሩቅ ይታያል ። ርቀቱም የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ቡና ቤቱ ምን ያህል በራቀ ምድረ በዳ ላይ እንደሚገኝ ነው። ሰዒድ በመስኮቱ አሰተውሎ ሲመለከት በኮረብታው ዙሪያ ንዑሀ አየር ለማግኘትና ዕረፍት ለማድረግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ምድረ በዳ ከመጡ ሰዎች የሚመጣውን ድምፅ ሰማ ። ቦዩም ከጋራው ሥር ለሚዘናጉት ሰዎች በውሃና በእሳት ፍም የሚሠሩትን ጋያዎች ይዞ ሲሄድ የቡና ቤቱ ደንበኞች ፈጥኖ ደርሶ ነበር ። አልፎ አልፎም ሳቅ ይሰማል ። በዚህ ጊዜ የአንድ ሰጋ መጣት ድምፅ ይመስላል" አስኪ በዚህ ዓለም ወጥ የሰፈነበት አንድ ሥፍራ አሳዩኝ" አለ ።

አንድ ሌላ ሰው የተሰነዘረውን ጥያቄ ተቃወመ "ይህ እኛ ያለንበት ቦታ ወጥ አልሰፈነበትም ማለትህ ነው?

"ይህን እኛ የተሰበሰብንበትን ቦታ በአውኑ ጊዜ እንዲህ ትላለህ ? በጣም የሚያሳዝን ነው ?"

"በእውነቱ ከሆነ ስጋትንና ፍርሃትን ማውገዝ የለብንም እንዲያውም ጠቃሚ ነው ። ለመፈለው ጊዜ እንዳናስብ ያረዳናል አይደል?

ይህ ከሆነ ሀሳብህ አንተ ወረ ሰላምና ወጥ ነህ ማለት ነው የመስቀያ ገመድ በአንገትህ ዙርያ ከሆነ እርግጥ ነው ወጥን ልትፈራ ትችላለህ "

"ምድረ በዳንና ፈለማን ተገን በማድረግ እንደልባችሁ በደስታ ትመያየላችሁ ። ዳሩ ግን ወደ ከተማ መሄዳችሁ አይቀርም ። ምን ሊውጣችሁ ነው ከዚያ ስትሄዱ?" አለ ሰዒድ በሀሳቡ ። ሰዎቹም ውይይታቸውን ቀጠሉ ።

"እውነተኛው አሳዛኝ ነገር ግን ጠላታችን ሆኖ ወዳጃችን መስሎ የሚታይ ሰው ነው"

"በተቃራኒም የእኛ ወዳጅም ጠላታችን ሊሆን ይችላል"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኛ ፈሪዎች ነን ለምን በዚህ አናምንም ?"

"ሊሆን ይችላል ። ግን ጅግንነት እንዴት ሊኖረን ይችላል በአሁኑ ጊዜ?"

"ምን ጊዜም ቢሆን ጅግንነት ጅግንነት ነው"

"ሞትም ሞት ነው"

"ጨለማና ምድረ በዳ ደግሞ ሁሉንም ያጠቃልላሉ ?"

"ምን ዓይነት ሙይይት ነው ! ምን ማለታቸው ነው ?"

የሚገርመው ስለእኔ ሁኔታ የሚገልፁ ይመስላሉ ። እንደዚሁ እንደሣፊው የጨለማ ሚስጥር እኔም በሎጋኑቱ እንደዚህ ያሉ ሃሳቦችና ስሜቶች ነበሩኝ ። መጣሪያ የሚያዘው ለትግል ነው እንጂ ለግድያ አይደለም ። ከዚህ ኮረብታማ ቦታ በስተጀርባ በሚገኘው አሁን ቡና ቤት የተቋቋመበት ቦታ ወጣቶች ብቱቶ ልብሶች ለብሰው በንፁህ ሀሊናቸው ለትግል የሚረዳ ልምምድ ያደርጉ ነበር ። በ19 ቁጥር ቪላ የሚኖረ ውም ሰውዬ ከእነሱ አንዱና ዋናው ነበር ። ይሰለጥናል ፡ ያሰለጥናል ፡ ታላቅነትም ጥበብ የተሞላባቸው ነበሩ ። እንዲህ ይል ነበር ሰዒድ ማህራን "ሽጉጥ ከዳቦና አንተ አዘውትረህ ከአባትህ ጋር ከምትመላለስበት የሼክ ተክታዮች ውዝዋዜ የበለጠ ነው" ካለ በኋላ በዚህ ሀገር ለአንድ ሰው ምን የሚያስፈልገው ይመስልሃል ?" እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ ። አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ። "ሽጉጥ ያስፈልገሞል ፡ እንዲሁም መፅሀፍ ። ሽጉጡ ያለፈውን ሂሳብ ለማጣራት ሲረዳ መፅሀፉ ደግሞ የወደፊቱን ፅድል የሚወስንበት ነው ። ስለዚህ አንተ መሰልጠንና ማንበብ አለብህ" አለ ጥያቄውን መልስ ሳይጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብቅ ራሱ መልሱን በመስጠት ። ከዕለታት አንድ ቀን ደግሞ በስርቆት ተይዞ እንዲህ አለኝ "ብራዮ! አንተ በመስረቅህ ከበዝባዦች ትንሽ ከንጠአታቸው ይቀንስላቸዋል ሀጋዊ ነው አትጠራጠር" ይህንንም የተናገረው በተማሪዎች ሆስቴል አንድ ምሽት ነው ። ፊቱን ፈካ አድርጎ ሳቁን እያስተጋባ ነበር ። ይህ ምድረ በዳ ሰሰዲድ ጉብዝናና ብልሃት ምስክር ነው አልተባልክም ወይ ? አንተ ራስህ ሞት ነህ ። ተኩሰህ አትስትም አልተባልክም ወይ ? አለ በሀሳቡ ። ዓይኖቹን ጨፈነ፡ ተዝናና ፡ በንፁህ አየር መደሰት ጀመረ ። በዚህ ሁኔታ እያለ በድንገት ሰው ትከሻውን እንደነካው ተሰማው ። ታርዛንን አስተውሎ አየ ። ታርዛንም ሽጉጥ በሌላ እጁ ይዞለት ሲሰጠው ሲል "በእግዚአብሔር ፈቃድ ለጠላትህ እሳት እንዲሆን እመኛለሁ" ብሎ ሰጠው ።

ሰዲድ ሽጉጡን ተረከበ "ስንት ነው ዋጋው መዓሊም ታርዛን ?" አለ ሽጉጡን እየፈተሸ ።

"የኔ ስጦታ ነው"

"አይ አመሰግናለሁ ። ግን ይህን አልቀበልም ። እኔ የምፈልገው ለአከፋፈሉ ጊዜ እንዲሰጠኝ ነው ። አሁን ለመክፈል ስለማልችል ብቻ ነው"

"ምን ያህል ጥይቶች ያስፈልጉሀል?" ብሎ ከጠየቀው በኋላ ወደ አግዳሚው ወንበር አመሩ ። በተከፈተው በር ሲያልፉም የሴት ሳቅ ሰሙ ። "ኑር ኑች እኮ አታስታውሳትም?" አለ ታርዛን ፊቱን ፈካ አድርጎ ። "ኑር" አለ በዓይኖቹ ከበፉ ውጭ ያለውን ጨለማ አተኩሮ እያመለከተ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ወደዚህ መምጣቷን እንደቀጠለች ናት እንዴ?” አለ ሰዒድ ዓይኖቹን አፍጥጦ ከበሩ ውጭ ያለውን ጨለማ እያስተዋለ ለማየት ግን አልቻለም ።

“አልፎ አልፎ ትመጣለች አውን አንተን ስታይ በጣም ነው ደስ የሚላት” አለ ታርዛን ።

“ጠብሳለች ?” አለ ሰዒድ ።

“አም የጣፋጭ ምግቦች ፋብሪካ ባለቤት ልጄን?”

ከአግዳሚ ወንበር አንደተቀመጠ ታርዛን ዐይን ጠራ “ኑርን በዘዴ ጥራት” አለው ። መልካም አጋጣሚ ነው ። እሷን ለማየት መቻል ጊዜ ምን ዓይነት ለውጥ እንዳደረገባት ለማወቅ ኑር የሱን ልብ ለማማኘት ብዙ ጥረት አድርጋ ነበር ። ልቡ በዚያን ጊዜ የዚያች እምነቱ ቢስ ንብረት ነበር ። ድንጋይ ነበር ለማለት ያስቸላል ። እንደዚህ ያለውን ሰው ማፍቀር እንዴት ስታይ ነበር ። እሷ የምትሰጠውን ስጦታም ሳይቀር ለነበዊያ ነው አሳልፎ ያሰጣት የነበረው ። በኪሱ ውስጥ ያለውን ሽጉጡን ነካ ነካ አደረገ ። ጥርሶቹን ነከሰ ። ኑር በበሩ ብቅ አለች ። ለእንደዚህ ያለ አስገራሚ ነገር አልተዘጋጀችም ነበር ። ከሰዒድ ትንሽ ራቅ ብላ ቆመች ። እሱ ፈገግ አለ። ግን ቀረብ ብላ ተመለከተችው : ትንሽ ከስታለች። ፊቷ በቅባትና በፓውደር ተለቅልቋል ። ነጭ ስስ ልብስ ለብሳ ለች። ሰውነቷ በግልፅ ይታያል ። ከሰውነቷ ጋር እንደላስቲክ ተጣብቋል ። ክብር የሚለው ቃል ከዚህ ምንም ቦታ የለውም። ወጉም አጠር ብሎ በአየሩ እየተወዛወዘ ወደ እሱ ተጠጋች።

“ምስጋና ለአምላክ ይድረሰው ነፃ ወጣህ” አለች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሁለቱም እጆች ለመጨባበጥ እየከጀሉ እሷም ትንሽ ስሚ ቷን ለመደበቅ እየሞከረች ። ከሁለቱ መካከል ገባች ።

"ኑር እንደምን አለሽ?" አለ ሰዒድ በፈገግታ ።

"አታያትም እንዴ ታበራለች ልክ እንደስሚ !" አለ ታርዛን ፈካ ባለ ፊቱ ።

"እኔ በጣም ደህና ነኝ አንተስ ?" ጨናህ ጥሩ ይመስላል ዓይኖችህ ግን የተቆጡ ይመስላሉ !"

"እንዴት?" አለ በፈገግታ ።

"እኔ ምንም አላውቅም ምን ልበል ዓይኖችህ ቀልተዋል። ከንፈሮችህ ማስጠንቀቂያ የሚያስተላልፉ ይመ ስላሉ" አለች ።

"ጓደኛ ይዘሻል ? አንቺን ለመውሰድ ይመጣል ?" አለ ሳቅ ብሎ በሀዘን መልክ ።

"አምን ግን እሱ ማንነቱን አያውቅም : እልም ብሎ ሰክሯል አለች ጭንቅላቷን በማወዛወዝ ወደ ዓይኖቿ በኩል የወደቀውን ፀጉር በእጇ እያነሳች ።

"ያም ሆነ ይህ ከእሱ ጋር ቀጠሮ አለሽ ማለት ነው?"

"ታፈቅረኛለህ እንዴ?" አለች ትንሽ ፈገግ በማለት ።

"ዝማጅ ነኝ ከዚህ አሸዋ ልንቀብረው ።"

"ስለሱ ምንም ደንታ የለኝም" አለች ።

"አይ ዛሬ ማታ አይደለም ። በሌላ ጊዜ ነው ።"

"እሱ ከበርቱ ነገር ነው የሚል ወሬ ሰምቻለሁ" አለ ።

"አምን በእሱ መኪና ወደ ሰማዕታት መቃብር እንሄዳ ለን ። እሱ ጭር ያለ ክፍት ቦታ ነው የሚወደው !"

t.me/OLDBOOKSPDF

“ጭር ያለ ክፍት ቦታ ነው የሚወደው የሰማዕታት መታሰቢያ ?” አለ ሰዒድ ስለ ጉዳዩ ደህና አድርጎ እያሰበ ራሱን በራሱ እንደሚነግር ሰው ።

የዓይኖቿ ሽፋሽፍቶች ተርበተበቱ ። ግራ እንደገባው ሰው በተለይ የሁለቱ ዓይኖች ሲገናኙ “አየህ አንተ ስለ እኔ ምንም እንደማታስብ” ስትል ጠየቀችው ።

“እውነት አይደለም ። አንቺን በጣም አድርጌ ነው የማፈቅርሽ”

“አንተ የምታስበው ስለ ከበርቱው ሰውዬ ብቻ ነው!”

“ከአንቺ ጋር አጣምሬ ነው የማስበው” አለ ፈገግ በማለት ።

“ሁኔታው ከታወቀ እኔ የለሁም ማለት ነው ። አባቱ ከፍተኛ ተሰዶ ማድረግ የሚችሉ ከበርቴ ሰው ናቸው ። ዘመዶቼም እንደ ጉንዳን ናቸው ። ለመሆኑ ገንዘብ ነው የሚያስፈልግህ?” በድንገት ስጋት በተሞላበት አገላለፅ ያቀረ በችለት ጥያቄ ነበር ።

“በይበልጥ መኪና ለማግኘት ነው የምፈልገው” አለ ቆም እያለ ።

“ባህሪሽን ላለመለወጥ ሞክሪ ። ከእሱ ጋር እንደወት ሮሽ ሁኚ” ብሎ በፍቅር ጉንጯን ቆንጠጥ አደረጋት ።

“ምንም የሚያስፈራ ነገር ሊደርስ አይችልም ። ማንም የሚጠረጥረሽ የለም ። እኔ ሀሳን እየደለሁም ። ከዚያ በኋላ ከምታስበው በላይ ልንገናኝ እንችላለን ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 6 —

ሰዓድ ቦታውን በደንብ አድርጐ ስለሚያውቀው ወደ ወታደሮች ሠፈር የሚወስደውን መንገድ ወደ ጐን በመተው ምድረ በዳውን በማቋረጥ ወደ ሰማዕታት መቃብር በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመድረስ ወደ እዚያው አመራ ። ወደ ሰማዕታት መቃብር ሲገሰግስ ለተመለከተው ልክ ከጭንቅላቱ ላይ ወደግቡ የሚያደርስ አቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ የተተከለበት ይመስል ነበር ። ወደ መቃብሩ ቦታ መድረሱን ያወቀው በዚያ ያለውን ታላቅ ጉልላት ከሩቅ በመመልከቱ ነው በከዋክብት ብርሃን አማካይነት መኪናዋ የት ቦታ እንደቆመች ይፈልግ ጀመር ። መቃብሩን እየዞረ መፈለጉን በመቀጠል ወደ መቃብሩ ደቡባዊ ክፍል ሲደርስ መኪና የሚመስል ነገር ከሩቅ አየ ። ወደዚያው አመራ ። በቅዕበት ጐንበስ ብሎ ጭንቅላቱን እስከ ጉልበቱ ድረስ አደረሰ ። ጀሮዎቹ ጥልቅ የሆኑ ሚስጥራዊ ሹክሹክታዎች መስማት ጀመሩ ። "አስደን ጋጭ ነገር ሊፈጠር ይችላል ። ደስታም በቅዕበት ሊቋረጥ ይችላል ። ግን የኔ ጥፋት አይደለም ። የስነ ስርዓት መጥደልና መርበትበት ሊፈጠር ይችላል" አለ በሆዱ።

"ምኞታችን ምንም እንኳ ጥሩ ቢሆንም ስነ ስርዓት ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

ይ፦ድለናል” የሚለው የረዐፍ ጥቅስ በሀሳቡ መጣ ።

የመኪናውን በር በእጁ ያዝ አደረገ ። ከመኪናዋ ውስጥ የሚወጣ ትንፋሽ ፊቱን ገረፈው ። እጅታውን በኃይል ያዘው። በሩን ብርግድ አድርጎ ከፈተ ።

“እንዳትንቀሳቀስ !” ብሎ አስጠነቀቀ ።

ሁለት ሰዎች በድንጋጤ ፈዘዙ ። ሁለት ጭንቅላቶች ችም በድንጋጤ ሲመለከቱ ታዩት ። ሽጉጡን እንደ ማዕበል በማወለብለብ” እንዳትንቀሳቀሱ ። አለበለዚያ እተኩሳለሁ ፡ ዉጡ !” አለ ።

“እለምንሃለሁ ፡ እባክህ ማረኝ” የሚል የኑር ድምፅ ተሰማ ። ሌላው ደግሞ ማንቁርቱ የታነቀ የሚመስል ድምፅ “ምንድን ነው ... ምንድን ነው የምትፈልገው እባክህን ?” አለ ።

“ወጣ ነው የምልህ!”

ኑር ከመኪናው ዘሳ ወረደች ። ልብሶቿን በአንድ እጁ ሰብስባ ይዛ ቀጥሎም ወጣቱ እግሮቹን በሱሪው ውስጥ ለማጥለቅ እየታገለ ወጣ ። ሰዒድ ሽጉጡን በወጣቱ ጭንቅላት ላይ ደገነው ።

“እባክህ አትተኩስብኝ” ሲል ለመነው ።

“ሰዒድም በሚያስፈራ ድምፅ “ገንዘብ !” ብሎ አፈጠጠበት ።

“ኪቱ ከመኪናዋ ውስጥ ነው ያለው” አለ ወጣቱ በመርበትበት ።

“አንቺ ወደ መኪናው ግቢ” አለ ሰዒድ ኑርን በመግፋት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኑርም በማልቀስ መልክ "እባክህን ተወኝ ፡ ነፍሴን አትርፍልኝ፡ በእግዚአብሄር ይሁንብህ?" ስትል ተማጠነችው ።

ጃኬቱን አምፈሊ "አሰ ሰዒድ ። ሰጠችው ። ተቀብሎ የገንዘብ መያዣውን ቦርሳ አውጥቶ ጃኬቱን ከወጣቱ ፊት ላይ ወረወረውና "ህይወትህን ለማዳን ከፈለግህ አንድ ደቂቃ ብቻ ነው ያለህ!" አለው ። ወጣቱም እንደ ተወርዋሪ ኮከብ በዚያ በጨለማ እግሬ አውጪኝ ብሎ ተፈተለከ ። ሰዒድም በፍጥነት ወደ መኪናዋ ውስጥ ገባ ። ኑር ልብሶቿን ለበሰችና "በእውነቱ ከሆነ ፈርቼ ነበር ልክ አንዳልጠበኩህ ሆኖ ተሰማኝ!" ስትል ፍርሀቷን ገለፀችለት ።

መኪናዋ እየከነፈች ሄደች ። "መጠጥ እንጠጣ" አለ ሰዒድ ። አንድ ጠርሙስ ሰጠችው ። አንድ ጊዜ ጠጣና ለሷም መልሶ ሰጣት ። እሷም እንደሱ ጠጣች ። "አሳዛኝ ወጣት ነው፡ በጣም ነው የተበረከረከው" አለች ኑር ።

"አንቺ ገር ልብ ነው ያለሽ ። እኔ በበኩሌ ባለ አንዱስትሪዎችንና ከበርቴዎችን አልወዳቸውም" አለ ሰዒድ።

"አንተ ማንን ትወዳለህ ይህ ሀቅ ነው" አለች ኑር አቀማመጧን እያስተካከለች ። እሷን በፍቅር ለማባበል ፍላጐት ስላልነበረው መልስ ለመስጠት አልፈለገም ። መኪናዋ ወደ አባሲያ ቀበሌ ማምራቷን ስታውቅ ኑር "ከአንተ ጋር ያዩኛል እባክህ ?" እያለች ለመነችው እሱም ስለዚህ ነገር ያስብ ስለነበረ ወደ ደራሳ ወደሚወስደው

t.me/OLDBOOKSPDF

ተግንጣይ መንገድ መኪናዋን ጠምዝዞ ፍጥነት በመቀነስ እንዲህ አለ ።

"ወደ ታርዛን ቡና ቤት ሽጉጥ ፍለጋ ሄጄ ነበር ። ከተቻለም ከአንድ ድሮ ከማውቀው ጓደኛዬ ታክሲ ነጂ ጋር ለመዋዋል ነበር ግን ዕድሌ ይህችን የመሰለች መኪና አስገኘልኝ"

"እኔ ምን ጊዜም ቢሆን ጠቃሚ መሆኔን አታውቅም?" በማለት ኑር ጠየቀችው።

"በዕውነቱ ምንጊዜም ጠቃሚ ነሽ ፡ ለምን ቲያትር ቤት አትሠሪም?" በማለት ሰዒድ መለሰላት ።

"በዕውነቱ ከሆነ መጀመሪያ ጊዜ ፈርቼ ነበር" አለችው ።

"በኋላስ?"

"እኔ ተስፋ የማደርገው በሚገባ ድርሻዬን እንደተወጣሁኝና ወጣቱም እንደማይጠረጥረኝ ነው"

"እሱኮ ከፍርሃት ብዛት ከቁጥር ውጭ ስለነበር ማንንም ለመጠርጠር የሚችል አይመስለኝም" አለ ።

"ለመሆኑ ለምንድነው ሽጉጥና መኪና ያስፈለገህ ?" ጭንቅላቷን ወደ እሱ ቀረብ በማድረግ ጠየቀችው ።

"የሥራዬ መሣሪያዎች ናቸው"

"ወይ ጉድ ለመሆኑ መቼ ነው ከእሥር ቤት የወጣኸው?"

"ከትናንት በስቲያ"

"ታዲያ አሁን ወደዚያ ለመመለስ ነው የምታስበው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞያሽን በቀላሉ ለመቀየር ትችያለሽ ?"

ምንም መልስ ሳትሰጥ ወደ ጨለማው መንገድ የመኪና መብራቶች ብቻ ወደሚታዩበት አመራ ። ወደ መጠለያው ሲደርስ የመቀጠም ኮረብታ የሌሊቱ ቁራጭ መስሎ በቅርብ ይታይ ጀመረ ። ኑርም በፍቅር እንዲህ አለች ። "ታውቃለህ ምን ያህል እንዳዘንኩ አንተ በመታሠርህ?"

"ምን ያህል?" አለ ሰዒድ ።

"መቼ ነው ማሸፍህን የምታቆመው ?" አለች ኑር በቁጣ መልክ ።

"ከምሬ ነው ፡ እርግጠኛ ነኝ ከልብሽ እንደሆነ"

"አንተማ ልብም የለህ" አለች ኑር ።

"ልቤ ከእሥር ቤቱ ነው ተይዞ የቀረው"

"ከእሥር ቤት ከመግባትህም በፊት ልብ የሚሉት ነገር አልነበረህም"

"ለምንድነው ስለ ልብ ይህን ያህል አጠንክረን የምናወራው ? ለማወቅ ከፈለግሽ ከሀዲቷን ፡ ውሾቹንና አባቷን የካደችውን ልጅም ጠይቂ ። አንድ ቀን ልብ እናገኝ ይሆናል" አለ ሰዒድ ።

"ዛሬ ሌሊት የት ነው የምታድረው?" የት እንዳለህ ባለቤትህ ታውቃለች ?

"አይመስለኝም"

"አሁን ወደቤትህ ነው የምትሄደው?" ስትል ደግማ ጠየቀችው ኑር ።

"አይመስለኝም ። ቢሆንም ዛሬ ሌሊት አይደለም"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ወደ እኔ ቤት እንሂዳ !" አለችው በልመና መልክ ።

"ለብቻሽ ነው የምትኖሪው?"

"አምን ከነጀመዲን ጐዳና ከመቃብር ቦታና ከጅንያ ልብስ መጋዘን (ሰልባጅ) ከዚያው በስተጀርባ ነው ።

"እንዴት ያለ ስትራቴጂክ የሆነ ቤት ነው !" አለ ሰዒድ እንደመሳቅ እያለ ። ኑርም እየሳቀች ማንም ሰው አያውቀኝም ። ማንም ሰው አይገበኘኝም ። የኔ ክፍልም በፎቁ መጨረሻ ነው ። አንተም ከመጣህ ወደእኔ ክፍል የሚገባ የመጀመሪያው ሰው ትሆናለህ ።

መንገዱን ወደ ሸኸ ዓሊ ቤት ቀጠለ ። መኪናዋን ግን በደራስ ቀበሌ መግቢያ በኩል አቁሞ ወደ ኑር ዞር ብሎ "ከዚህ ቦታ ብትወርጂ ለአንቺ ተስማሚ ነው" አላት ።

"ከእኔ ጋር አትመጣም እንዴ ?

"ትንሽ ቆይቼ እመጣለሁ"

"አሁን በዚህ ውድቅት የት ነው የምትሄደው ?"

"አንቺ ማድረግ ያለብሽ አሁኑኑ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደሽ ያጋጠመሽን በሙሉ ከእኔ ጋር ሚስጥር እንደሌለሽ አድርገሽ ስለኔም ማንነት ከእኔ ፊዕሞ የራቀ ነገር ፈጥረሽ ንገሪያቸው ፡ ለምሳሌ ነጭ ፡ ወፍራም ፡ በቀኝ ጉንጩ በኩል የቆየ ጠባሳ ምልክት ያለበት ሰው አስመስለሽ ግለጪላቸው ። እኔ እንደጠለፍኩሽ ፡ እንደሰረቅሁሽ ፡ ክብረ ንፅህናሽንም እንደደፈርኩሽ አድርገሽ ንገሪያቸው"

"ክብረ ንፅህናዬን ደፈርክ ?" ስትል ኑር በአንክሮ ጠየቀች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ወደ እኔ ቤት እንሂዳ !” አለችው በልመና መልክ ።

“ለብቻሽ ነው የምትኖሪው?”

“አምን ከነጀመዲን ጉዳና ከመቃብር ቦታና ከጅንያ ልብስ መጋዘን (ሰልባጅ) ከዚያው በስተጀርባ ነው ።

“እንዴት ያለ ስትራቴጂክ የሆነ ቤት ነው !“ አለ ሰዒድ እንደመሳቅ እያለ ። ኑርም እየሳቀች ማንም ሰው አያውቀኝም ። ማንም ሰው አይጎበኘኝም ። የኔ ክፍልም በሮቱ መጨረሻ ነው ። አንተም ከመጣህ ወደእኔ ክፍል የሚገባ የመጀመሪያው ሰው ትሆናለህ ።

መንገዱን ወደ ሸኸ ዓሊ ቤት ቀጠለ ። መኪናዋን ግን በደራስ ቀበሌ መግቢያ በኩል አቁሞ ወደ ኑር ዞር ብሎ “ከዚህ ቦታ ብትወርጂ ለአንቺ ተስማሚ ነው” አላት ።

“ከእኔ ጋር አትመጣም እንዴ ?

“ትንሽ ቆይቼ እመጣለሁ”

“አሁን በዚህ ውድቅት የት ነው የምትሄደው ?”

“አንቺ ማድረግ ያለብሽ አሁኑኑ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደሽ ያጋጠመሽን በሙሉ ከእኔ ጋር ሚስጥር እንደሌለሽ አድርገሽ ስለኔም ማንነት ከእኔ ፊዕሞ የራቀ ነገር ፈጥረሽ ንገሪያቸው ፡ ለምሳሌ ነጭ ፡ ወፍራም ፡ በቀኝ ጉንጩ በኩል የቆየ ጠባሳ ምልክት ያለበት ሰው አስመስለሽ ግለጪላቸው ። እኔ እንደጠለፍኩሽ ፡ እንደሰረቅሁሽ ፡ ከብረ ንፅህናሽንም እንደደፈርኩሽ አድርገሽ ንገሪያቸው”

“ከብረ ንፅህናዬን ደፈርክ ?” ስትል ኑር በእንክሮ ጠየቀች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለእሷ ጥያቄ መልስ ሳይሰጥ ኮስተር በማለት "ይህም የተፈፀመው በዚህኑም ምድረ በዳ እንደሆነ ፡ እኒም ከመኪናው ወርውሬ ወደ ውጭ እንደጠልኩሽና በያዝኩት መኪና እንደፈረጠጥኩ ንገሪያቸው" አለ ሰዒድ ።

"እርግጠኛ ነህ ወደ እኔ ትመጣለህ ?"

"ቃል እገባልሻለሁ ። ከመኪና ውስጥ ጥሩ ቲያትር እንደሠራሽ በፖሊስ ጣቢያም ከዚያ የበለጠ ጥሩ ቲያትር እንደምትሠሪ እተማመናለሁ ።"

"ተስፋ አደርጋለሁ" አለች ።

"ይህና ሁኚ ኑርዬ" ብሎ በመኪናው በረረ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 7 —

“ነበዊያና ዓለ.ሽን በአንድ ጊዜ መማደል ድልን መጐና ፀፍ ማለት ነው ። ረዐፍንም ማስወገድ ከሱ ጋር ያለውን ሂሳብ ማጣራት አስፈላጊ ነው ። ከዚያ በኋላ መሸሽ ከተቻለም ወደ ውጭ አገር መሄድ ነው ። ግን ለሰናእ ማን ይቀርላታል ? ከጉሮሮ የተሰካች አጥንት ።” አለ ሰዒድ በጠላቶቹ ላይ ጥቃት ሲያስብ የአንድ ልጁ ነገር አስጨንቆት ።

“አንተ ሁልጊዜ በችኮላና በስሜት ነው የምትሠራው ። አሁን ግን ከመቸኮልህ በፊት በፍጥነት አስፈላጊ ነገሮችን አዘጋጅተህ ጊዜ ሳትወስድ እንደ ንስር ማጥቃት አለብህ ። ከወህኒ ቤት ከወጣህበት ቀን ጀምሮ እየተከታተለህ ነው ። የመኪናዋም ጉዳይ ክትትሉን አጠናክሮበሃል ። የፋብሪካ ውም ባለቤት ልጅ ቦርሳም በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ብሮች ብቻ ነው የያዘች ። መጥፎ ዕድል ነው ። ቶሎ ብለህ ማጥቃት ካልጀመርክ ሁሉም ነገር ሊበላሽብህ ነው ። ግን ሰናእን ማን ይንከባከባታል ? ከጉሮሮ የተሰካች አጥንት ። ምንም እንኳ አባትነቱን ብትክድም በጣም ነው የምወዳት ። ያቺ ከሃዲ እናትሽን ላንቺ ስል ልተውልሽ ? አሁኑኑ መልስ እፈልጋለሁ።” አለ ሰዒድ በሆዱ ።

በእግሩ በዚያ ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ የጠላቱን ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመፈለግ ሶስት ጠባብ የሰፈር መንገዶች በሚገናኙበት አልኢማም እየተባለ በሚጠራው መንገድ ማንጃበብ ጀመረ። መኪናዋንም ቀልዓ በሚወስደው በመንገዱ መጨረሻ ጠርዝ ላይ ጥግ አስይዞ አቁሚታል ። ሱቆቹ በሙሉ ተዘግተዋል ። በመንገዱም ዝር የሚል ሰው አይታይም ። በዚህ ሰዓት ማንም ይመጣል ብሎ እሱን የሚጠብቅ ሊኖር አይችልም ።ሁሉም በየቦታው ገብቷል ። የፈለገው ቢሆን ዓላማውን ለመፈፀም የሚገታው ነገር አይኖርም ። ሰናእም ያለ አሳዳጊ ዕድሜ ልኳን ብትኖርም የተፈፀመብኝ ክህደት ይቅርታ የማይደረግለት በጣም አስከፊ ነገር ስለሆነ መበቀል አለብኝ ። አይደለም እንዴ መምህር ረዑፍ?" አለ ሰዒድ በሆዱ ።

ሽጉጡን በኪሱ ውስጥ በእጁ ጨብጦ የጠላቱን ቤት መስኮቶች ተመለከተ ። በበሩ በኩል ወዳለው ግድግዳ ጠጋ ብሎ "ክህደት አስከፊ ነገር ነው ዓሊሽ ! ህይወት ለነዋሪዎች ጣፋጭ እንድትሆን አደፍራሽ ወንጀለኞችን ከሥር መሠረታቸው ማጥፋት አስፈላጊ ነው" እያለ ሲያሰላስል ወደ ቤቱ አምርቶ ድቅድቅ ባለው ጨለማ ደረጃዎችን በከፍተኛ ጥንቃቄ ከአንደኛ ፎቅ ፡ አልፎ ወደ ሁለተኛ ፎቅ ደረሰ ። የዓሊሽን ክፍል በእጁ እየጠቆመ "በዚህ በተዘጋው በር ውስጥ የመጨረሻ የበሰበሰ ፍትወቱ ስጋ እየተካሄደበት ነው" በማለት በአዕምሮው ካወጣና ካወረደ በኋላ "አሁን በሩን ሳንኳኳ ማን ይከፍት ይሆን ? ነበዊያ ትከፍት ይሆን ? ነጭ ለባሹም ከአንድ ቦታ ተደብቆ ይሆን ? መዝጊያ ሰብሮ መግባት!" ካለ በኋላ በሆዱ" ብዙ ጊዜ ሸሽተህ በሰላም እንደወጣህ ዛሬም ታመልጣለህ ። አንተኮ አንድን ፎቅ በሴኮንዶች ውስጥ የምትወጣ ነህ ። ከሶስተኛ ፎቅም ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሬት በሰላም ዘለህ የምትወርድ ጀግና ነህ ። ሲያሻህም ትከንፋለህ" ብሎ ካሰበ በኋላ "በአሁኑ ሰዓት በሩን ማንኳኳት ምንም እንኳ አስፈላጊ ቢሆንም ጥርጣሬ ሊፈጥር ይችላል ። ነበዊያ ጨቨቷን ታቀልጠዋለች ። እነዚያ እርኩሶችም ይመጣሉ ። ነጭ ለባሹም ይመጣል ። ስለዚህ የሚሻለው የበሩን መስተዋት መስበር ነው ።" ይህም ሀሳብ የመጣላት መጀመሪያ በመኪና ውስጥ እንዳለ ነበር ። አሁንም ከዚህ የተሻለ ዘዴ ያለ አልመሰለውም ። የሽጉጡን አፈሙዝ ወደ እሱ አድርጎ በሽጉጡ ሰደፍ የበሩን መስተዋት ሰበረው ። ስብርባሪውም ተፈናጠረ ። ማንቁርቱን እንደታነቀ ሰው የሚመስል ድምፅ ተሰማ ። ከበሩ በጣም ተጠግቶ የልቡ ትርታ በፍጥነት እየመታ ይጠባበቅ ጀመር ። ዓይኖቹ አፍጥጠው ጥቅጥቅ ባለው ጨለማ እያዩ ሽጉጡንም በተሰበረው የበሩ ቀዳዳ ወደ ውስጥ አግብቶ ደገነው ። የሰው ድምፅ ሰማ ። ምንም እንኳን የአእምሮ መረበሽ ቢደርስበትም የዓሊ ሽ ድምፅ መሆኑን አረጋገጠ ።

ሰውዬውም "ማነህ ? ምንድን ነው?" አለ ።

በስተግራ በኩል ያለ በር ተከፈተ ። ደብዘዝ ያለ ብርሃን ታየ ።

በዚህ ጊዜ ጋኔን የመሰለ ሰው በዝግታ ሲመጣ ሰዓድ የሽጉጡን ቃታ ሳበውና ድምፁ ልክ በውድቅት ሌሊት እንደሚሰማው የሰይጣን ድምፅ መሰለ ። ሰውዬውም ጩኸቱን በመልቀቅ ለመውደቅ ተግተረተረ ። ወደ መሬት ሳይደርስም በሁለተኛው ጥይት ተመታ ። ይህ ነው የማይባል የሲት የእርዱን እሪታ ድምፅ የነበዊያ መሆኑን አረጋገጠ ። እሱም "ቆይ! ያንቺ ተራም ደርሷል ከእኔ አታመልጭም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰይጣን ማለት እኮ እኔ ነኝ ።" አለና ፊቱን አዙሮ የፎቁን ደረጃዎች አላንዳች ጥንቃቄ ሸሽቶ እየዘለለ በሴኮንዶች ወደፎቁ መጨረሻ በሰላም ደረሰ ።

ትንሽ ቆም ብሎ ካዳመጠ በኋላ በዋናው በር ወጥቶ በእርጋታ መሄድ ጀመረ ። ከዚያም ብዙ መስኮቶች ሲከፈቱ ሰማ ። ሰዎችም በየአቅጣጫው በመጠያየቅ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይጥራሉ ። እሱም መኪናዋ ወደቆመችበት ወደ መንገዱ መጨረሻ አመራና የመኪናዋን በር ከፍቶ ገባ ። ፖሊስም ከቀልጣ አደባባይ እየሮጠ ሲመጣ ተመለከተ ። ከመኪናዋ ወለል ውስጥ ሰጥ አለ ። ፖሊሱም ጩኸት ወደተሰማበት አቅጣጫ ሩጫውን ቀጠለ ። ሰዓድም የፖሊሱ ኮቴ እየራቀ መሄዱን ካረጋገጠ በኋላ መኪናዋን አስነስቶ በፍጥነት በረረ ። አደባባዩንም በደንቡ መሰረት ፍጥነቱን ሳይጨምር ሠረው ። ጩኸቱ ግን ስሜቱን በሙሉ ረበሸው ። ሰውነቱ በቅዕበት ዛለ ።

መኪናዋንም እንደ እብድ ሰው ያለ ቁጥጥር ነዳት ። "ነፍሰ ገዳይ ! ነፍሰ ገዳይ ! ። ከገዳዮቹ አንዱ ሆነሃል ይህም ለአንተ አዲስ ነገር ነው ። ብርቅ ዕቃዎችን ከመስረቅ ወደ የእርኩስ ሰዎችን ህይወት ማጥፋት ተሸጋግረሃል ።" ካለ በኋላ በሆዱ "አንቺም ጊዜሽን ጠብቂ ከእኔ አታመልጭም ። ሰይጣን ማለት እኮ እኔ ነኝ ። ምስጋና ለሰናእ ይድረስ ህይወት ሰጥቼሻለሁ ግን ከሞት በባሰ ቅጣት ነው ያለሽው ። ዛሬ ነገ እኔም መሞቱ ነው እያልሽ ስትባንኚ ዕድሜ ልክሽን ትኖሪያለሽ ። እኔ በህይወት እያለሁ አንድ ቀን ሊደላሽ አይችልም" እያለ ከአዕምሮው ጋር ሲሟገት መኪናዋም ወደ ሙሐመድ አሊ ጐዳና አመራች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የትና ለምን እንደሚሄድ ግን ፈፅሞ አላወቀም ። በአሁኑ ጊዜ ነፍሰ ገዳይ የሚለው ቃል ብዙ ሰዎች እየደጋ ገሙ የሚመላለሱት ቃልሆነበት ። "ስለዚህ ገዳይ ከሆንክ በተቻለ መጠን መደበቅ አለብህ ። ከስቅላት መራቅ አለብህ። ስቅላቱን የሚፈፅመውም ሰው ለመጨረሻ ጊዜ ምን እንዲደረ ግልህ ነው የምትፈልገው ? ብሎ ይጠይቅሀል ። እረ ምን አለበት መንግሥት ይህን ጥያቄ ለጥሩ ነገር ቢያውለው ?" ካለ በኋላ ራሱን በደንብ መቆጣጠር ጀመረ።

የወታደሮችን ጭፈና አልፎ ወደ አባሲያ እያመራ መሆኑን አወቀ ። በጣም እድርጎ ደነገጠ ። ወደዚህ የወታደ ሮች ካምፕ ወደሚገኝበት አስጊ ቦታ እንደገና በመጣቱ ጥያኔቱን ጨምሮ በጥቂት ደቂቃዎች ከዚያ አካባቢ ወጣ ። ከመጀመሪያው ከዋናው መንገድ መገንጠያ ላይ መኪናውን አቁሞ በእርጋታ ወደቀኝና ወደ ግራ ሳያመለክት ልክ ስፖርት እንደሚሠራ ሰው ወደፊት እየተንጐራደደ ሄደ ። ሰውነቱ ዛለ፡ ሀሞም ተሰማው ። ምናልባት አእምሮው ከባድ ጭንቀ ትና ውጥረት ስለደረሰበት ሳይሆን አይቀርም ። "ለአንተ የሚሆን መጠለያ በአሁኑ ሰዓት የት ይገኛል?... ኑርስ ? በዛሬ ለሊት ወደ ኑር ቤት መሄድ የምርመራና የጥርጣሬ ለሊት ስለሆነ አስጊ ነው ። የጨለማውም ዓለም ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም ይቀጥላል" አለ በሀሳቡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 8 —

ሰዒድ የሼኹን ቤት በር ግፍትር አድርጐ አለአንዳች ተቃውሞ ከፍቶ ከገባ በኋላ እንደገና ዘጋውና የዘምባባ ዛፍ ወዳለበት ግቢ አመራ ። የዘምባባው ዛፍም ከመርዘሙ የተነሳ በሀዋ ውስጥ ዓይናቸውን አፍጥጠው ለሚጠብቁት ከዋክብት እጁን የዘረጋ ይመስላል ። "እንዴት ያለ ግሩም የሆነ መደበቂያ ቦታ ነው!" በሀሳቡ ። የሼኹ ቤት በቀንም ሆነ በማታ ምንጊዜም ክፍት ነው ። እነሆ በጨለማ ተውጦ ልክ እኔን የሚጠባበቅ መስሎ ይታያል ። እኔም ወደዚያው በእርጋታ አመራሁ ። ከሹክሹክታ በስተቀር ምንም ዓይነት ድምፅ አይሰማም ። ከሹክሹክታው መካከል "አላህ" የሚለውን ቃል ለመለየት ቻለ ። ሼኹ ማንብነባቸውን ቀጠሉ ። እኔ ከዚያ መኖሬን ያወቁ አልመሰለኝም ወይም ለማወቅ አልፈለጉም የሚል ሀሳብ መጣበትና ሰዒድ መፅሀፎች ወደተደረደሩበት በስተግራ በኩል ወደሚገኘው የክፍሉ ማዕዘን አመራ ። ከተነጠፈው የሰሌን ምንጣፍ ልብሱንና ጫማውን እንዳደረገ ከንዶቹን ተንተራሰ ። ሞንቅላቱ የንብ ቀፎ መስሎ ተሰማው ። ሆኖም ምንም ነገር ለማድረግ እንደማይችል ተረዳ ። በአፅምሮውም እንዲህ የሚል ሀሳብ አደረበት ። "አንተ

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትፈልገው የተኩሱንና የነበዊያን ጩኸት ደግመህ ለመስማት ነው። ከዚህ ላይ ደስ የሚልህ ነገር ቢኖር የሰናእ ጩኸት ባለመስማትህ ነው ። ሼኹን ለምን ሰላምታ አታቀርብላቸውም ? ጌታዬ የአላህ ሰላምታ ይድረስዎት አትላቸውም ። ግን ድምፅህ በጣም የተጻከመ ይመስላል ። ሰላምታም ለመስጠት የምትችል አትመስልም ። ውሃ ውስጥ የሰጠምክ ነው የምትመስለው ። አሁን የምታስበው ቆዳህ ወልሉን ሲነካ እንደ ግንድ ለጥ ብለህ የምትተኛ ነው የሚመስልህ! የሼኹ ተከታዮችም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው አንተን ሲያዩ በርግገው የሚሄዱ ይመስልሃል ። ነገር ግን ቀስ በቀስ የአላህ ስም ሲነሳ ልባቸው እየራራ ይሄዳልና ያዝኑልሃል ። "እኒህ አስገራሚ የሆኑ ሼኽ ለመሆኑ መቼ ነው የሚተኙት?"

የሚገርመው ግን እኚህ ሼኽ ጭሳ ባለ ድምፅ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ አሉ "እኔ ራሴ ምንም ማረጋገጫ ካላገኘሁ በስተቀር ፍጡር ማለት ከሀዲት ነው"

ሰዒድ በዚህ መሀል ከስቃዩ እንደተገላገለ ፈገግታ አሳየ ። "ለዚህ ነው ሼኹ እኔ እዚህ መሆኔን ሊሰማቸው ያልቻለው ። እኔም ብሆን ስለራሴ ምንም አይሰማኝም ።

በድንገት የጭህ ስሜት (አዛን) በዚያ በረጋ ሌሊት እንደ ማዕበል አስተጋባ ። ይህም አንድ ሌሊት እንቅልፍ አልባ ማሳለፉ እያሳዘነው ምናልባት በማግስቱ አስደሳች ነገር ያጋጥመኝ ይሆናል ብሎ አሰበ ። ጥሪውን እንደሰማ ከስቃዩ የተገላገለ መስሎት ብድግ ብሎ ተነሳ ። በመስኮትም ጭህ ሲቀድ ተመለከተ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እሱ ግን ከድካም ብዛት ራሱን መይም ሽጉጡን ማንቀሳቀስ አልቻለም ። ሼኩም ለስግደት ተዘጋጁና ሩኖስ አበሩ ። ስለሱ መኖር አለመኖር ምንም ምልክት አልሰጡም ፡ ግን ስጋጃቸውን ካነጠፉ በኋላ ለመስገድ ዝግጁ ሲሆኑ እንዲህ ብለው ጠየቁ ። "የጐህን ስግደት አትሰግድም እንዴ? እንዲህ ብለው ጠየቁ ። "የጐህን ስግደት አትሰግድ እንዴ?" ለም። ሼኹም ስግደታቸውን ቀጠሉ ።ሰዒድም ከባድ እንቅልፍ ወስዶት ነበር ። በህልሙ በእሥር ቤት ውስጥ ምንም እንኳ ወባዩ ሽጋ ቢሆንም ሲገረፍና ከገረፉት በኋላም የሚያሰፍር ጩኸት በማሰማቱ ሰናእ ልጁም በደረጃዎች መጨረሻ ቆማ ረዐፍን በጅራፍ ስትገርፈው ተመለከተ ። ቁርጣንም ሲቀራ ሰማ ። ስው መሞቱን አረጋገጠለት ። እንዲሁም ፖሊሶቹ በመኪና ሆነው ከሞተሯ ብልሽት የተነሳ መንቀሳቀስ የማትችለውን የሱን መኪና ስለተከታተሏት በአሪቱም ማዕዘን ጥይት ተኮሰባቸው ። በዚህ ጊዜ በድንገት ረዐፍ ብቅ ብሎ የሰዒድን እጆች አጠንክሮ በመያዝ ሽጉጡንም ወሰደበት ። ከዚህ ላይ ሰዒድ እንዲህ አለ ። "ከፈለግህ ግደለኝ ፡ ልጂ ግን ንፁህ ነች ። እሷ አይደለችም በፎቅ ደረጃዎች መጨረሻ የገረፈችህ ። እናቷ ነበዊያ ነች በዓሊሽ ቀስቃሽ ነት" ካለ በኋላ ከሚከታተሉት ሰዎች ለማምለጥ ከሼኹ ተከታዮች መካከል ተሸሎክሉት ገባ ። ሼኹም ፈዕመው እንደማያውቁት ሆነው "ማነህ አንተ? እንዴት ወደዚህ ልትመጣ ቻልክ አሉት?" ሰዒድም እኔ ሰዒድ ማህራን የዓም ማህራን የርስም የድሮ ተከታይ የነበረ ልጅ ነኝ ካለ በኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስላለፈው ጥሩ ጊዜ ለማስታወስ ያህል ነገራቸው ። ሼኹ ግን "መታወቂያህን አሳየኝ" አሉት ። ሰዒድ በጣም ስለገረመው እንዴት አንድ የበቃ ፀሎተኛ መታወቂያ ይጠይቃል? በፀሎት ቦታ ኃጢያተኞችና ዓድቃን በእኩል ዓይን ነው የሚታዩት ። ሼኹ "መታወቂያ የምጠይቅህ ኃጢአተኛ መሆንህን ለማረጋገጥና ዓድቃንን ስለምጠላ ነው" አሉት ሰዒድም እንደ ማስረጃነት በሽንጡ የቀሩ ጥይቶች ቢያሳያቸውም ሼኹ ግን ይህ በቂ አይደለም በማለት መታወቂያ እንዲያሳይ ከጠየቁት በኋላ "የመንግሥት ትዕዛዝ በቀላሉ አይጣስም" አሉት ። ሰዒድም የመንግሥት ትዕዛዝ የሚለው አነጋገር ገረመው ። "መንግሥት በእንደዚህ ያለ የፀሎት ስነ ስርዓት ምን ያገባዋል?" አለ ። ሼኹም ንግግራቸውን በመቀጠል "ይህም ትዕዛዝ የመጣው ከከፍተኛ የኃይማኖት መሪነት እጩ ከሆነው ከረዐፍ ነው" አሉት ። ለሶስተኛ ጊዜ ሰዒድ ገረመው ። "ረዐፍ በግልፅ የታወቀ ከሀዲና ወንጀል ከመሥራት የማይቆጠብ ነው" ሲላቸው ሼኹም ንግግራቸውን በመቀጠል "ስለዚህ ነው ረዐፍ ለከፍተኛ የኃይማኖት መሪነት እጩ የሆነው" አሉት ። ቅዱስ ቁርዓንን በአዲስ ትርጉም እንዲተረጎም ቃል ገብቷል ። ማንም ሰው በዚህ አዲስ ትርጉም መሰረት የመግዛት አቅሙ እስከፈቀደለት ድረስ እንዲጠቀም ያደርጋል ። ከዚሁ የሚገኘው ገንዘብም ለመሣሪያ ማከማቻ ፡ ራስን በራስ ለመግደል ለመሳሰሉ ከለቦች ይውላል" ሲሉ ሼኹ ገለፀለት ። ሰዒድ በዚህ ጊዜ "ይህ ከሆነ ዓለማው እኔ ዝግጁ ነኝ የማጎበሩ ፀሀፊ ሆኜ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድሠራ የረዑፍም የጥንት ገበዝ ተማሪ ስለነበርኩ በችሎ ታዬ እንደሚረካ ለፀሀፊነቱም ብቁ የሆነ ማስረጃ አለኝ" ሲል ሰዒድ መልስ ሰጣቸው ።

ከዚህ በኋላ ሼኹ ቁርዓን አነበቡ ፋኖሶችም በዘንባባው ዛፍ ቅርንጫፍ ተሰቀሉ ። አንድ ተማሪ "የግብዕ ህዝብ ሆይ የነቢዩ ዘር የሆነው ሁሴን የናንተ ነው" የሚል ዝማሬ አሰማ። ሰዒድም ዓይኖቹን ሲከፍት ዓለም በሙሉ ቀልታ ባዶና ትርጉም አልባ መስላ ታየችው ። ሼኹም ነጭ በነጭ ለብሰው። ሽበት የወረረው ጢማቸውን አንዣርገው ፡እግራቸውን አጣጥፈው ከምንጣፉ ላይ በእርጋታ ተቀምጠዋል ። ሰዒድ ከእንቅልፉ ባኖ ቁጭ አለ ። ሼኹም አስተውለው አዩት። ወደሼኹ በማቅኮር ይቅርታ ለመጠየቅ እንደሚፈልግ ሰው ወዲያውኑ እንደ እሳት ሰደድ በፍጥነት ትዝታዎች ከፊቱ ተደቀኑበት ። ሼኹ በዚህ ጊዜ "እኛ አሁን ያለነው ከሰዓት በኋላ ወደ አሥር ሰዓት ገደማ ስለሆነ ምግብ የሚሉት አልቀመስክም" አሉት ።

ሰዒድ በመስኮት ብቅ ካለ በኋላ እንደገና ሼኩን ተመለከተ ። "ከሰዓት በኋላ" አለ በመገረም ።

"አምን እኔኮ እንድትተኛ የተውኩህ አላህ ስጦታዎችን በፍቃድ በፈለገው ሰዓት ሊሰጥ ስለሚችል በማለት ነው" አሉ ።

ሰዒድ በድንጉት አንድ ነገር ትዝ አለው ። ከዚህ ተኝቼ ሳለሁኝ አንዳንድ ሰዎች ሳያዩኝ አልቀረም የሚል ጥርጣሬ

t.me/OLDBOOKSPDF

አደረበት ። “እኔ እኮ ብዙ ሰዎች ሲገቡ ሲወጡ ይሰማኝ ነበር” ሲል ዋሸ ። ከድካሙ የተነሳ እሱ ግን ፈፅሞ አይሰማም ነበር ። ሆኖም አንድ ሰው ምሳ አመጣለት ። አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ቦታውን የዘምባባውን ዛፍ ውሃ አጠጥቶ ግቢውንም ለአላህ አፍቃሪዎች አዘጋጅቶ ሄደ ።

“ለመሆኑ ፀሎተኞቹ በስንት ሰዓት ነው የሚመጡት? አለ ሰዒድ እንደመደናገጥ እያለ ።

“ፀሐይ ስትጠልቅ”

“አንተ ለመሆኑ መቼ ነው የመጣኸው?” አሉት ።

“ገሀ ሲቀድ”

ሼኹ ለጥቂት ጊዜ ዝም ካሉ በኋላ ጢማቸውን በእጃቸው እያሻሹ “ልጄ አንተ የምታሳዝን ፍጡር ነህ” አሉት ።

ሰዒድ በመደናገጥ “ለምን?” ሲል ጠየቀ ።

ሼኹም “ከባድና ጥልቅ የሆነ እንቅልፍ ነው የተኛኸው፡ ሆኖም ዕረፍት የሚሉት ነገር አታውቅም ። የፀሐይን ቃጠሎ ጉዳት እንደማያውቅ ህፃን ከጠራራው ፀሐይ የተኛ ትመስል ነበር ። የሚቃጠለው ልብህ ወደ ጥላ ለመሄድ እየከጀለ ግን ወደሚያቃጥለው ፀሐይ ያመራል ። በእግርህ መሄድ አልተማርክም ወይ?” አሉት ።

ሰዒድ ቀያይ ዓይኖቹን እያሻሸ ፡ “በጣም አሳዛኝ ነገር ነው ተኝቼ ሳለሁ ሰዎች ሲመለከቱኝ?” አለ ።

“ዓለም ስለ እሱ ምንም ስለማታውቅ እሱም ስለ አለም ምንም አያውቅም” አሉ በደንታ አልባነት አነጋገር ።

ሰዒድ በዚህ ጊዜ ሽንጡ የሚገኝበትን ኪስ ዳሰሰ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህ ላይ አንድ አስገራሚ ሀሳብ ብልጭ አለበት ። ሺኹ ምን ያደርጉ ይሆን አሁን ሽጉጤን አውጥቼ ብደቅንባቸው? ለመሆኑ የመሸበር መልክ ይታይባቸው ይሆን ?"

"ርቦሀል እንዴ?" ብለው ጠየቁት ።

"አልራበኝም"

እሳቸውም አተኩረው ተመለከቱት ። ምን የሆነ ሰው ነው በሚል አኳኋን?

"ጌታዬ ምን ያደርጉ ይሆን በእኔ ላይ የደረሰው ቢደርስ ብዎት ፡ ባለቤትዎ ብትከዳዎት ፡ ልጅዎ አባትነትዎን ብታስተባብል?"

"የአላህ ባሪያ ለአላህ ብቻ ነው የሚገዛው!" አሉት ዓይኖቻቸው በርህራሄ ተሞልተው።

በዚህ ጊዜ አንድ ሰው በከፍተኛ ድምፅ "አቡልሆል" እያለ ሲጮህ ሰማ ። ሰዒድ ቱሉ ወጣና ጋዜጣ ሻጩን ልጅ ጠርቶ አሥር ሳንቲም ሰጠው ። አቡልሆል ጋዜጣንም ይዞ ወደነበረበት ተመለሰ ። የሺኹን መኖር ፈፅሞ ረስቶ ዓይኖቹ በጋዜጣው አንድ ትልቅ ርዕስ ላይ እያተኮሩ ። "በቀልዓ ቀበሌ የደረሰ አስከፊ ወንጀል" ፣ በሚለው አቢይ ርዕስ ላይ ዓይኖቹ በቅፅበትና በፅብደት መስመሮችን አጉርጠው ቢመለከቱም ምንም ለመረዳት አልቻለም ። እሱ የፈፀመው ወንጀል ነው ወይስ ሌላ? ግን የራሱ ፡ የነበሚያና የዓሊሽ ፎቶግራፎች ወጥተውበት ነበር ። ይህ ከሆነ በደም ተንከሮ ከመለስ ላይ ተኝቶ ያለው ሰው ማነው?" ታሪኩ ተዕዝሏል ። በግልፅ ይነበባል። ወንጀሉ ነፋስ እንደበተነው አፀራ የትም ተዳር

t.me/OLDBOOKSPDF

ኗል። ስለ እሱ ታሪክው ጋዜጣም እንዲህ ይላል ። "ከእሥር ቤት ሲወጣ ባለቤቱ አንድ የሱ ተከታይ የነበረ ሰው አግብታ አገኛት" ይላል "ይሁንና ማነው ያ ሰው በደም ተንከሮ ከወለሉ ላይ ተኝቶ ያለው? እንዴት በጥይት ሊወድቅ ቻለ ሚቹ ሌላ ሰው መሆኑ ነው? የማላውቀው ሰው ነው ማለት ነው?" ጋዜጣውን እንደገና በትክክል ማንበብ ጀመረ ።

"ዓሊሽና ነበዊያ ቤታቸውን ነጭ ለባሹና ደጋፊዎች በተገኙበት ሰዓድ ስለ ልጁ ለመነጋገር በመጣበት ዕለት ቤቱን ለቀው ወጥተዋል ። በክፍሉም ሌላ ቤተሰብ ገብቶበ ታል ።የቁልፍም : የደላላም ሳይከፍል አልቀረም ። ለካ የሰማሁት ድምፅ የዓሊሽ አልነበረም! ጨኸቱም የነበዊያ አልነበረም!" አለ በሀሳቡ ። በወለሉ ላይ የተዘረረውም ሰው የሸአባን ሁሴን በመሐመድ አሊ ጐዳና የጉሊት ቸርቻሪ ነው ።

"አቡልሆል ጋዜጣ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ሲል ዕሯል ። "ሰዓድ ማህራን ባለቤቱንና የድሮ ጓደኛውን ለመግደል መጥቶ ከቤቱ ውስጥ አዲስ ነዋሪ የሆነውን ሸዕባን ሁሴንን ገደለ ። የዓሊሽ ጐረቤት ከሆኑት አንዱ ሰዓድ ማህራን ወንጀሉ ከተፈፀመ በኋላ ከቤቱ ወጥቶ ሲሮጥ መመልከቱን መስክሯል ። ፖሊስንም ጠርቷል ። ነገር ግን በአካባቢው በተፈጠረው ግርግር ድምፁ ሳይሰማ ቀርቷል ።" "ምን ዓይነት የዕብደት ሽንፈት ነው! ምን ዓይነት ዋጋ ቢስ ወንጀል ነው!" አለ ሰዓድ ሆዱ እየተቃጠለ ። ከእንግዲህ በኋላ ሰላም የለም ። የመስቀያ ገመድ አንገቱን እየተጠባበቀኝ ። ዓሊሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን በሰላምና በደህና ይኖራል ። ሐቁ ይህ ነው ። ጉዞውም ወደ መቃብር ነው ። ዓይኖቹን ከጋዜጣው አራቀ ።

ሼኹ በዚህ ጊዜ በመስኮት እየተመለከቱ ገፅታቸው ላይ የደስ ደስ መልክ ይታይባቸው ነበር ። የሳቸውም ፈገግታ ባልታወቀ ምክንያት ሰዒድን አስፈራው ። ወደ መስኮቱ በኩል ሄዶ ቆም ብሎ ሼኹ የሚመለከቱትን ለማየት ፍላጐት አደረበት ። ምናልባት እሱም ሰማይን ሲመለከት ፈገግታው ይመጣለት እንደሆን በማሰብ ነበር ። ነገር ግን ምኞቱን አልፈፀመም ። ሼኹ ፈካ ይበሉ አይበሉ አይደለም ዋና ጉዳይ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሼኹ ተከታዮች ወደዚህ ይመጣሉ ። አንዳንዶቹም በጋዜጣ ፎቶውን የተመለከቱት በደንብ ሲያውቁት ስለሚችሉ እልፍአእላፍ ሰዎች ፎቶውን በአሁኑ ጊዜ በመገረምም ሆነ በፍርሀት ወይም በማድነቅ በመመልከት ላይ ናቸው ። ህይወቱ ወና ሆነ ። ፖሊሶችም አስከ ህይወቱ መጨረሻ ድረስ ይከታተሉታል ። ፊቱንም በመስተዋት ለማየት ይፈራል ። ነፍሱ ልትወጣ ትንሽ ነው የቀራት ። ከጉድጓድ ወደጉድጓድ አንደምትሽሎከሎክ አይጥ በመርዝ ፡ በድመትና በዱላ አንደሚያሳድዷት ዓይነት ነው ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ጠላቶቹ ዓለማቸውን ይቀጫሉ ።

ሼኹ በዚህ ጊዜ ወደ ሰዒድ ዞር ብለው በለስለስ አንደበት "ደክሞሀል ሂድና ፊትህን ታጠብ" አሉት ።

ሰዒድም በጭንቀት ጋዜጣውን እያጣጠፈ "እሄድሎታለሁ እኔን ከማየት ያርፋሉ" አለ ። ሼኹ ለስለስ ባለ አንደበታቸው እንደገና "ይህ እኮ ያንተ መጠለያ ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

አለ·ት ።

“አሞን ግን ሌላ መጠለያ ሊኖረኝ አይችልም?”

“ሌላ ቢኖርህ ወደዚህ አትመጣም ነበር” አሉ አንገታ·ቸው·ን በመድፋ·ት ።

በሰዓድ ሀሊና እንዲህ የሚል ሀሳብ መጣበት ። “አሁን አን·ተ ያለ·በህ ወደ ተራራ·ው ሂደህ እስኪጨልም ድረስ ከዚያ መው·ጣት የለ·በህም ብርሃን የሚሉ·ትን ነገር አስወግድ ። ሻዕባን ሁ·ሴን·ን መግደል·ህ ፋይዳ የሌለው ድካም ነው ። ለምን ይጠቅማል ? ሻዕባን አን·ተ ማነህ? እኔ አላው·ቅህ አን·ተ አታ·ው·ቀኝ ልጅች አለ·ህ? ለመሆኑ አንድ ቀን የማታ·ው·ቀው የማያው·ቅህ ሰው እንደሚገድል ታስብ ነበር?” ያለ አንዳች ምክን·ያት·ም እንደምት·ገደል ታ·ው·ቅ ነበር? ነበዊያ ዓሊሽን ስላገባች አን·ተ የም·ት·ገደል መሆንህን ታ·ው·ቅ ነበር? በትክ ክል መሞት ያለባቸው ዓሊሽ ወይም ረዐ·ፍ ሳይገደሉ ቀርተው አን·ተ በስህ·ተ·ት እንደምት·ገደል ታ·ው·ቅ ነበር? እኔ ገዳይህም ብሆን ሚስጥሩ አልገባኝም ። ሼህ ዓሊም ቢሆኑ ሊገባቸው የሚች·ል አይመስለኝም ። እኔ የሞከር·ኩ·ት የ·ተ·ተበ·ተበብ·ን ወጥመድ በክፈ·ል ለመበጣጠስ ነበር ። ነገር ግን የባሰ የ·ተወሳሰበ ሆነ·ብ·ኝ” እያለ ሰዒድ ቁና ቁና ተ·ነፈሰ ።

“በጣም አድርጎ ደክሞሃል!” አሉ ሼኹ ።

“ይቺ የእርስዎ ዓለም ነች ያደከመች·ኝ!” ሲል መለሰላ·ቸው ሲቃ በያዘው ድም·ፅ ። “እኛም አንዳንድ ጊዜ በዚች ዓለም እንዘም·ራለን” አሉ ሼኹ በፀጋ ።

“ደህና ሁ·ኑ ጊታ·ዬ” አለ ብድግ ብሎ የሚሄድበት·ን

t.me/OLDBOOKSPDF

አቅጣጫ ለይቶ እንደሚያውቅ ሰው ።

“ደህና ሁኑ ማለትህ ፍቺ የሌለው ቃል ነው ። አንተ ምን ለማለት እንደፈለግህ ባላውቅም እስክንገናኝ ድረስ ደህና ሁኑ ብትል የሚሻል ይመስለኛል” አሉት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— ፱ —

“ምን ዓይነት ጨለማ ነው እባካችሁ! ወደ የሌሊት ወፍነት መለወጥ አለብኝ ማለት ነው? በአሁኑ በውድቅት የተጠበሰ ጮማ ስጋ ሽታ ከአንድ በር ሰርጐ የሚመጣው ለምንድን ነው? ኑር ለመሆኑ መቼ ነው የምትመጣው ? ለብቻዋ ትመጣ ይሆን? እኔም ከሷ ከፍል ለረጂም ጊዜ ማለት ፖሊሶቹ እስኪረሱኝ ድረስ ለመቆየት እችል ይሆን? ረዐፍም ከእኔ ለዘላለም የተገላገልክ ይመስልህ ይሆን? ግን በዚች ሽጉጥ ዕድል ከረዳኝ ብዙ አስደናቂ ሥራዎች አከናውን ይሆናል ። በዚች ሽጉጥ የቱኙትን ሰዎች እቀስቅስ ይሆናል ። የኔ ችግር ስር መሰረቶች እነሱ ናቸው ። ምክንያቱም ነበሚያ፡ ዓሊሸና ረዐፍ የተባሉት ሰዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት የሆኑ እነሱ ናቸው ።

የእግር ኮቴ የሚመስል ድምፅ በፎቁ ደረጃዎች ሲረገጥ ሰማና ሰው መምጣቱን ካረጋገጠ በኋላ በፎቁ ደረጃ መደገፊያ በኩል ቆሞ ደብዘዝ ያለ ብርሃን በማድማዳዎች በኩል ሲንቀሳ ቀስ ተመለከተ ። “የክብሪት ብርሃን ሳይሆን አይቀርም” አለ። የእግር ኮቴው ድምፅ እየጮላ መጣ ። ድምፁ ከባድ ቢሆንም በዝግታ ነበር ። ኑር ፡ ሰዓድ መሆኑን እንድታውቅና እንዳትደነግጥ በማሰብ ጉሮሮውን አፅድቶ ጮኸ ብሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

"እህህ" አለ ። ኑርም "ማነህ?" አለች ፍርሃት በተሞላበት ድምፅ ። ሰዒድ ራሱን በደረጃው መደገፊያ መካከል በማድረግ በገቸተኛ ድምፅ "ሰዒድ ማህራን" ነኝ አለ ። የቀሩትን ደረጃዎች ሮጥ ብላ ወጣችና ክንዶቹን በመያዝ "በጣም አድርጌ አዝናለሁ ለመሆኑ ብዙ ጠበቅህ?" አለች ። በሩን ከፈተች ፡ ከንዱን እንደያዘችው ወደ ክፍሉ አመሩ ። መብራቱን አበራች ። ከዚያም አንዲት አነስ ያለች ክፍል አልፈው ሶፋ ወዳለው የሳሎን ክፍል ከገቡ በኋላ በፍጥነት ወደ መስኮቱ ሄዳ ክፍሉን አፍኖት የነበረውን ዓየር ለማስወጣት ከፈተችው ። "እኔ ከዚህ የደረስኩት ልክ እኩለ ለሊት ነው" ካለ በኋላ ፊት ለፊት ካሉ ሁለት ሶፋዎች አንዱ ላይ ዘርፈጥ ብሎ ተቀመጠ ።

"አንቺን ስጠብቅ ጠንራ ሽበት አወጣ!"

"አንተ ትመጣለህ የሚል ሀሳብ ፈጽሞ አልነበረኝም" አለች ከአንድ ሶፋ ተቀምጣ ከምትሰፋቸው ጨርቃ ጨርቆች የቀሩትን ቁርጥራጮች በመሰብሰብ ።

"እንዴት እመጣለሁ ብዬ ቃል ገብቼልሽ?" አለ የቀዘቀዘውን ስሜቱን በፈገግታ በመሸፈን ። እሷም መልስ ሳትሰጥ ትንሽ ፈገግታ በማሳየት "ትናንት ፖሊስ ጣቢያ ተገኝቼ ቃሌን ሰጠሁ ። በመስቀለኛ ጥያቄ ከፋኝ ነው ያሰቃዩኝ ። ለመሆኑ መኪናዋ የት ደረሰች ? አለችው ።

ኩቱን አውልቆ ከሶፋው ወንበር ካስቀመጠ በኋላ በላብና በአቧራ የተለበደው ሸሚዙን እያስተካከለ "መኪናዋ ምንም እንኳ በጣም አድርጋ ብታስፈልገኝም አንድ ቦታ መጣል አለብኝ የሚል ሀሳብ መጣብኝ ። ስለዚህ ጣልኋት ። እነሱም ያገኟታል ፡ ለባለቤቱ ይሰጧታል ። መንግሥት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሆነ አንዳንድ ሌቦችን ይደግፋል ። እንደኛ ያሉትን ምስኪኖችን ማን ያጠቃል!”አለ ።

“ለመሆኑ ትናንት ምን ሠራህባት?” አለች በጭንቀት።

“በዕውነቱ ምንም አልሠራሁም ፡ ሆኖም ሁሉንም ነገር ጊዜው ሲደርስ ታውቂዋለሽ” “ግሩም ከፍል ነው ፡ ዓየርም ፡ ፀሐይም በደንብ ይገባል ፡ አካባቢው የመቃብር ቦታ ስለሆነ ሌላ ነገር የለበትም ። ስለዚህ ዓየሩም ያልተበከለ መሆን አለበት” አለ በማሾፍ ራሱን በመስኮት ወጣ አድርጐ ከተመለከተ በኋላ ።

እሷ በዚህ ጊዜ ዓይኖቿን አፍጥጣ በፍቅር ትመለከተው ነበር ። እሱ ግን የደከመ አዕምሮው የተረበሸ ይመስላል ። ሁሉን ነገር ትቶ የሷን ፍላጐት ማሟላት እንዳለበት ግን ይረዳል ።

“ከውጭ ቆመህ ሰረጂም ጊዜ ስለጠበከኝ በጣም አድርጌ ነው ያዘንኩት”

“አይ ምንም አይደል ግና ሰረጂም ጊዜ ያንቺ እንግዳ ሆኜ ከዚሁ ልኖር አይደል” አለ አተኩሮ ወደ እሷ በመመልከት።

“ደስ ይለኛል ዕድሜ ልክህን ከእኔ ጋር ብትሆን!”

“ወደ ጐረቤቶችሽ ከመዛወሬ በፊት ከአንቺ ጋር እቆያለሁ!” አለ ሌባ ጣቱን ወደ መቃብር በመቀሰር ።

እሷ በሌላ ሀሳብ ውስጥ ተመስጣ ስለነበርና የሱን ቀልድ ስላላጤነችው እንዲህ ስትል ጠየቀችው ። “ቤተሰቦችህ አይጠይቁህም እንዴ?”

“ምንም ቤተሰብ የለኝም” አለ ጭንቅላቱን ዝቅ አድርጐ የላስቲክ ጫማውን በመመልከት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ባለቤትህ ማለቱ ነው”

“እሷ ማለት ስቃይ ፡ ዕብደትና የከሸፉ ጥይቶች ማለት ነው!” ብሎ መለሰላት ። ጠያቂዋ የምትፈልገው እንደዚህ የረቀቀ መልስ ሳይሆን አብረው መሆናቸውን ወይም መለያየታቸውን ለማወቅ ነበር ።

“አንተ ለመደበቅ ብትሞክርም ጋዜጦች በሰፊው እያወሩት ስለሆነ መደበቁ ለምን ይጠቅም ይሆን?” አለ በሀሳቡ ። አያይዞም “እኔ ምንም ቢተሰብ የለኝም ብያለሁ” አሁን አንቺ ይህ ቃል ምን እንደሆነ ትርጉሙን ለማግኘት እንደምታስቢና ፊትሽም የደስታ መልክ እንደሚታይበት ይገባኛል ፡ ደስታሽ ግን ለእኔ ደስ አይለኝም” አለ እንደገና በሀሳቡ ።

“ፈታሁት እንዴ?” አለች ኑር በመገረም ።

“በእሥር ቤት እያለሁ ነው የፈታኋት ። ስለዚህ ጉዳይ ባናወራ ይሻላል”

“አጣማ ነች ፡ ተንኮለኛ ነች ፡ እንዳንተ ያለ ባል ዕድሜ ልክም ቢፈረድበት መጠበቅ ነበረባት” አለች በቁጣ መልክ።

“እንደኔ ያለ ሰው በእውነቱ አያሳዝንም ፡ ባታገኚልኝ ይሻላል!” ካለ በኋላ በሆዱ “እውነቱን ከፈለግሽ እኔ ለብዙ ጊዜ አልተንከባከብኳትም” ሲል ነገራት ።

“ያም ሆነ ይህ ለአንተ የምትገባ ሴት አይደለችም!”

“እውነትሽን ነው ካንቺ ጋር ላመሳጠናት ግን ሰማይና መሬት ናችሁ ፡ አንቺ ጭራሮ ፡ አንድ ሀመስ የቀረሽ ፡ እፍ ቢሉሽ የምትጠፊ ፡ በጣም አድርገሽ የምታሳዝኚ ፡ እሷ ግን ሰውነቷ ሙሉ ሀያው ፡ ቁመናዋ አስደሳች” ካለ በኋላ በሀሳቡ” አንድ ሰው ከዚህ መሆኔን እንዲያውቅ አልፈለ ግም!” ሲል አሰጠነቀቃት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደ ኩል እኳልሃለሁ ፡ ከብብቴ ሥርም እደብቅሃ ለሁ!" አለችው የሷ መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ ቀጥላም "የሆነ አደገኛ ነገር ፈፅመሃል ወይ?" ስትል በልመና መልክ ጠየቀችው ። በአሉታ ትከሻውን ነቀነቀ ።

ኑርም ቆም በማለት "የሚበላ ነገር ላመጣልህ ነው ፡ ምግብና መጠጥም አለኝ" አለችው ። ታስታውሳለህ እኔ ሳፈቅርህ አንተ ምን ያህል ገሸሽ እንዳደረከኝ?" ስትል በምሬት ወቀሰችው ።

"ለፍቅር ጊዜ አልነበረኝም"

"ከፍቅር የተሻለ ምን አለ? ካለች በኋላ በመገረም እኔ ፈንዳንድ ጊዜ ልብህ ከድንጋይ ነው የተሠራው እል ነበር ። ሆኖም አንተ ወሀኒ ቤት ስትገባ እንደኔ አድረጉ ያዘነልህ የለም" ስትል አዕናኗችው ።

እርሱም "ስለዚህ እኮ ነው ወደ ማንም ሰው ከመሄዴ በፊት በቀጥታ ወደ አንቺ የመጣሁት" አላት ።

"ምን ማለትህ ነው በአጋጣሚ አይደለም እንዴ የተገና ኘነው! አንተ ግን ፈፅመህ ሳትረሳኝ አልቀረህም" አለች እንደመቆጣት ብላ ።

"ምን ማለትሽ ነው አንቺስ ሌላ ቦታ የማላገኝ መስሎሽ ነው—" አለ ሆን ብሎ የተቆጣ በመምሰል ።

በጣም አድርጉ አሳዘናት ። ጉንጮቹን በፍቅር በእጆቿ እየዳሰሰች በዚህ ጊዜ አንድ ነገር ትውስ አላት "ይቅርታ አድርግልኝ የአራዊት ጥበቃ (ሙ) ጠባቂዎች ጦብኚዎችን ከአንበሳ ጋር እንዳይጫወቱ ይከላከሉ አይደል? ፊትህ እን ዴት ግሏል ። ምን አለ በቀዝቃዛ ውሃ ብትታጠብ" ስትለው ሀሳቡን በደስታና በፈገግታ ተቀበለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመታጠቢያ ቤት ስትወጣ ምግቡ ተዘጋጅቶ ይጠብቅ ሀል ። ከመኝታ ቤት ሆነን ነው የምንመገበው ። የመኝታ ክፍሉም ከዚህ ክፍል የተሻለ ልክ እንደዚህ ወደ መቃብሩ ትይዩ ነው!" አለችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 10 —

አቤት የመቃብር ብዛት! ዓይኖቹ ለማየት እስከቻሉ ድረስ ያለው ቦታ ሁሉ መቃብር የተዘረጋበት ነው ። በመቃብሮች አናት ላይ የተተከሉት ድንጋዮች የሚያመለክቱት ነገር ቢኖር "እጃችሁን ስጡ" የሚሉ ይመስላሉ ። ሆኖም እነዚህ መታጎን ምንም ዓይነት ስጋትና ፍርሀት የለባቸውም። ቦታውም የፀጥታና የድል ቦታ ከመሆኑም በላይ ገዳይና ተገዳዩ ሲቦኾና ፖሊሶች ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ በሰላም አንድ ላይ ተቃቅፈው የሚተኙበት ሰላማዊ ቦታ ነው ።

ኑር ለጥ ብላ ተኝታለች ። ከርፊያውም የሚያቋርጠው ከሰዓት በኋላ ከእንቅልፏ ስትነሳ ብቻ ነው ። "ከዚህ እስር ቤት መቆየት አለብህ ፖሊሶች እስኪረሱህ ድረስ ። ለመሆኑ ፖሊሶች ይረሳሉ?" አለ በሀሳቡ ። መቃብሮች የሚያስታውሱህ ነገር ቢኖር ሞት ምን ጊዜም ቢሆን ህያውያንን እንደሚያታልል ነው ። ከዚያች ቀን ፡ ሰዓትና ደቂቃ በጭፍን ተኩሰህ ያልተፈለገ ሰው ከገደልክ በኋላ የሞት ፍርድ እንደተፈረደብህ ታውቃለህ ። ሆኖም ብዙ ጥይቶች ስላሉህ ገና አልተሸነፍክም ማለት ነው ። ሰዓድ ዓይኖቹን ከመስኮቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነቅሎ ወደ አልጋው እያተኮረ ሳለ ኑር ተነሳች ። ራቂቷን ወጉሯ ተመሰቃቅሎ በጭንቀት የተዋጠች ትመስል ነበር ። ሰዲድን ስታይ ደስ አላትና "በሀልሜ እጅግ በጣም ሩቅ ቦታ የሄድክብኝ መሰለኝና አንተን ለመጠበቅ ተስፋ እስከመቁረጥ ደረጃ ደርሼ ነበር" አለችው ። "ይህ ህልም ነው" አለ በሀዘን መልክ! ፍቺው ግን "አንቺ ሩቅ ቦታ ትሄጃለሽ ፣ እኔ ነኝ ለረጂም ጊዜ በቀቢፀ ተስፋ የምጠብቅሽ" አላት ። ወደ መታጠቢያ ቤት ሄደች ። ታጥባ ስትመለስ ወጉሯን በማድረቅ ላይ እያለች ትክ ብሎ ተመለከታትና ወጣት መሆኗን አስተዋለ ። ዕድሜዋ ግን እንደሱ ሰላሳ አመት ገደማ ነው ። እሷ ግን ልጅ ነኝ ትላለች ። ስለዕድሜዋ ትዋሻለች ። ውሸት በገሀድ ከምትፈፅማቸው ብዙ ታጢአቶችና መጥፎ ነገሮች አንዱ ነው። የሚያሳዝነው ግን ሌብነት ከነዚሁ ታጢያቶች አንዱ አለመሆኑ ነው ። "ጋዜጦችን እንዳትረሽ?" አላት ከበራፉ ከደረሰች በኋላ ወደ ሳሎን ቤቱ እያዘገመ ። እሱም ከሳሎን ቤቱ ተመልሶ ከሶፋው ላይ ተቀመጠ ። አሁን እሱ ለብቻው ነው ። ፊዕሞ በዚህ ዓለም ብቸኛ ሰው ነው ። መዓሐፎቹንም ከሼክ አሊ ቤት ነው የተዋቸው ። ጊዜውን ለመግደል የተሸነቋቆረውን የክፍሉን ጭው ጣሪያ ያማትራል። የሳሎን ቤቱ የቀይ ስጋጃ ነፀብራቅም በጣሪያም ይታየው ጀመረ ። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ከሚከንፉ እርግቦች ላይ የተጫነ ሉል ከምትመስለውና በመጥለቅ ላይ ከምትገኘው የምሽት ፀሐይ የተወረወረው ጮራ ወደ ክፍሉ ገባ።

"ሰናእ ያንቺ ዝምታ ልክ እንደዚህ መታበር ዝምታ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሆነብኝ በጣም አድርጐ ያሰቃየኛል ። እኔና አንቺ እንደገና እንገናኝ ይሆን? የት? መቼ? አንቺ አውን እንደማትወጅኝ እርግጠኛ ነኝ ። በተለይ አጉል የሚተኩሱና የሚባርቁ ጥይቶች በበዙበት በዚህ ዓለም እንደዚህ ከሚከሽፉ ጥይቶች ጋር ብዙ ትዝታዎችና ምኞቶችም ፏምር አብረው ይከሽ ፋሉ። አሳዛኝ ነገሮችንም ትተው ያልፋሉ'' ። ካለ በኋላ በሀሳቡ የኔ ችግር የሚጀምረው በጂዛ ጐዳና በሚገኘው በተማሪዎች ሆስቴል ነው ። ዓለ.ሽ ይሆን ያህል ከፍተኛ ሚና በህይወቱ የሚጫወት አይደለም ። ነበዊያ ግን ራሴን ከሥር መሰረቱ አናግታዋለች ። ነበዊያ አንዳንድ ምግቦችን ለመግ ዛት ከተማሪዎች ሆስቴል አጠገብ ወደሚገኘው ሱቅ ''ግሮ ሰሪ'' አዘውትራ ትመጣ ነበር ። ቁመናዋ ከማማሩም ሌላ አለባበሷ ማራኪና አስደናቂ ስለነበር በገረዶች አካባቢ የቁንጅና ንግሥት ተብላ ትጠራ ነበር ። ኑሮዋም በአንድ አሮጊት የቱርክ ከበርቴ ሴት ቤት በግርድና ነበር ። ይህች የቱርክ ከበርቴ ሴት በአትክልት ባጌጠው በአንድ ትልቅ ቪላ ውስጥ ለብቻዋ ትኖር ነበር ። በጣም ከበርቴና ትዕቢተኛ ሴት ነበረች። ከሷ ጋር በማንኛውም ዓይነት ግንኙነት ያላቸው ሠራተኞች ቆንጆ እንዲሆኑ ፣ ንፅህናቸውን እንዲጠበቁና ልብሳቸውን እንዲያሳምሩ ታስገድዳቸው ነበር ። ስለዚህ ነበዊያ ከቁንጅናዋ ሌላ በአለባበሷም ሽቅርቅር ፣ ወጉሯም ዘንፋላ ፣ ጫንቃዋን የሚሸፍንና ሰንደል ጫማም የምታደርግ፡ ቀሚሷም ሀያው የሆነውን ሰውነቷን የሚያጐላ ፣ ዓይኖቿም በጣም ማራኪ ፣ አፍንጫዋም ስልክክ ያለ ፣ አጭም ሀይወት

t.me/OLDBOOKSPDF

የተሞላበት የሚመስል ፡ አገጩም በጥንቃቄ የተቀመጠ ወደ መጨረሻው ክብ የሚመስል ፡ ባጠቃላይ አቋሟ የአገር ቤት ቆንጆ እንቡጥ ልጃገረድ ነበረች ።

ሰዓድም ከተማሪዎች ሆስቴል ሥራውን ጨርሶ እሷን በመንገዱ መጨረሻ ቆም ብሎ ይጠብቃት ነበር ። ከሩቅ ስትመጣ ጅምሮ በዓይኖቹ ይከታተላታል ። ወደ እሱ እየቀረበች በመጣች ቁጥር አዲስ ሀይወት ያገኘ ይመስለው ነበር ። ዐይኖቹ እሷን ሲያዩ እንደ አስደሳች ሙዚቃ ይደስታሉ ። በደስታም ያቀላሉ ፡ ወደ መስክር ደረጃም ይደርሳሉ ። ወደ ግሮሰሪውም ስትገባ ምንም እንኳ ብዙ ሰዎች ለመግባት ወረፋ ይዘው ቢሆኑም እንኳን ሁሉ አልፎና ገፍትሮ ሹልክ ብሎ ተከታትሏት ይገባል ። ምሯቱ በዚያን ጊዜ እንድ ቃል ስድብም ቢሆን ከሷ ለመስማት ይጓጓ ነበር ። እሷ ግን ምንም ስሜት እንደሌላት ገፍትራው ትሄድ ነበር ። በዚህ ጊዜ ሀያሉ ይፈልምበታል ። ሆኖም ብርቱ ጠንካራ ሰው ስለሆነ የፍቅርን ትግል ቀጠለበት ። እንድ የዘንባባ ዛፍ ብቻ ወደምትገኝበት ቦታ ስትደርስ ሮጥ ብሎ ሄዶ መንገዱን ያደናቅፋት ጀመረ ። እሷም በቁጣ ለመሆኑ አንተ ማነህ?'' አለችው ። ''እኔ'' አለ በመንደርደርና ትዕቢት በተሞላበት አነጋገር ''አንቺ ስለእኔ ማንነት ትጠይቂያለሽ የኔ ፍቅር በእንቺ አካልም ሆነ መንፈስ ሰርጾ መግባቱን አታውቂም እንዴ?'' አላት ።

''እኔ መጥፎ ስነምግባር አልወድም'' ስትል መለሰች ለት።

t.me/OLDBOOKSPDF

“እኔም ካንቺ የበለጠ ነው ሞራለቢስ ሰውን የምጠላው። መልካም ባህሪን ፡ ውበትንና ጥሩ ስነምግባር ያለው ሰው ከልቤ ነው የማፈቅረው። አሁን ያልኩት ሁሉ ባንቺ ላይ ነው የሚንፀባረቀው ። የኔ ፍቅር እስከቤቱ በራፍ ድረስ ላድርስሽ” ስትላት

“እባክህን ጥሩ ከፊቱ ዞር በል ፡ የአንተን እርዳታ አልሻም” አለችህ ። ከፊቷ ግን ትንሽ የፈገግታ ብልጭታ አሳየችህ ። አንተም ይቺን የደበዘዘች ፈገግታ መሰረት በማድረግ ተከተልካት ።

“ከዚህ አንድ እርምጃ ብትጨምር እመቤቱ ያዩኛል ጉድ ያፈላብኛል እመቤቱም ከበረንዳ ተቀምጠው ነው የሚጠባበቁኝ” አለች ።

“እኔ በበኩሌ በጣም እድርጌ አልሽኛ ነኝ ከፈለግሽ ትንሽ ወደኋላ እንሂድና የምነግርሽ ነገር አለ አልካት ። “ምን ልትነግረኝ ነው?”

“እኔ ዓይንሽን አልሞላም እንዴ?” አልካት (ጭንቅላቷን በኋይል አወዛወዘች ነገር ግን ፍጥነቷን ቀነሰች ። እንዲህ እንዲህ እያለ ከነበዊያ ጋር አስደሳች ፍቅር መሰረትክ ። ግን በዚያን ጊዜ በዚያ አካባቢ የተመሰረተው ፍቅር መዘዙ ካንተ አልፎ የብዙ ሰዎችን ህይወት የሚነካ ብሎም ዓለም አቀፍ እንደሚሆን ታውቅ ነበረ? በዚያ ጊዜ የተሰማህ ደስታ ወደር የለውም ነበር ። ዘለልክ ጨፈርክ ወደ ተማሪዎች ሆስቴልም በደስታ ብዛት እንደሰከረ በሬ መስለህ በጐረናው ድምፅህ የፍቅር ዘፈን እየዘፈንክ ሄድክ ። የተሻለ ሥራም ማግኘት

t.me/OLDBOOKSPDF

አለብኝ በማለት የሰርክስ ተጫዋች ለመሆን ወሰንክ። ከዚያት የሰርክስ ቡድን ጋርም ከቀበሌ ወደ ቀበሌ ከክፍለ ሀገር ወደ ክፍለ ሀገር በመሄድ ሠራህ ። ነገር ግን አንድ ምሳሌ ትዝ አለህ "ከዓይንህ የራቀ ከልብህም ይርቃል" የሚለው ። ስለዚህ ከነበዊያ መራቅ የለብኝም ብለህ ወሰንክ ።

ከዕለታት አንድ ቀን በአካባቢያችሁ ከሚገኘው የካይሮ ዩኒቨርስቲ በራፍ አጠገብ ከነበዊያ ጋር ቆመህ "ምን አለበት በእስልምና ሀግ መሰረት ትዳር ብንመሰርት" አልካት። በዚያን ሰዓት ብዙ ልጆች ወደ ዩኒቨርስቲ ሲገቡና ሲወጡ ትመለከት ነበር ። እነዚህ ልጆች ከአንተ በዕውቀትም ሆነ በትምህርት የተሻሉ አልነበሩም ። ዩኒቨርስቲ ለመግባት የቻሉት የከበርቴ ልጆች በመሆናቸው ብቻ ነው ። በዚህ ሰዓት በዩኒቨርስቲ አካባቢ ባለው መንገድ ሰለምለም ያለ የጨረቃ ብርሃን በስተቀር በቂ ብርሃን አልነበረም ። ለፍቅር ግን አመቺ ነበር ። በዚህ ጊዜ ነው ስለአንተ ማንነት ማውራት የጀመርከው "ሥራዬ ከፍተኛ ትርፍ የሚገኝበት የወደፊት ዕድሌም እጅግ በጣም ብሩህ የሆነ ፡ መኖሪያዬም በደራሳ ቀበሌ በጀበል ጐዳና ከሼክ አሊ ቤት አጠገብ በሚገኘው አንድ ትልቅ የተዋበ ፎቅ ነው ። ሼክ አሊ በጣም የተባረኩ መንፈሳዊ አዛውንት ናቸው። ስንጋባ አስተዋውቅሻለሁ ። በቅርቡም መጋባት አለብን" አልካት ። "አንችም ከዚያች ትዕቢተኛ የቱርክ ሴት መገላገል አለብሽ" አልካት ። በዚህ ጊዜ እሷ "እኔ አባት እናት የለኝም እክስት ግን በሲዲ አልአርበዒን ቀበሌ አለችኝ" አለችህ ። አንተም እጇን ያዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

አድርገህ "ባል እንድሆንሽ ፍቀጂልኝ" ብለህ በዚያ በጨረቃ ብርሃን ሳም አደረካት ። ከዚያ በኋላ ከየአቅጣጫው የመልካም ምኞት ቃላት ጐረፉልህ ። የሰርክሱ ባለቤት (ዘያትም) ለሠርጉ እንዲረዳህ መቶ ብር ለገሰህ ። ዓሊሽም ሠርጉን እንደራሱ ሠርግ ቆጥሮ ጥሩ ጓደኛ በመምሰል ደስታው ከመጠን በላይ ነበረ ። "ከዚህ ላይ በጣም አድርጐ የሚከነክነኝ ነገር ቢኖር" አለ ሰዒድ "እኔ ጀግናውና ብልህተኛው ፡ ቀዩ ሰይጣን ሳይቀር የሚፈራኝ ፡ እንዴት አድርጌ ሞኝና ጂል ሰው በሆነው በዓሊሽ ልታለል በቃሁ? እኔ እርግጠኛ ነኝ ዓሊሽና ነበዊያን ወደ ሳይና በረሃ ነቢዩ ሙሴ ወደጠፉበት ብልካቸው እኔ እንኳን ባልኖር እኔ ከነሱ መሀል ያለሁ እየመሰላቸው እንድም መጥፎ ስነ ምግባር ሳይፈፅሙ ተመልሰው እንደሚመጡ አልጠራጠርም ። ግን እሷ ምን ዓይነት እርኩስ ሴት ናት አንበሳን ትታ ወደ ውሻ ትጠጋለች ። ይህ የሚያመለክተው በተፈጥሮዋ ቆሻሻ ሴት ስለሆነች በሁለቱ ዓለምም መገደልና መሰቃየት አለባት ። ግን የምሰጋው ዓይነ ስውር የሆኑ ጥይቶች መገደል ያለበትን ትተው ንፁህ የሆነውን ሰው እንዳይገድሉ ነው ። ብዙ እርኩሶች እያሉ ንፁሀንን የማይመለከታቸውን የሚገድሉ ጥይቶች ለስቃይና ለእብደት ይዳረጋሉ። ከዚህ ላይ ሰናእ ልጁ እንዴት እንደተወለደች የነበረው ደስታ የመጀመሪያ ቀን ለቅሶዋ ምን ያህል አስደሳች እንደነበረ ትዝ አለው ። ከእንቅልፉ ባንኖ ሲነሳ ይህ ሁሉ የታየው በህልሙ እንደሆነ ተረዳ ። "ለካስ ዓሊሽ ሽጉጥ ይዞ እኔን ለመግደል ሲያሳድደኝ የነበረው

t.me/OLDBOOKSPDF

በህልሜ ነበር ማለት ነው?'' አለ።

በቅዕበት የቁልፍ ሽኩሽኩታ በመቆለፊያው ሲገባ መገጓያውም ሲከፈትና ሲዘጋ ድምፅ ሰማ ፡ መብራትም በራ። ኑርም በፈገግታ በትልቅ ኪስ ወረቀት በየዓይነቱ ምግብ ይዛ ብቅ አለች ። ሳም አደረገችውም ። ''ታላቅ ግብግ አሮስቶ ፡ ቢስቴክ ፡ ላዛኛ ፡'' ምረጥ አለችው ።

እሱም ሳም አድርጐ ''ጠጥተሻል?'' ሲል ጠየቃት

''የሥራው ዐባይ ነው'' ብላ ከነገረችው በኋላ ገላዬን ታጥቤ እመጣለሁ ፡ ጋዜጣዎችን አምጥቼልሃለሁ'' አለችው። በዓይኖቹ እየተከታተላት ወደ መታጠቢያ ክፍሉ ሄደች ። እሱም የጧትና የከሰዓት በኋላ ጋዜጦችን በሙሉ ስሜቱ መቃኘት ጀመረ ። እሱን የሚመለከት ብዙ አዳዲስ ነገሮች ባይኖሩም ወንጀልንና ወንጀለኛውን በሚመለከት ሰፋ ብሎ ካሰበው በላይ ተዕሹል ። በተለይ በ ''አልዘሀራ'' የረዉፍ ጋዜጣ በዝርዝር በቀስቃሽነት መልክ የእሱን የሌብነት ታሪክ፡ በተከታታይ ያደረጋቸውን ጅብደኝነት ፡ በፍርድ ቤት የተሰጡትን ፍርዶች ፡ የሠረቃቸውን የሀብታም ቤቶችና በአሁኑ ሰዓት ደም ማፍሰሱ በጋዜጣው ላይ በታላላቅ ጥቁር ፊደሎች የተፃፉ አርእስቶች ሆነዋል ። ለመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ሌላ ወሬ የለም ማለት ነው እልፍ አእላፍ ሰዎች ጋዜጦችን እያነበቡ ስለስዒድ ወንጀል እየተወያዩ ነበሚያ የፈዐሙትውን ክሀደት ያወግዛሉ ። ሰዒድ ይያዛል ይገደላል እያሉ ስለ እሱ ዕድል በሠፊው ይወያያሉ ። እሱ ግን ይጨነቃል ። በፍርሀት አንዳንድ ጊዜም በኩራት ንዴት ደምስሮቹን ሊበጥሳቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ትንሽ የሚቀረው ይመስላል ። በርከት ያሉ ሀሳቦች በአንድ ጊዜ አእምሮውን ያፈናንቁታል ። አንዳንድ ጊዜም ሳይታሰብ ግልፍ ያደርገውና ተአምር የሚፈጥር ይመስለዋል ። በዚህ ውኔታ እያለ የጋዜጦችን ገፆች ማገለባበጥ ጀመረ ። ዓይኖቹ በድንገት የሰናእን ፎቶ አተኩረው አስተዋሉ ። አውሬ የሚመስለውን የራሱንም ፎቶ ተመለከተ ። ነበሚያም የለየላት ሽርሙጣ ትመስለለች ። ፈገግ ወዳለችው ወደ ሰናእ ተመልሶ በትዝታ ማስተዋል ጀመረ ። ፈገግ ስትል አበት ማስደሰቷ ስለገዳዩ ምንነት ምንም ስለማታውቅ ነው ። ባለው ኃይልና ፍላጎት ተመሰከታት ። በዚህ ላይ አንድ ስሜት እንደ ዱብ እዳ መጣበት ። ምንም ማድረግ አይቻልም ከመስኮቱ በኋላ የተኙ ሰዎች እነሱ ብቻ ናቸው ንፁህ አየር የሚተነፍሱት ። ተስፋ በመቁረጥ ምን አለበት አሁን ሰናእን ይዞ ወደ ውጭ ቢኮበልል ግንም ወደማያውቀው ቦታ ወይም ከስቅላት በፊት ለማየት እንዲፈቀድልኝ ብሎ ምኞቱን ቢጠይቅ ። በዚህ ሀሳብ እንደተዋጠ ወደ ሶፋው ሄዶ ኑር ከምትሰራበት ቁርጥራጭ ጨርቅ ወደ ተከመረበት እጁን ገባ አድርጐ መቀስ አውጥቶ የሰናእን ፎቶ ከጋዜጣው በጥንቃቄ ቆረጠ ። ኑር ከመታጠቢያ ቤት ተመልሳ ስትመጣ መንፈሱን በማረጋጋት ላይ ነበር ። ከመኝታ ክፍል ሆና ጠራችው ። እሱም እየተገረመ እንዴት ሳታውቀው ይህን ሁሉ መሬ አመጣችልኝ እያለ ወደዚያው አመራ ። ያዘጋጀችውም ግብዣ በጣም ሰፊ እጅን የሚያስቆረጥም ነበር ። ብዙ ገንዘብ ወጪ ሳታደርግ አልቀረችም ። እሱ ከሶፋው በምግብና

t.me/OLDBOOKSPDF

መጠጥ ከተሞላው ጠረጴዛ ከኑር ፊት ለፊት ተቀመጠ ። የሚያስገመጅውን ምግብ እየተመለከተ እሷን ለማስደሰት ሲል የረጠበውን ፀጉሯን ዳሰሰው''

''አንቺን የምትወጂር ሴት በዚህ ዓለም ትኖር ይሆን?'' አለ ።

''እሷም ፈገግ እያለች ፀጉሯን በቀይ ሻሽ ሸብ በማድረግ መጠጡን በብርጭቆዎች እየቀዳች ሰሚድን በቁጥጥሯ ስር በማዋል እየተደሰተች ለአጭር ጊዜም ይሁን እንዲደሰት ታደርገዋለች ። ቀላ ያለውን ቆዳዋን በግልፅ እያሳየች ልክ እንደ ጥሩ ምግብ ትኩስ መስላ ትታያለች ።

''አንተም እንደዚህ ያለ አንጋገር ትችላለህ እንዴ?'' አለችው በማፌዝ መልክ

''አንዳንድ ጊዜ እኮ ፖሊሶቹ ከአንተ የተሻለ ርህራሄ የሚያውቁ ይመስለኛል''

''እኔ አንቺን በማግኘቴ እጅግ ደስተኛ ነኝ''

''እውነት ነው?''

''አዎ እውነት ነው አንቺ ርህሩህ ነሽ ፍቅርሽ አይቻልም''

''በፊትም እንደዚህ ነበርኩ ማለት ነው?''

''በዚያን ጊዜ የፍቅር ሰው አልነበርኩም''

''አሁንስ''

''አሁንማ እንጠጣ እንደሰት'' አለ ብርጭቆውን በማንሳት ።

ምግቡንም ሆነ መጠጡን በስሜት እየበሉ ሳለ እንዲህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስትል ጠየቀችው "እንዴት በዚህ ቤት ጊዜህን አሳለፍህ?"

"በጨለማና በመቃብሮች መካከል ነዋ ለመሆኑ ከዚህ መቃብር የተቀበሩ ዘመዶች አሉሽ? ብሎ ጠየቃት ቁራሽ ስጋ በእጁ ይዞ ለመብላት እያለ ።

"የእኔ ዘመዶች በሙሉ ነፍሳቸውን ይማር በሌኒያ በሚባል መቃብር ነው የተቀበሩት" ላፍታ ያህል ዝምታ ሰፈነ። የሚሰማው ድምፅ የሰዓሮች ፡ የብርሌቆዎችና የስኒ ዎች ቻቻታ ብቻ ነበር ። በዚህ ጊዜ ሰዓድ "ለአንድ የመኰንን ሙሉ ልብስ የሚሆን ጨርቅ እንድትገዝልኝ በፍቅር እጠይቅሻለሁ?" አላት ።

"የመኮንን?"

"አታውቂም እንዴ በወህኒ ቤት ሳለሁኝ የልብስ ስፌት ተምሬአለሁ?"

"ግን ምን ሊያደርግልህ?" አለችው በመጨነቅ ።

"ወታደራዊ ማዕታ አለብኝ"

"እኔ እኮ እንደገና እንዳጣህ አልፈልግም?"

"ፈፅሞ ስጋት አይግባሽ" አለ በከፍተኛ በራስ መተማመን "ባለፈው እኮ ሰዎች ለፖሊስ ባያጠቁመብኝ ኖሮ በምንም ዓይነት አልያዝም ነበር" ኑር በሞንቀት ተነፈሰች።

"ወደ ሥራሽ ስትሄጂም ሆነ ከሥራሽ ስትመለሺ አንቺንም ቢሆን እኮ አደጋ ሊያጋጥምሽ ይችላል ። አይችልም እንዴ?" ሲል ጠየቃት ጉንጩ በምግብ ተወጥሮ ። ሁለቱም ተሳሳቁና ኑር ወደ እርሱ ዘንበል በማለት ከርዳድ ያሉ ከንፈሮቹን ላመች።

t.me/OLDBOOKSPDF

“በእውነቱ ከሆነ ለመኖር ከፈለግን ፍርሀት የሚሉትን ጨርሰን ማስወገድ አለብን” አለች ኑር ቀና ብላ ።

“ምንም ቢሆን?” አለ ሰዒድ ራሱን ወደ መስኮት በማድረግ

“ስለሞት አታንሳ ይሰውረን!”

“ከምወደው ጋር ስሆን ሞትን ፈፅሜ እረሳለሁ” አለ በደንብ ቢስነት ሰዒድ በኑር ጥንካሬና በፍቅሯ በመገረም ከልብ አመሰገናት ። በዚሁ ጊዜ አንዲት የእሳት ራት መብረቱን ደጋግማ እየሠረች ለመጣም ስትቀበዘበዝ ትክ ብሎ ተመለከታት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

—11—

ከእኛ አካባቢ ያለው የመታጠቢያ ቤታ እንደም ቀን እንግዶችን ሳያስተናግድ የዋለበት ቀን የለም ። አንተም ምንም ሌላ ዓላማ ስለሌለህ በመስኩ አፈልግህ የማያቋርጠውን የሞት እንቅስቃሴ ታስተውላለህ ። በውነቱ ከሆነ በጣም የሚያሳዝኑት የሞቱት ሰዎች ሳይሆኑ ቀባሪዎች ናቸው ። እያለቀሱ ይመጣሉ ። ሲመለሱም እንባቸውን እየጠራረጉ እየተወያዩ ይመለሳሉ ። ከሞት በላይ የሆነ ኃይል ነው በዚህ ዓለም እንዲኖሩ የሚያስገድዳቸው ።

አባትህ ዓም ማሀራንም የዋሀ የተማሪዎች ሆስቴል በበኃ የንበሩት በመካከለኛ ዕድሜያቸው በዚህ ሁኔታ ተቀብረዋል ። ከባድ የህይወት ዘመናቸውን በሥራ ፡ በእምነት ፡ በደስታና በረካታ አሳልፈዋል ። እንተም ብትሆን ገና ከህፃንነትህ ጀምረህ ነው አባትህን በሥራ የረዳሀቸው ። ይህ ሆኖ ሳለ በተሰበሰብህ ምንም በድህነት ቢቆረመዱም ቅለ· ከቀኑ መጨረሻ በእንድ ላይ በመሆን በፎቱ ምድር ቤት መግቢያ በኩል ተሰብስባችሁ ትደሰቱ ትጫወቱ ነበር ። ዓም ማሀራንና ባለቤታቸው ለብቻቸው ሲወያዩ አንተ ልጃቸው ይግም ለብቻህ ትጫወት ነበር ። ዓም ማሀራን በእግዚአብሄር

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚያምኑ ከፍ ያለ እርካታ ከማግኘታቸውም በላይ ተማሪዎ
ቹም ያከብሯቸው ነበር ። የሳቸው ብቸኛ መዝናኛ የሼክ አሊ
ቤትን መጐብኘት ነበር ። አንተም በሳቸው ምክንያት
የሼኩን ቤት ለማወቅ ቻልክ ።

“ስዒድ ና ከእኔ ጋር ። ከዚህ ከምትጫወትበት መስክ
የበለጠ ላሳይህ ። ጣፋጭ ህይወትን ከምርታት ጋር ከመቅሰም
ህም በላይ የሰላምና የእርካታን ስሜት በልብህ ይቀርፃል ።
ይህም ለዓለማችን ትልቅ ግኝት ነው” ይለህ ነበር ።

ሼኩም በዚያ በብሩህና ርህሩህ በሆነው ፊታቸው ፈገግ
እያሉ ይቀበሉህ ነበር ። አንተም በነፋስ ክብ መሳይ ጢማ
ቸው ትደሰት ነበር ።

“አንድ ቀን ስለሱ ያጫወትከኝ ልጅ ይህ ነው?” አሉ
ለአባትህ ።

“ብልህ ለመሆኑ ዓይኖቹ ያመሰክራሉ ። ልቡም
እንዳንተ ልብ ንፁህ ነው ። የአላህን ትእዛዝ የሚፈፅም ሀቀኛ
ደግ ሰው እንዲሆን ምኞታችን ነው” አሉ ሼኩ ። እውነት
ነው አንተ ሼኩ አሊን ከልብህ ነው የወደድካቸው ። በብሩህ
ገፅታቸው በፍትር የተሞሉት ዐይኖቻቸው በጣም አድርገው
ማርከውሃል ። እንዲሁም ጣዕመ ዜማዎቹና ውብዋዜዎቹ
በመንፈስህ ሠርፀው ደስታን ፈጥረውልሃል ። ገና ልብህ
የፍትርን ትርጉም ሳያውቅ ዓም ማህፈን ከዕለታት አንድ ቀን
ሼኩን እንዲህ አሏቸው ። “ይህ ልጅ ምን ማድረግ እንዳለበት
አስተምሩልኝ” ሼኩም መልስ ለመስጠት ጐንበስ ብለው
ሰዒድን በመመልከት “እኛ የምንጣረው ከልደት እስከ ሞት

t.me/OLDBOOKSPDF

ድረስ ነው ። ሰዒድ አንተ ያለብህ ራሥህን መጠጣጠር የምትሠራቸውን ሥራዎች ሁሉ ለሰው ልጅ ደኅንት የሚበጅ መሆን አለበት" አሉት ሺኽ ። አንተም ይህን ምክር በትክክል የተጠቀምክበት የሌብነትን ሙያ በያዝክበት ጊዜ ነው ። ምክንያቱም ያገኘኸውን ሁሉ ለብዙ ሰው አካፍለህ ልና። ጊዜም እንደ ህልም እያለፈ መጣ ። የዋሁ ዓም ማህራንም አረፉ ። በድንገት አንተ በማታውቀውና በማይገባህ ሁኔታ ከዚህ ዓለም ተለዩ ። ለሺኽ አሊም ቢሆን አሚሚታቸው ሊገባቸው አልቻለም ። በአባትህ ሞት እንደ ጨት ደንግጠህ ነበር? በዚያን አለት ጧት ራስህን እያወዛወዝክ ፡ ዐይኖችህን በእጅህ እያሻሸህ ፡ እንቅልፍህን ለማስወገድ ትታገል ነበር ። በተማሪዎች ሦስቱል መግቢያ አጠገብ በምትገኘው በዚያች በትንሿ ክፍል ውስጥ እናትህ እየሙሀና እያነበ ነበር ። አንተም ከእንቅልፍህ ተንቀሳቅሰህ ፡ በፍርሀትና ተስፋ በመቁረጥ ምርር ብለህ አለቀስክ ። በዚያን ቀን ከሰዓት በኋላ ረዐፋ በዚያን ጊዜ የህግ ተማሪ ስለነበር የሠራው ሥራ አኩሪ ነበር ። በጣም ሀብታ ማራኪ ሰው ነበር ። አንተም ሺኽ አሊን እንደምትወዳቸው እሱንም ከሳቸው የበለጠ ትወደው ነበር። በእሱም ጥረት ነው በአባትህ ምትክ እንድትሠራ የተደረገው። አንተም ምንም ሀሣን ብትሆን ግዳጅህን በትክክል ተወጥተሃል ።

ምንም ያህል ሳያቆዩም እናትህ አረፉ ። አንተም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው የሞትክው ለማለት ይቻላል ። በእናትህ ሀመም ምክንያት ከፍ ያለ ችግር ደርሶብሃል ። ከዚህ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረውፍን ሳናስታውሰው አናልፍም ። በዚያን ዕለት እናትህ በጠና ታመው ደም በብዛት እየፈሰሳቸው ትልቅና ማራኪ ወደሆነው አስደሳች አፀድ መሀል ወደሚገኘው የአካባቢህ ሳቢር ሆስፒታል ወሰድካቸው ። ሆስፒታሉ ከእናንተ አቅም በላይ የሆነ በአንተ አዕምሮ ፈፅሞ ሊታለም የማይቻል ውብና ውድ ቦታ ነበር ። ቦታውም ራሱ "ይህ ለአንተ አያደለም ርቀህ ሂድ!" የሚል ይመስላል ። ግን ለእናትህ አስቸኳይ ህክምና በጣም አድርጎ ስለሚያስፈልጋቸው ሌላ አማራጭ አልነበረህም ። የታወቁት ሀኪም ከክፍሉ ሲወጡ ሰምቼ ስማቸውን ሲጠሩ ስለሰማህ አንተ በፍጥነት ሮጥ ብለህ ጀለቢያህን እንደለበስክ ፡ ነጠላ ጫማ እንዳደረግህ ፡ "እናቱ! ደም !" ብለህ ጮኸህ ስትነግራቸው ሀኪሙም በመነጥራቸው በንቀት ተመለከቱህ ። እናትህንም ቆሸሸ ያለ ልብስ ለብሰው ከአግዳሚው ወንበር ላይ ተኝተው ሳሉ ተመለከታቸው ። በዚህ ጊዜ አንድ የፈረንጅ ነርስ በዚያ አካባቢ ቆማ ሁኔታውን ትመለከት ነበር ። ሀኪሙም ምንም ዓይነት የህክምና እርዳታ ሳያደርጉ ጥለዋቸው ሄዱ ። በዚህ ጊዜ ነርሷም ወደናንተ ጠጋ ብላ በማታውቀው ቋንቋ አነጋገረችህ። ችግርህን እንደምትካፈልህ ተረዳህ ። አንተም ምንም እንኳ በዕድሜህ ገና ልጅ ብትሆንም ከመጠን በላይ በሆነ ንዴት ተውጠህ ችግሮንና ድህነትን አወገዝክ ። አንድ ወንበርም ወርውረህ ከወለሉ ጋር በማጋጨት ብትንትኑ እንዲወጣ አደረክ ። ከዚያም አንተና እናትህ በሚያሳዝን ውጤት ከሆስፒታሉ ሙሉ በሙሉ ተባረራችሁ ። ከአንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወር በኋላም እናትህ በተሰበረ አሰላንደኑ የነበሰውን ሁሉንም አፈራ ። ከዚህ ዓለም የሚለዩበት ጊዜም ሲቃረብ ሥጋቸን ጭብጥ አድርገው ይዘውህ ነበር ። ነያኖቻቸውም ከአንተ ሊያ እንደራቁ ነበር ።

እናትህ ለአንድ ወር ያህል ታመው በትንሳኤ ጠዋት አንተ ከአንድ ከገጠር የመጣ በሆስቴስ ከሚኖር ከንበረ ተማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰርተህ ስለነበር ተማሪውም አዳን ጓች ምርመራ አከናውኖ መታህ ። ረዐናን በጉዳዩ ገብቶ በሰላማዊ መንገድ እንድትፈታ አደረገ ። ነባ ወጣህ ። በአሥራት ረዐናን በዚያን ጊዜ እውነተኛ ርህራሄና ሰብአዊ ከሙሆኑም በላይ አለታህና አስተማሪህም ነበር ። ሰብቻችሁ ስትሆኑም ረጋ ባለ ድምፅ "አትፈኔነት በዕውነቱ ከሆነ ይህ ያሁኑ ስርቆት በፍፁ አስተያየት ተገቢና ምክንያት ያለው ነው ። ሥጋቸው ማን ይከታተለህ አለ ። ንግግሩን በማያዳግ ጻጭቶም በሆኑ እንደገለጸሽ አያደለም ብለህ ነው? ምንም እንኳን ስርቆት ያበታህ ምክንያቶች ትክክለኛ ቢሆኑም በእነሱ ሰንድ ስትገ ማለት በስርቆት የተመሰደን ንብረት በስርቆት መመለስ አለበት የሚል ዕምነት ሳያጥራቸው ይተራል ብለህ ነውም አለ በማፈገ ።

"እኔ እነ ከዚተሰቦቹ ርቱ በቸማር ፡ በስቃይና በረሃብ ነው የምማረው" ሲል ረዐናን በቁጣ ሥነ ብሎ የተናገረው ያታመለህል ። "ረዐናን እነዚህ መመረያዎችህ የት ያደሰው ያሆን አውን? እንደ አባቱና እናቱ እንዲሁም እንደ ባለቤቱ ዕምነት ሞተው ለሆን ይችላል ። ታስታውስ እንደሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

የ·ማሪዎችን ሆስቱል ት·ሁ ሌላ ሲሳይ የምታገኝበት ሥራ በሌላ ቦታ ፈልግ የሚል ሀሳብ መጣብህ ። በዚሁ ጊዜ በአረንጓዴው መስክ መጨረሻ በምትገኘው አንድ የዘንባባ ዛፍ ሥር ቆም ብለህ ሳለህ ነበሚያ መጣች ። አንተም "እኔን መፍራት የለብሽም ከፍ ያለ ጥቅም የሚያስገኝ ሥራ ለማግኘት መሄዴ ነው ። እንደምወድሽ አትርሺ ። ላረጋግጥልሽ የምፈልገው ነገር ቢኖር አንችን ለማስደሰት በተከበረ ቤትም እንድትኖሪ ለማድረግ እጣጣራለሁ" አልካት ። "አረ እናንተ ቀብሮች ከዚህ ውጭ ጥቅጥቅ ባለው ጨለማ የተሞላችሁ በእኔ ትዝታዎች እንዳታሾፉብኝ አደራ እላለሁ!" ሰዒድ ከተጋደመበት ቀና ብሎ ከሶፋው ላይ ተቀመጠ ። በክፍሉ ጨለማ ሰፍኗል ። በዚህ ጊዜ ረዐፍ እንደሚያየው ሆኖ ተሰማው ። በማፌዝ እንዲህ አለው ።

"አንተ እርኩስ በአንተ ጋዜጣ በአዘጋጅነት ብቀጠር ኖሮ የሁለታችንም ትዝታዎች እንዲወጡ ከማድረጌም ሌላ የለበስከውን ያስመሳይነት ካባ ገልፌ ውስጣዊ ማንነትህን ለማያውቅህ ሁሉ በትክክል አጋልጥ ነበር" አለ ።

"እኔ እስከመቼ ድረስ ነው ከዚህ በጨለማ ታፍኜ የምኖየው? ኑር እንደሃነች ጉህ ከመቅደዱ በፊት አትመጣም። አለ ፌክ ብሎ በመገረም ። በድንገት ሊቋቋመው የማይችል አንድ ኃይል ተሰማው ። በተን ትየ በውድቅት ሌሊት ሽርሽር ወጣ ። በጥንቅቂ ወደ መሳኒዕ ጉዳና አዘገመ። ከዚያ ወደ ገላጣው ቦታ ሄደ ። ከመይበቂያው እየራሳ በሄደ ቁጥር ይበልጥኑ ክትትል እየተጠናከረ የመጣ መሰለው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀይወቱ በስጋትና በውጥረት የተሞላ ስለሆነ አንቅስቃሴው ሁሉ በአካባቢው አየተሽሎከሎከ እንደሚኖሩ አይጠፉና አባቦች ሆነ ። ብቻውን በዚያ ድቅድቅ ባለው ጨለማ ተጓዘ ። የከተማውም መብራቶች ከሩቅ የሚከታተሉት ይመስላሉ ። የመጠጥ ያህል ብቸኝነት አሰከረው ።

ከቡና ቤቱ እንደደረሰም ከታርዛን ጐን ተቀመጠ ። በዚያን ጊዜ በቡና ቤቱ አንድም ሰው አልነበረም ። ከአንድ የኮንትሮባንድ የመጣሪያ ኑጋዴና የቡና ቤቱ ቦይ በስተቀር ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም በኮረብታው ሥር የሰው ሓሜሓታ ሰማ ። የቡና ቤቱ ቦይ አንድ ብርጭቆ ሻይ አመጣለት ። ታርዛንም ወደ እሱ ጠጋ በማለት

"ከአንድ ሌሊት የበለጠ በአንድ ቦታ አትቆይ" አለው በሹክሹክታ ። የመጣሪያ ኮንትሮባንድ ኑጋዴውም "ለምን ወደ ላይኛው ግብፅ አትሄድም? አለው" ምክሩን በመለገስ ።

"እኔ እዚያ የማውቀው ሰው የለኝም" አለ ሰዒድ ጥያቄውን እንዳልተቀበለ ሰው ።

"ታውቃለህ" የኮንትሮባንዱ ሰው ንግግሩን በመቀጠል "እኔ ብዙ ሰዎች በላይኛው ግብፅ ስላንተ በአድናቆት ሲያወሩ ሰምቻለሁ" አለ ።

"ፖሊሶችስ?" አለ ታርዛን በጋለ ድምፅ "በአድናቆት ይመለከቱታል ወይ?" የኮንትሮባንዱ ሰው ካንጀቱ ሳቀ ።

"ፖሊሶችን የሚያስደንቃቸው ምንም ነገር የለም" አለ በመጨረሻ ትንፋሹን ዋጥ ዋጥ እያደረገ ።

"ሰዒድም እውነት ነው ፈፅሞ ምንም የለ" አለ በንገሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

በመስማማት ።

“በጣም የሚገርም ነው ምን ጉዳት ያስከትላል ከሀብታሞች መስረቅ?” አለ የቡና ቤቱ ቦይ በስሜት ። ሰዒድም ለሱ ክብር እንደተዘጋጀ አቀባበል መስሎ ስለታየው በጣም አድርጎ አስደሰተው ። በፊገግታም “የጋዜጦች ምላስ ከመስቀያው ገመድ ይረዝማል ። ፖሊሶች ከጠለፁህ ሀዘቡ ቢወድህ ምን ጥቅም አለው?” አለ ።

“ታርዛን በቅዕበት ብድግ ብሎ በመስኮቱ ግራ ቀኝ ተመልከቶ ተመልሶ መጣና” እኔ እንደሚመስለኝ አንድ ወጉረ ልውጥ ሰው ወደኛ ሲመለከት አየሁ “አለ በድንጋጤ መልክ ። የሰዒድ ዓይኖች አጉርጠው አካባቢውን በአንድ ጊዜ በመስኮቱ በኩል ከዚያም በበሩ በኩል አንጣጥረው ይመለከቱ ጀመር ። ቦዩም ጉዳዩን ለማጣራት ወደ ውጭ ወጣ አለ ።

“አንተ ሁልጊዜ የምታየው የሌለ ነገር ነው” አለ ኮንትሮባንድ ነጋዬው ፊቱን ወደ ታርዛን በማዞር ።

“ዝም በል አፍህን ዝጋ! የመስቀያ ገመድ ቀልድ ፈጠታ መሰለህ!” አለ ታርዛን ቱማ በተሞላበት ድምፅ ።

ሰዒድ ቡና ቤቱን ትቶ ሄደ ። ሽጉጡን በኪሱ ውስጥ በእጁ ይዞ ገላጣ ወደሆነው ቦታ በዚያ በጨለማ ተንዘዘ ። አካባቢውን በጥንቃቄ እየታኘ ግራ ቀኙን እየተመለከተ ፡ የተለያዩ ድምፆችን እየሰማ ፡ ፍርሃትና ብቸኝነት ተጫዋቾት የሚታዩን የመሆኑ ስሜት ይበልጥኑ ከመቼውም ይልቅ በአሁኑ ጊዜ ጮልቶ ተሰማው ። ጠላቶቹንም መናት እንደሌለ

t.me/OLDBOOKSPDF

በት ያምናል ። እነሱም መሞቱን አረጋግጠው ፈላውን ከላዩ በስተቀር አዕምሮአቸው እረፍት እንደማያገኝ ያውቃል ።

ወደ ኑር ቤት አቅራቢያ በነጅመዲን ጐዳና ወደማገኘው ሲጠጋ በመስኮት የመብራት ብርሃን አየ ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከቦና ቤቱ ከወጣ የርካታ መንፈስ ተሰማው ። እፎይም ተንፈታ ነበር ። ትንሽ ለማባበል ብሎ ተጠጋት ። ደሩ ግን ፈቲ እንደሚያመለክተው ከባድ ድካም ተጫጭኗታል ። ዐይኖቿ በርበሬ መስለዋል ። አንድ ችግር እንደደረሰባት ግልፅ ነው ። ከአልጋው ጠርዝ በስተግራ በኩል ተቀመጠ ። "ኑር ምን ነካሽ?"

"ተወኝ ሞቼልሀለሁ" አለች በተበሳጠሰ ድምጿ" ደጋግሞ አስመለሰኝ ከፍተኛ ድካም ይሰማኛል ።"

"መጠጥ እንዳይሆን"

"እድሜ ልክ እንደጠጣሁ ነኝ" አለች ዐይኗቿ እንባ እያንጠባጠቡ ። ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው ኑር ስታለቅስ የሚያያት ፡ በሁኔታውም ተደናግጦ "ታዲያ ምንድነው ምክንያቱ?" አላት ።

"ደበደቡኝ!"

"ፖሊሶቹ?"

"አይደለም አንዳንድ ባለጌ ተማሪዎች ሳይሆኑ አይቀርም ። ሂሳብ ክፈሉ ስላቸው ደበደቡኝ ።

"በይ ፊትሽን ታጠቢና ትንሽ ውሃ ጠጪ" አላት ጥልቅ በሆነ ርህራሄ በተሞላበት ድምፅ ።

"እሺ በኋላ አውን በጣም አድርጐ ደክሞኛል"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ውሾች!" አለ በንዴት ባቲን በፍቅር መልክ እያሻሸ ። እሺም ደከም ባለው ድምጹ

"ለዩኒፎርም ያልከው ፌርቅ ያውልህ ከሶፋው ላያ ባለው ጥቅል ወረቀት ውስጥ!" አለችው ።

ጣቶቿን ወደ ሶፋው በማመልከት ። እሱም በምስጋናና በደስታ ወረቀቱን ከፍቶ ፌርቁን ተመለከተ ።

"ይቅርታ አድርግልኝ ዛሬ ሌሊት ጤናዬ ስለታወከ ላረካህ አልችልም"

"ያንቺ ጥፋት አይደለም ፊትሽን ታጥበሽ ተኚ"

ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ሰፈነ ። በመቃብሩ መግቢያ በኩል ውሻ ፏሽ ። ኮርም በረጂሙ ተነፈሰች ። ድምጹን ከፍ አድርጋ በሀዘን መልክ "የወደፊቱ ዕድልህ እንዳበባ የፊክ ሠላም ፡ ሀብትና አርካታም ታገኛለህ ብላሀለች ።"

"ማናት?" አለ በመገረም ።

"ጠጠር ላያዋ!"

"መቼ ነው ጠንቋዮች እውነት የሚናገሩት?" ሰላምና እርካታ የት አለ?" እኔ ምንም ነገር አልፈልግም ። በሰላም ለመተኛት ፡ እንቅልፌን ፌርሽ በጥሩ ስሜት ለመነሳት ፡ ወጥ ያለ ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ ነው ። ሰባቱን ሰማያት በጥበቡ ሰፈጠረው ይህን ማድረግ ያቅተው ይሆን?" አለ ።

እንዳንተ ያለ ሰው እንደዚህ ያለ ህይወት ሊመኝ ይችላል ። ህይወትህን በሙሉ አሸንዳዎችን በመውጣት ፡ ከጣሪያዎች በመዝለል ፡ ያሳለፍክ ፖሊሶችም አንተን ለማደን ከሠሌማ ሲያባርሩህና ንብህን ሰዎችን በተሳሳተ ጥይቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትጓድል ሰው አይደለሀም ወይ? አለ በሀሳቡ እራሱን እየታዘበ ።

"አንቺ ትንሽ መተኛት አለብሽ" አላት በጣም ቅርጥ ብሎት ።

"እኔ የምጠብቀው የጠወር ጣይዋ ታል እንዲፈፀም ነው ። ያ እሷ ያለችው ቀን ይመጣል ..." አለች ።

"ጣሩም ነው አዎ ይመጣል !" አለ በማሾፍ ።

"አንተ እንደ ሀሳን ነው የምትቆጥረኝ" አለችው በቁጣ።

"አይደለም"

"ያ ያለችው ቀን በእርግጥ ይመጣል!" ሲል መለሰላት።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 12 —

ኑር የወታደሩን ዩኒፎርም ሲለካ በአድናቆት ዓይን ተመለከተችው "እባክህ አስበህ ሥራ ። እንዳጣህ አልፈልግም" አለችው በልመና መልክ ።

"ዩኒፎርም ማሰፋትህ በጣም ጥሩ ሀሳብ ነው" አለ ሰዒድ ራሱን በመስኮት እየተመለከተ ።

የ"ሽለቃነት ማዕረግ ይበቃኝ ይመስለኛል"

ኑርም በትናንትናው ሌሊት ስለ ሰዒድ ታሪክ በዝርዝር ከመስማቷም በላይ እንዲሁም በርከት ያሉ የሱን ፎቶዎች በአንድ ሳምንታዊ መጽሄት ከአንድ በኋ ቤት ደንበኛ አግኝታ መመልከቷን ነገረችው ።

"ሰው ገደልክ! ምን ዓይነት ስቃይ ነው! እንዳትገድል አልተማጸንከህም እንዴ?" አለችው ተስፋ በሚያስቆርጥ አለቃቀስ እያለቀሰች ።

"ይህ የቆየ ግድያ ነው ። እኔና አንቺ ገና ሳንገናኝ የተፈፀመ ነው" አላት በማባበል ።

"አንተኮ አትወደኝም" አለች ዓይኖቿ ወደሩቅ ቦታ እየተመለከቱ ። "ሆኖም ምን አለበት እየተሳሰብን በፍቅር አብረን ብንኖር!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ብወድሽ አይደለም እንዴ አብረን የምንኖረው?"

"ምን ጥቅም አለው ነፍሰ ገዳይ እስከሆንክ ድረስ?" አለች ተስፋ መቁረጧን እያጣናከረች ።

"አይሆሽ አብረን እንሸሻለን" አለ ሰዒድ ባስተማማኝ ድምፅ ።

"ታዲያ ምንድነው የምንጠብቀው?"

"ማዕበሉ ወጥ እስኪል ነዋ!"

"ግን እኔ የሰማሁት ወታደሮቹ የነገሩን ከተማ መግቢያ መውጫ በሙሉ ዘግተዋል ምን ማለታቸው ነው? እንተን የመጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ ማድረጋቸው ነው?" አለች ወለሉን በእግሮቿ እየመታች ።

"ለመሸሽ ስወስን እሸሻለሁ ታያለሽ ። ለዚህ ሁሉ መነሻ የጋዜጦች የምስጢራዊ ጦርነት ነው!" አለ በቁጣና ባልተረጋጋ መንፈስ የኑርን ጠባር በእጁ ያዝ አድርጎ ።

"ሰዒድ ማሀራን! ማለት ማን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ጋዜጦች በሙሉ ስለእሱ ነው የሚያወሩት ። አንቺ ግን ንቀሽዋል ። ስሚ አብረን ለዘላለም እንኖራለን ። የጠጠር ጣይዋ ትንቢትም ይፈፀማል!"

በማግስቱ ብቸኝነት ስላጠቃውና አዳዲስ መሬዎችን ለመፈለግ ሲል ወደ ታርዛን ቡና ቤት አመራ ። ታርዛንም በሩቅ ሲመጣ ስለተመለከተው በፍጥነት ወደ እሱ ሄደ ራቅ ብሎ ወደበረሃው ወሰደው ።

"ይቅርታ አድርግልኝ የእኔ ቡና ቤትም ቢሆን የሚያስ ተማምን ቦታ አይደለም"

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ እኮ ማዕበል ትንሽ ወጥ ያለ መስሎኝ ነው" አለ ሰዒድ ፊቱን ጠቅር በማድረግ ።

"ምን ማለትህ ነው በጋዜጦች ምክንያት ይብስኑ አሁን ተፋፍሟል ። ተደበቅ ። ከካይሮም ለመውጣት አትሞክር"

"ጋዜጦች ከሰዒድ ማሀፉን ሌላ ርእስ አጡ?" አለ ሰዒድ በቁጣ ።

"ያንተን ያለፈውን የሌብነት ታሪክህን በሰፊው በማውጣት በአካባቢው ያሉትን የመንግሥት መታደሮች በመሰበአንተ ላይ እንዲዘምቱ ቅስቀሳቸውን እያፋፋሙ ነው" ሲለው ሰዒድ በዚህ ጊዜ ለመሄድ ተዘጋጀ ። "ሌላ ቀን በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ከበና በቱ ውሏል አንተ በምትፈል ገው ሰዓት እንድንገናኝ" አለ ታርዛን ። ከዚያም ደህና ሁን ተባብለው ተሰነባበቱ ።

ሰዒድም ብቸኝነትና ሥጋማ መደሰፈነበት መደበቂያው ወደሠነው ወደ ኑር ቤት ተመለሰ ።

"ረፀኑ አንተ ነህ ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሠንከው" አለ ቆጣ ብሎ ።

"ጋዜጦቹ በሙሉ ሚዛኑ እንዳለ ነው የሚቆጠረው ። የአንተ ጋዜጣ (አልሀሀራ) ብቻ ነች ያለፈው ታሪክን እየቦረቦረች ታሰራጭ በተዳደ እንዳያስተን ለመተስተሰ የምትጣጣር ። እኔንም እንደ አንድ ተአምር ሰራ ጀግና በማስመሰል የሚገፈው ዓላማው እኔን ለማስገደል ነው ። ረፀኑ የስትላት ገመድ በእንተ ዙሪያ ሳያገባ ሊተኛልኝ አያችልም ። ሠግም ፡ ፍትህም በልጣንም ከሱ ጋር ነው ያለው አንተም ቢሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለዚሁ ለተበላሸው ተረ ህያውነህ ትርጉም ሊኖረው የሚች
ለው ጠላቶችህን ስትፈልርስ ነው ። ዓለሽ ሀጉው አያታ
ችም ። ረዐፍ ከፍተኛ ጥበቃ በሚያረግለት ቪላ ውስጥ ነው
የሚኖረው። ለህያውነህ ምን ትርጉም አለው ጠላቶችህን
ካልቀጣህ?" የመጣ ቢመጣ ውሾችን መትጣት አለብህ" አለ
ለሰው እንደሚያወራ በጉልህ በሚሰማ ድምፅ ለራሱ ።

"ረዐፍ እስክ ለመሆኑ ንገረኝ እንዴት ጊዜ አንድን
ሰው ወደ አስክሬ ነገር ሊለውጠው ይችላል!? አንተ አብየ
ታዊ ተማሪ ፡ ልዐላንና መሳፍንትን ፡ ደጃዝማቾችን ሚሙር
በተማሪዎች ሆስቱል በግልፅ ስታመግዝ እኔ በዚያን ጊዜ
ከአባቱ እግር ሥር ቆሚ ድምፅህን እሰማ ነበር ። እስካሁን
ድረስ በጆሮዬ ተቀርፆ ይመላለሳል እነዚህ ሰዎች በአንተ
አነጋገር ሌቦች እንደሆኑ ትናገር ነበር ። አንተም ሰፊውን
ህዝብ መስለህ ፡ ጀለቢያ ለብሰህ ፡ ከጓደኞችህ ጋር በከፍለ
ሀገር ለቅስቀሳ ስትሄድ ትዝ ይለኛል ። ድምፅህም በነዚያ
በገበሬዎች ማሳ ውስጥ ያስተጋባ ነበር ። ይህ ነው እኔን አሁን
የሚገርመኝ ። ሼክ ዓለም ቢሆኑ ይህን እንቆቅልሽ ሊፈቱት
አይችሉም ።"

t.me/OLDBOOKSPDF

በአንተ ጥረትም ነው አባቱ ትምህርት ቤት እንድገባ ያደረጉኝ በፈተናም መልካም ውጤት ሳገኝ ከልብ ሳቅህ "አዩ ልጅዎን?" አሉ ካቸው አባቴን "እርስዎ ሊያስተምሩት አልፈለጉም ነበር ። ዓይኖቹን ይመልከቱ ስር ነቀል ለውጠችን የሚያመጣ ልጅ ነው" አልክ ። መፅሀፍን እንድወድ አደረከኝ። ልክ እንደ እኩያህም ታወያየኝ ነበር ። እኔም ደህና አድርገው ከሚያዳምጡህ ሰዎች በዚያ ቦታ ፡ በዘምባባው ዛፍ ሥር ፡ የኔ ፍቅር በበቀለበት ስለ ሰፈው ህዝብ መብት ፡ ሀብት፡ ረሀብ ፡ የተቀደሰ ጦርነትና ትክክለኛ ፍርድ ስትናገር ከአድማጮችህ አንዱ ነበርኩ ። አንተ እስር ቤት ስትገባም ስለ አንተ ያለኝ ግምት እጅግ በጣም ከፍ ያለ ሆነ ። በኋላም እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰርቂ አንተ እንዳዳንከኝ ፡ ክብሬንም እንደመለስክልኝ በሀዘን መልክም እንዲህ እንዳልከኝ አስታውሳለሁ ። "የግል ስርቆት ዋጋ የለውም ። ስርዓት መኖር አለበት!" ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ማንበብና መስረቅን አላቋረጥኩም ። አንተም የሚሰረቁ ሰዎችን ስም ዝርዝር ትሰጠኝ ነበር። እኔም በስርቆት ከበርኩ ። በቸርነትም ለብዙ ሰዎች ገንዘቤን በተንኩ ። ከነዚህም መካከል በጣም የሚያሳዝነው ዓሊ ሽ ነበር ። እውነት ረዐፍ ነው የዚያ ትልቅ ቪላ ባለቤት!" አለ ሰዒድ በተቆጣ ድምፅ በዚያ በጨለማ ።

"ጋዜጦችን በእኔ ላይ ዘመቻቸውን እንዴት ጥለው የምታደርግ በውነት አንተ ረዐፍ ነህ? ሀሊናህንና ያለፈውን ታሪክህን እንደገደልክ ልትገድለኝ ትፈልጋለህ? (ወዮ ውልህ አንተ አባብ) አለ በሀሳቡ ። አንድ ነገር ግን ማወቅ አለብህ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ አንተን ሳልገድል አልሞትም ። አንተ የመጀሪያው ከሀዲ
ነህ ። ስለዚህ እያወቀኝ አላመንህም ያለኝን ሰው ገድዬ
ብገድልስ! ሞኖም ለሀይወቱም ሆነ ለሞቱ ትርጉም እንዲኖ
ረው አንተን መግደል አለብኝ ። በአንተ ላይ የምተኩሰው
የቱላ ጥይት ለመጨረሻ ጊዜ በዚህ ዓለም እጅግ አስከፊ በሆነ
ነገር ላይ የምተኩሰው ጥይት ይሆናል ። በዚህ በመታበር
በታ የተኙት በሙሉ ይደግፉኛል ። የዚህን እንቅስቃሴ ፍቺ
ለሺህ አለ እንተወው ።

የነሀ ስግደት "አዛን" ሲሰማ በፉ ሲከፈት ሰማ ። ኑርም
ምግብ ፡ መጠጥና ጋዜጦችም ይዛ መጣች ። ደስ ያላት
ትመስላለች ። የተናንትናውንም አሳዛኝ ሁኔታዎችን የረሳች
ትመስላለች ። የሷም ሁኔታ የእሱን ተስፋ የመቁረጥ ስሜትና
ድካም አስወገደለት ። እንደገና ሀይወትን ማፍቀር ጀመረ ።
ወደ ተጠበሰው ስጋ ፡ መጠጡና ጋዜጦቹ በስሜት አተኮረ ።
ኑርም ሳም አደረገችው ። ለመጀመሪያ ጊዜም ባለመሰታወ
መሆኗን በማመን እቅፍ አድርጉ ሳማት ። ከእሱ እንዳትለ
ይም ተመኝ ። እንደተለመደውም የመጠጥ ጠርሙስ ከፍታ
አንድ ብርጭቆ ሞላችለት ። ባንድ ጊዜ ፉት አላት ።

"ለምን አልተኛህም ነበር?" አለች ኑር ከድካም የተነሳ
ዐይጋ የመስለውን ፊቱን በመመልከት ። እሱም ጋዜጦችን
በስሜት ይገለባብጥ ስለነበር መልስ አልሰጣትም ።

"በጨለማ መጠበቅ ከባድ ስቃይ ሳይሆን አይቀርም"
አለች ስለ እሱ ሁኔታ ሀዘኔታ እየተሰማት ።

"በውጭ ምን አዲስ ነገር አለ?" አላት ጋዜጦችን

t.me/OLDBOOKSPDF

አጣጥፎ መደ ኮን በማስቀመጥ ።

“እንደተለመደው ነው” አለች ከሰሰ የውስጥ ልብስ በስተቀር ልብሶቿን በማውለቅ ። በዚህ ጊዜ ሰሚድ ላብና ንውደር የተቀላቀለበት ጠረኗ አፍንጫውን መታው ።

“ህዝቡ ስለአንተ እያወራ ነው ። ልክ እንደ አንድ ከመዕሀፍ የሚነበበ የጀግኖች ታሪክ ሳያነብ” ካለች በኋላ ንግግሯን በመቀጠል “በእኛ ላይ ምን ሳያነብ ስውደ እንደሚደርስ ህዝቡ አያረጋም” አለች ።

“አብዛኞቹ ግብፃውያን ሊባን አያፈሩም አያጠፉም” አለ ሰሚድ ትንሽ ሰጋ በእጁ ያለ ለመጉረስ እየተዘጋጀ ። ምግባቸውን በመቀመስ ለጥቂት ደቂቃዎች ዐጥ አሉ ። ሰሚድም ቀጠል አድርጉ “ግን በተራዊሯቸው ውሸቱን ያጠላሉ” አለ በሰም ለበሰ አንጋገር ።

“እኔ ውሸቱን እወጸለሁ” አለች ፈገግ በማለት ጣቶቿን እያወጻጻች። “ነገር ግን አንተ የምትላቸውን ሳያነብ ውሸት አያደለም” አለች ቀጠል አድርጋ ። በየጊዜው አንዳንድ ውሸት ነበሩኝ ። የመጨረሻው አውን በትርቡ ሞተ “በማም አድርገ አወንኩለት አለተሰኩኝ ከዚያ በኋላ ውሻ የሚለት ነገር ደፅሞ አልፈልግም አሉኩ”

“አመንኩሽን ነው ጥቅር ችጣ የሚያመጣ ከሆነ ማሰማደ ነው” አሉት ።

“አንተ እኮ አንን አተረጻጎም ፣ አታደቅረኝም”

“እንዲህ አተበሀ” አለ በመለመን መልክ “አታውም እንደ ነለም በመሰ ሙክኔ የተሞላበት ፍርድ የተሳሰበት

t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑን?”

ኑር አስክትሰክር ድረስ ስለጠጣች ለመቀመጥም አዳገ ታት” ትክክለኛ ስሜ ኑር ሳይሆን ሸለቢያ ነው አለች የቡና ቤት ስሟን ትታ የገጠሩን እያስታወሰች ። ከዚያም አያያዛ ስለልጅነቷ ታሪክ አወራችለት ። በበሲና ቀበሌ በሀየንነቷ በዚያ ቆሻሻ ውሃ በተጠራቀመበት ቦታ ፡ እንዲሁም በወጣት ነቷ ጊዜ ያሳለፈችውን ትዝታ ፡ ከወላጆቿም ሸሽታ መጥፋ ቷን በሙሉ ዘርዝራ ካስረዳች በኋላ “አባቴ የመንደር ጭቃ ሹም ነበሩ” ስትል ገለፀችለት ።

“የጭቃ ሹሙ አገልጋይ ነበሩ ማለትሽ ነው!?” አለ ሰዒድ ።

ፊቷን ጠቆር አድርጋ አስተዋለችው ። እሱም ንግግሩን በመቀጠል “ረሳሽው እንዴ አንቺ ነሽ እኮ ካሁን ቀደም የነገርሽኝ” አላት እሷም ከልቧ ሳቀች ። እኔ እንደዚህ ብዬህ ነበር?”

“አዎ ይህ ነው ረዑፍን ከሃዲ እንዲሆን ያደረገው” አለ።

ዓይኖቿን አፍጥጣ ተመለከተችው ማነው ይህ ረኡፍ የምትለው?”

“እሱን ተይው ፡ በብቸኝነትና በጨለማ የሚኖር ሰው ውሸት መስማት አያስችለውም ሲል መለሰላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 13 —

ከግማሽ ሌሊት በኋላ ደብዘዝ ባለ የጨረቃ ብርሃን ሰዒድ በገላጣው ቦታ በኩል አድርጎ ሄደ ። ከቦና ቤቱ ሊደርስ አንድ መቶ ሜትር ገደማ ሲቀረው ቆም ብሎ ለሶስት ጊዜ ያህል አኻ ጭቶ ጠበቀ ። ጠላቱን ማጥቃት ካልቻለ ማበዱ ስለሆነ ስለዚህ ጉዳይ ምናልባት ታርዛን አዲስ ወሬ እንዳለው ለመጠየቅ ተስፋ አደረገ ።

ታርዛን የጨለማ ማእበል መስሎ መጣ ። ተሳሳሙ ።

“ምን አዲስ ወሬ አለ?” ብሎ ሰዒድ ጠየቀ ።

“በመጨረሻ አንድ ከነሱ ሰዎች መጥቷል”

“ማን?”

“ቢያዛ ነው” አለ ታርዛን እጆቹ የሰዒድን እጆች ጠንከር አድርገው እየጨበጡ ።“ቢያዛ አሁን ከኔ ቦና ቤት ሆኖ እየተገበያየ ነው ።”

“ስለዚህ የእኔ መጠበቅ ዋጋ አልባ ሆኖ አልቀረም ማለት ነው ። ለመሆኑ በየትኛው መንገድ ይሄድ ይመስል ሃል?” በማለት ሰዒድ ጠየቀው ።

“በጅበል መንገድ በኩል ነው የሚሄደው”

“በጣም አድርጌ ነው የማመሰግንህ ጓደኛዬ”

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዒድ ለለምለም ብላ በምታበራው ፈረቃ ብርሃን እየታገዘ በባርቹ ወደ ተከበበው የውሃ ጉድጓዶች ወደሚገኙበት ወይ ይበብ አቅጣጫ በፍጥነት አመራ ። ከዚያም ወደ ተራራው የሚወስደውን መንገድ ይዞ ከተጓዘ በኋላ እስትራቴጂክ የሆነ ቦታ መርጦ ከአንድ ዛፍ ስር ተደብቆ ይጠባበቅ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ንፁህ የሆነ የአየር ሽውታ ስሜቱን ቀሰቀሰው ። አካባቢው በጣም የተሰወረ ቦታ ነው ። ሰዒድም ሽጉጡን ጠንከር አድርጐ ይዟል ። ጠላቶቹን እንዴት አድርጐ እንደሚመታ ያብሰለስላል ። "ሞት የመፈረሻው ለለማዊ ዕረፍት ነው ። መጀመሪያ አሊሽን መግደል" አለ ከፍ ባለ ድምፅ ። ግን ማንም አልሰማውም ። በአየሩ ሰክረው ከሚያንሱ ዛፎች በስተቀር ። ቀጥሎ ረዐፍን መግደል ። ሁለቱን ሰዎች በአንድ ሌሊት መፍጀት ከዚያ በኋላ የመጣ ይምጣ" አለ ሰዒድ በሀሳቡ ።

ፈ በትዕግሥት እየተጠባበቀ ሳለ ብዙ ሳይጠብቅ ጋኔን የሚመስል ነገር በፈለማው ከራቅ ተመለከተ ። ሰውዬው በኮረብታው በኩል ወደ ዛፎቹ ለመምጣት አንድ ሜትር ያህል ሲቀረውም ሰዒድ ከተደበቀበት ተንደርድሮ ወጥቶ ሽጉጡን ከፊቱ ሳይ ደግሞ "ቁም!" አለው ። ጋኔኑ ኮረንቲ እንደያዘው ሰው ቀጥ ብሎ ቆመ ። ሰዒድንም አተኩሮ ተመለከተው ። አንድም ቃል አልተናገረም ሰዒድ እንዲህ አለ።

"በያዛ የት እንደነበርክ ፡ ምን እንዳደረክ ፡ ምን ያህል ገንዘብ እንዳለህ በሚገባ አውቃለሁ" ሰውዬውም ጫን ጫን

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተነፈሰ በኋላ እጁን ቀስ በቀስ በፍርሃት ማንቀሳቀስ ጀመረ "ገንዘቡ የልጅቱ ነው" አለ ። ሰዒድ በጥፊ መታው ። ይብሱኑ ጨለመበት ።

"ገና አላወከኝም ቢያዛ አንተ ውሻ!"

"ማነህ አንተ? ድምፅህን የማውቀው ይመስለኛል ግን አላምንም" አለ ቢያዛ ።

"እኔ ሰዒድ ማህራን ነኝ!" አለ ጮኸ ብሎ ። "እንዳትን ቀሳቀስ! እንቅስቃሴ ማለት ሞት ማለት ነው"

"ልትገድለኝ! ለምን? በሁለታችን መካከል ምንም ዓይነት ጥላቻ የለም" እያለ ወተወተ ። ሰዒድ እጁን ወደ ቢያዛ ደረት በመሰንዘር ትልቅ ቦርሳ አገኘ ። በኃይል መንጭቆ አወጣው ።

"ይህ ብቻ ነው?" አለ ሰዒድ እያጉመተመተ ።

"ይህ የኔ ገንዘብ ነው ጠላትህ አይደለሁም" አለ ቢያዛ በፍርሃት ጮክ ብሎ ።

"ዝም በል እኔ ገና የምፈልገውን አላገኘሁም"

"በሁለታችን መካከል የቆየ ጓደኝነት እንዳለ አትርሳ" አለ ቢያዛ ያለፈውን ለማስታወስ እየሞከረ ።

"ህይወትህን ነፃ ለማውጣት ከፈለክ ዓሊሽ የት እንደ ሚኖር ንገረኝ?" አለው ሽጉጡን በእጁ እያወዛወዘ ።

"እኔም ሆነ ሌላም ሰው ቢሆን ስለእሱ መኖሪያ የሚያውቅ የለም" አለ በማረጋገጥ ።

"ቦታውን ካልጠቆምከኝ በስተቀር እገድልሃለሁ ገንዘብህንም እርግጠኛውን ካልነገርከኝ አልመልስልህም!" ካለ

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ሰዓድ ከበፊተኛው በባሰ አሙታት በጥፊ አርሟለው ።

“እኔ አላውቅም እምልልሀለሁ አላውቅም” አለ በሚያ ሳዝን ድምፅ

“ውሸታም!”

“በምትፈልገው ሁሉ ልማልልህ!”

“እንደ ጨው ሚሚ ማለት ነው?”

“እኔ ምንም አላውቅም ። ማንም ሰው አያውቅም ። አንተ ቤቱን ከጐበኘህ በኋላ ጉዳት እንዳያደርስበት በማሰብ ከክፉሮ ከተማ ውጭ ረውድ አልፊርጅ ወደተባለው ቤታ ሄጄልል ይባላል ።”

“አድራሻውስ”

“ትንሽ ታገሰኝ ባክህ?” ካለ በኋላ ተጠልል አድርጐ “ሽፅባን ሁሴን ከተገደለ በኋላ ቤተሰቦቹንም ጭምር ይዞ ነው የሄደው የት እንደሄደ ለማንም አልተናገረም ። በተፈጠረው አደጋ እሱና ባለቤቱ በጣም አድርገው ተርበትበተው ነበር ። ማንም ሰው ከዚህ የበለጠ የሚያውቅ ያለ አያመስለኝም”

“ቢያዛ! ወየልህ! እውነቱን ተናገር ብሎ ሰዓድ አሁንም አፋጠ ያዘው ።

“እምልልሀለሁ ሀቁን ነው የምናገረው!”

ሰዓድ ለሶስተኛ ጊዜ በጥፊ አጮለው ። በስቃይ መልክ በተበጣጠሰ ድምፅ ቢያዛ ጮኸ ።

“ለምን ትመታኛለህ? እግዜር ካለበት ቦታ ፈልገ ያጥፋው ። እሱ ወንድሜ ነው እንዴ? አባቱ ነው እንዴ? እኔ በሱ ምክንያት ለምንድነው የምሞተው?”

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰዒድ ወደ መጨረሻ ቢያዛን ወደ ማመን አደላ ። ጠላቱንም እንደማያገኝ ተስፋ ወደመቁረጡ ደረሰ ። በነፍስ ግድያ ወንጀል የማይፈለግ ቢሆን ኖሮ ዕድል እስኪያጋጥመው ድረስ ጠላቱን የገባበት ገብቶ ከመግደል አይመለስም ነበር ። ነገር ግን ያቺ አጉል ጥይት ቅስሙን ሰበረችው ።

“አንተ በድለኸኛል!” አለ ቢያዛ የሰዒድን መረጋጋት ከተመለከተ በኋላ ። ምንም መልስ አላገኘም ። “ገንዘቤንስ?” አለ በጥፊ የተቃጠሉትን ጉንጮቹን በእጆቹ እየዳበሰ “እኔ እኮ አንዳችም መጥፎ ነገር አላደረኩም ገንዘቤን መውሰድ የለብህም ። ጓደኝነታችንንም መርሳት የለብህም!” እያለ ለመነው ።

“የዓሊሽ ጓደኛ ነበርክ” አለው ሰዒድ በንቀት መልስ ።

“እውነት ነው ጓደኛውና ሽርክም ነበርኩ ይኸ ማለት ደግሞ ያንተ ጠላት ነኝ ለማለት አይደለም ለተፈፀመው ከሀዲትም እኔ ተጠያቂ አይደለሁም”

“ጠርነቱ አበቃ ሰዒድም ወደኋላ ማፈግፈጉን መረጠ።

“እሺ” አለ ሰዒድ “ትንሽ ገንዘብ ያስፈልገኛል”

“የፈለከውን ያህል ውሰድ” አለ ቢያዛ ።

ሰዒድ “መቶ ብር ብቻ ይበቃኛል” ብሎ መሰደ ። ሰውየውም ነፃ መውጣቱን ማመን እያቃተው በረረ ።

ሰዒድም እንደገና በዚያ በረሃ ብቻውን ቀረ ። ፈጨረቃ ዋም በበለጠ እያበራች ነው ። የዛፎችም ሹክሹክታ ተጠናክሯል ። “ዓሊሽ ከቅጣት ያመለጠ ይመስላል ። ከሀዲቱን ይዞ ከቀሩት ከሀዲዎች ጋር በሰላም ከሚኖሩት ሰዎች አንዱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሦኒል ረዐፍ ህያዉቱ መና እንዳትሠን ፡ዐሸሩ ሳልቆጥ
ዖመጣ ቢመጣ አን፡ን መግደል አለ፡በኻ" በማለት ሰዒድ
ሠላኤሠን አጠናከረ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 14 —

ሰዲድ ከሌሊቱ ልክ በሰባት ሰዓት ወደ ቤቱ ገብቶ የመኰንን ዩኒፎርም ለብሶ እንደገና ወጥቶ ወደ ዓባሲያ ጐዳና ተጓዘ ። በተቻለም መጠን ከመብራቶች እየራቀ አካሄዱን በከፍተኛ ጥንቃቄ እየተቆጣጠረ ረጋ ባለ መንፈስ ነበረ ። ከዚያም ታክሲ በመያዝ ወደ ጀለእ ድልድይ ሄደ ። በመንገዱም በርከት ያሉ የፖሊስ አባሎችን በመጥፎ ዓይን ተመለከተ ። በቀጥታ ጀልባዎች ወደሚቆሙበት ከድልድዩ አጠገብ ወዳለው ቦታ አመራ ። አንድ ትንሽ ጀልባ ለሁለት ሰዓት ተከራየና የረዑፍ ሀንፃ ወደሚገኝበት ወደ ደቡብ አቅጣጫ አመራ ። አየሩም አርኪ ነበር ። ቀዝቀዝ ያለ ንፋስ ይነፍሳል ። ጨረቃዋም በከዋክብቶች በአጌጠውና በጠራው ሰማይ ላይ ብርሃኗን በአባይ ዳርቻ ባሉት ዛፎች ላይ አሳርፋለች ። በዚህ ጊዜ ሰዲድ አዲስ አስገራሚ ጉልበት ተሰማው ። አንድ አስደናቂ ነገርም በቅርቡ እንደሚፈጽም ዕምነት አደረበት ። የዓሊሽ ነፃ መሆን በረዑፍ ላይ ቅጣት ከተወሰደ ሽንፈት አይደለም ብሎ ራሱን አዕናና ። ረዑፍ ማለት ከፍተኛ የክህደት ደረጃ አርማሃው ። ሌሎችም ከሀዲዎች እንደነዓሊ ሽና ነበዊያ ያሉት በሱ ስር ይጠቃለላሉ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“ሂሳቤን ለማጣራት ነው የመጣሁት ረዑፍ” አለ ሰዒድ ጀልባዋን በሃይል በመቅዘፍ “ከፖሊስ በስተቀር ሌላ ማንም ሰው በሁለታችን መካከል ዳኛ ሆኖ ሊፈርደን ቢቆም ከህዝብ ፊት ትምህርት በሰጠሁት ነበር ። ከሀቀኛ ሌቦች በስተቀር ሁሉም ከኔ ጋር ነው ። ይህም ነው ወና አለመሆኔን የሚያዕናናኝ ። እኔ የአንተ መንፈስ ነኝ ። አንተ ግን ከደኸኛል። ለመስረቅ መደራጀት ያስፈልገናል የምትለውና አንተ ድሮ ትዘክራቸው የነበሩትን ብዙ ነገሮች እኔ አሁን እየተረዳኋቸው ነው ። ግን በጣም አድርገሙ የሚያሳዝነው ብዙ ሚሊዮን ህዝብ እየደገፈኝ ሳለ በብቸኝነት አስከፊ ዓለም ውስጥ መኖሬ ነው ። ማንም የሚረዳኝ ሰው የለኝም ። እልም ያለ ጥፋት ነው ። ጥይት የሚያስወግደው አይደለም ። ሆኖም ጥይቷ ትክክል ናት ። በደም የተቀባች አቤቱታ ስለሆነች ሀያውና ሙታንን ከማርካቷም በላይ የመጨረሻ ተስፋቸውን እንዳይቆርጡ ታደርጋለች”

የጀልባዋን አቅጣጫ ወደ ዳርቻው ዘምበል አድርገሙ ወደ ደረቁ መሬት ወጣ ። ይህን ሁሉ ሲያደርግ በእርጋታ በዩሬርሙ በመተማመን ነው ። በእግሩ ትንሽ ሄድ አለ ። መንገዶቹ ግን ጭር ብለው ዝር የሚል ሰውም የለም ። ወደቤቱ ሲቃረብም ምንም ዓይነት ጥበቃ የሚባል ነገርም አላጋጠመውም ። ይህም ሊያስደስተው ችሏል ። በበሩ መግቢያ በኩል ካለ አንድ መብራት በስተቀር ቤቱ በጨለማ የተዋጠ ይመስላል ። ይሽውም የሚያስረዳው የቤቱ ባለቤት ገና ያልገባ መሆኑን ነው ። ለሰዒድም ግልግል ነው ። ህንፃው

t.me/OLDBOOKSPDF

መደሚገኝበት በስተግራ በኩል መዳለው መንገድ ሄደ። ከዚያም ወደ ጂማ ገዳና አመራ ። የአባይን መንገ ዳርጅ ተከትሎ መንገዱን በከፍተኛ ጥንቃቄ እየቃኘ ከአንድ ዛፍ ስር ቆም ብሎ ያጠባበቅ ጀመረ ። ዓይኖቹ አገርጠው ቢቱን ይመለከታሉ ። ትንሽ ሰልቸት ሲለው በጥቁር የተለበደውን የአባይን መንገ ውሃ ያስተውላል ። ዐሳቡም ወደ ረዐፍ ክፀደት ይከንፋል ።

መኪና በመጣ ቁጥር ቁና ቁና እየተነፈሰ በጉጉት ይጠባበቃል ። በመጨረሻም አንድ መኪና በህንፃው በር ፊት ለፊት ቆመች ። ዘበኛውም በሩን እስከ መጨረሻው ከፈተው። ሰዒድም ግድግዳውን ተጠግቶ ከቤቱ በስተግራ ወዳለው ፀጥ ብሎ በመግቢያው ፊት ለፊት ቆመ ። መኪናዋ በገባችለመግባት ስትሞክር በመግቢያ ባለው መብራት በመታገዝ ሽንጡን አውጥቶ ወደ መኪናዋ በር አነጣጠረ ። የመኪናዋ በር ተከፈተ ። ረዐፍ ወጣ ። በዚህ ጊዜ "ረዐፍ!" በማለት ሰዒድ ጮክ ብሎ ተጣራ ። ረዐፍም በድንጋጤ ድምፅ ከየት በኩል እንደመጣ ቀና ሲል በአንዳሩ ከመቅጽበት አንድ ጥይት በአትክልቱ በኩል ሰዒድ ላይ ተተኮሰበት ። ሰዒድም "እኔ ሰዒድ!" በማለት "እንክ ቅመስ!" ብሎ አፀፋውን ተኮሰ።

ሰዒድ ሳያስበው ከሌላ አቅጣጫ ከእሱ ቀድሞ ከአትክልቱ ቦታ የተተኮሰበት ጥይት በጣም አስገረመው ። ጀሮው ንም የበጠሰው መሰለው ። ተደናገጠ ። ጮንበስ ብሎ በተከታታይ የሚተኮሱትን ጥይቶች አሳለፈ ። ሞኖም ቀና

t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎ በፍጥነትና በመረበሽ ተኮሰ ። ከዚያም ሮጥ ብሎ ወደ አባይ ወንዝ ሄደ ። ዝልል ብሎ ከጀልባዋ ገባና ትንሽ ወደ ውሃው ገፋት ። ባለ በሌለው ኃይሉ እየቀዘፈ ወደ ወዲያኛው ማዶ ለመሻገር ሞከረ ። የጥይቶች ድምፅና የሰዎች ጩኸት ተሰማ ። ከወንዙ ዳርቻ በአጭር ጊዜ ውስጥ ደረሰ ። በፍጥነት ዝልል ብሎ መሬት ነካ ። ጀልባዋም በውሃው እየተንሳፈፈች ተዋት ። ሽጉጡን በእጁ በመያዝ ምንም እንኳ ስሜቱ ቢረበሽም በእርጋታና በፀጥታ ወደቀኝ ወደጣሪ ሳያል መሄድ ጀመረ ።

በርከት ያሉ ሰዎች በድልድዩ አካባቢ እየተሯሯጡ ነው። የተለያዩ የሰዎች ጩኸትም ይሰማል ። አንድ የፊሽካ ድምፅ የሌሊቱን ዓየር አናጋችው ። "አንድ ነገር ሳያደርስ ለመጨረሻ ጊዜ መዋጋት አለብኝ" የሚል ሀሳብ ተደቀነበት። ሆኖም አንድ ታክሲ እንዳጋጣሚ በዚያ ስታልፍ አገኘ ፡ ተደሰተና ገብቶ ሲቀመጥ የተሰማው ሀመም ምንም መስሎ አልታየውም ነፃ ከመውጣቱ ጋር ሲያመሳስነው ። ወደ ኑር ክፍል አጐንብሶ እየዳበሰ ደረሰ ። በዚያ በጨለማ ከነዩኒፎርሙ ጋደም አለ ። ህመሙም ይበልጡኑ ተሰማው ። የህመሙን ቦታ አወቀ ። ከጉልበቱ ትንሽ ከፍ ብሎ ነው ። በእጁም ዳሰሰው ። ወፈር ያለ የፊሳሽ መልክ ያለው ነገር መሆኑን ተረዳ ። ይጠዘጥዘውም ጀመር ። ከምን ጋር ተጋጭቶ ይሆን? ጥይት ይሆን? ከግድግዳው በስተጀርባ ቆሞ እያለ ወይም ሲሮጥ ይሆን? በጣቶቹ የቁስሉን ቦታ ዳበሰ ። ህመሙ ተሰማው ። ግን የገባ ጥይት የለም ። ቧጭራው ነው ያለፈችው

t.me/OLDBOOKSPDF

ማለት ነው? ቆም ብሎ በጨለማ ዩኒፎርሙን አውልቆ አስቀመጠ ። የማታ ልብሱን ከሶፋው በመዳበስ ፈልጎ አገኘ። እግሩንም ለመሞከር በእግሩ መንጐራደድ ጀመረ ። አንድ ነገር ታወሰው ። ከዕለታት አንድ ቀን በመሐመድ አሊ ጐዳና አንድ ጥይት ከባቡ ውስጥ ገብታ ምንም ሳይመስለው ጐዳናውን አቋርጦ በደህና መሄዱን ትዝ አለው ። አንተ ተአምር የምትሠራ ሰው ነህ ለመሸሽ ትችላለህ ። ቁስሉን ግን የተፈጨ ቡና ነስንሰህ ካሰርከው ይድናል ዋናው ነገር ግን ረዑፍ ተገድሎ ይሆን? ማነው ከዚያ አትክልት ቦታ ሆኖ ጥይት የተኮሰ? አሳዛኝ የሚሆነው አንድ ሌላ ንፁህ ሰው ገድለህ እንዳይሆን ነው ። ግን ረዑፍ ሳይገደል አይቀርም ። ተኩሰህ አትስትም ። ከአሁን በፊት በልምምድ ጊዜ በዚያ በኮረብታው በስተጀርባ በሚገኘው በረሃ ተመስክሮልሃል ። ለጋዜጦች እንዲህ ስትል ትዕዛላቸውአለህ ። "ለምን ረዑፍን ገደልክ?" ብለህ በዝርዝር የሱን በደሎች ትገልፃለህ ። በዚህ ጊዜ ለህይወትህም አዲስ ትርጉም ታገኛለህ ። ረዑፍን የምትገድል ጥይት የአንተን የጥፋት ስሜት የምትገድል ናት። ዓለም አለ ስነ ምግባር ማግኔት በሌለበት በጠፍር መንሳፈፍ ማለት ነው ። እኔ ምንም የምፈልገው ነገር የለም ። የምመኘውም ነገር ቢኖር ትርጉም ያለው ሞት እንድሞት ነው ።

ኑር በጣም ድካም እየተሰማት ምጣብም መጠጣ ተሸክማ መጣች ። እንደተለመደው ሳም አደረገችው ። ፈገግ ብላም የሱን አጠፌታ ሰላምታ ለመቀበል ስትል ዓይኖቿ ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተንጠለጠለው ሱሪ አተኩረው ተመለከቱ ። የተሸከመችውን ዕቃ ከሶፋ ላይ ወርወር አድርጋ "የምን ደም ነው!" ብላ ጮኸች ።

እሱም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ያየው ። እግሩን ግልጥ አድርጎ አሳያት ። "ቀላል ቁስል ነው ከታከሰ በር ጋር ተጋጭቼ ነው"

"አንተ እኮ አለምክንያት አይደለም ዩኒፎርሙን ለብስህ የሄድከው ። የአንተ ዕብደት መጨረሻ የለውም ። እኔን በሀሳብ ልትገድለኝ ነው!"

"ትንሽ የቡና ዱቄት ቢነሰነስበት ቁስሉ ሊሽር ይችላል እንዲያውም ዐሐይ ከመውጣቷ በፊት" አለ ።

"ነፍሴ ከመውጣቷ በፊት ማለትህ ነው? አንተ እኩሉስ በቀስ እየገደልከኝ ነው ። ኧረ መቼ ነው ይህ ቅዠት የሚበቃው?"

ኑር እየተናደደች በብስጭት ቁስሉ ላይ የቡና ዱቄት ነስንሳ ከምትሰፋቸው ጨርቆች ቁርጥራጭ ፍለጋ አሰረችው። ዕድሏን በማማረር ረጂም ጊዜ አሳለፈች ።

"በቀዝቃዛ ውሃ ገላሽን ብትታጠቢ ይጠቅምሻል" አላት ።

"አንተ የሚጠቅመውንና የሚጐዳውን ለይተህ አታውቅም" እያለች ወደ መታጠቢያ ክፍሉ አመራች ።

እሷ ወደመኝታ ቤቱ እስክትመጣ ድረስ የጠርሙሱን አንድ ሶስተኛ ጠጥቶት ቆየት ።

"ጠጪ እኔ ከዚህ በታ በሰላምና በፀጥታ ነው ያለሁት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የፖሊሶች ዓይን ከዚህ ቦታ አይደርስም" አላት ።

"እኔ በጣም አሳዛኝ ፍጡር ከመሆኔ በላይ ዕድለ ቢስ ነኝ" አለች በውሃ የራሰውን ወጉሯን እያበጠረች ።

"ማነው ስለ ወደፊቱ ዕድል መወሰን የሚችለው?" አለ ምግብ እየበላ ።

"የራሳችን ሥራ ብቻ ነው" ስትል መለሰችለት ።

"በዚህ ዓለም ምንም የተረጋገጠ ነገር የለም ። አንቺ ከእኔ ጋር መሆንሽ ብቻ ነው ይሽውም ካለአንቺ ለመኖር አልችልም"

"አንተም እንደዚህ ያለ አነጋገር ትችላለህ?"

"ከዚህ የበለጠ ማለት እችላለሁ ። እኔን ለመግደል ከሚከታተሉኝ ጥይቶች መካከል እንቺ ብቻ ነሽ አለኝታዬና ገነቴ ።"

ረጂም ትንፋሽ ተነፈሰች ። ከለሊቱ ጋር የምትወያይ ይመስል ነበር ። እሱም ንግግሩን በመቀጠል "አንቺኮ በጣም ጥሩ ሰው ነሽ በዚሁ አጋጣሚ ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ" በማለት አወደሳት ።

"እኔ አሳዛኝ ፍጡር ነኝ አንተ በሰላም እንድትቆይልኝ ነው የምፈልገው"

"ዕድላችን እንዳለ ነው" አለ ።

"ለምን አንሸሽም ፡ አስብበት" አለችው ።

"እም አስብበታለሁ ግን ትንሽ ውሾቹ ዓይናቸውን እስኪጨፍኑ እንቆይ"

"አንተ በማይሊሽነት ባለቤትህናን ሌላውን ሰው ለመግ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደል ትፈልጋለህ ። መግደል ግን አትችልም ፡ እንዲያውም ራስህን ታጠፋለህ”

ከውጭ ምን ያመራል? ስለእኔ”

“አንድ ባለታክሲ ስለአንተ በጋለ ስሜት ያከራከረ ነበር ግን ምን ያደርጋል አለ ንፁህ ምንም ያልሠራውን ሰው ገደለ” አለ ።

ሰዲድክው አለ! የደም ስሮቹ ነዘሩ ። ስታዩን ለመሸፈን መጠጥ ቀድቶ ጠጣ ። እሷንም እንድትጠጣ ጠቆማት ። ብርጭቆውን ከአፉ ስታደርስ

“ሌላስ ምን ሰማሽ” አላት ።

“እኔ ባመሸሁበት ተንቀሳቃሽ መርከብ አንድ ሰው ስለአንተ ሲያወራ ቅመም ነው አዝናኝ ነው ሀዘቡን ከዚህ አሰልቺ ዓለም ያወጣዋል” አለ ።

“አንቺስ ምን መልስ ሰጠሽ?”

“ምንም አላልኩም ። እኔ አንተን እጠብቃለሁ ፡ አንተ ግን ራስህን አትጠብቅም ። አንተ አታፈቅረኝም ፡ እኔ ግን ከሀሳቡቴ የበለጠ አድርጌ ነው የምገምትህ ። ዕድሜዬን ሙሉ ደስታ የሚባል ነገር ከአንተ ጋር ካልሆነ ላገኘው አልችልም ። ጸሩ ምን ይሆናል ከኔ ፍቅር ሞትህን ትመርጣለህ” ካለች በኋላ ብርጭቆውን በእጇ እንደያዘች አለቀሰች ። እሱም በእጁ ጨበጥ አድርጎ “ቃሉ እንደተከበረ ነው” አላት በጀሮዋ በማሽከሸክ ። ቀጥሎም አብረን እንሸሻለን ለዘለዓለምም አብረን እንኖራለን” ሲል አረጋገጠላት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

—15—

አቤት የታላላቅ አርዕስቶችና ቀስቃሽ ፎቶዎች ብዛት! የጋዜጦች ታላላቅ ዜናዎች አርዕስት ሆነሃል ። ለረዑፍ ቃለ—ምልልስ ተደርጐለት እንዲህ ሲለ መልሷል ። "በዚያን ጊዜ እኔ ተማሪ ሳለሁ ሰዒድ ማህራን የሆስቴሉ ዘበኛ ነበር ። በጣም አድርጌ አዝንለት ነበር ። ከእሥር ቤት እንደወጣም እርዳታ ፍለጋ እኔ ዘንድ ሲመጣም አዲስ ህይወት እንዲጀምር በማሰብ የገንዘብ እርዳታ አድርጌለታለሁ ። ነገር ግን በዚያን እለት ሌሊት ለመስረቅ ወደቤቱ ተሽለኽለኩ ገባ ። እኔም አድፍጬው ያዝኩት ። የኃይል ቃል አሰምቼ ካስፈራራሁት በኋላ ሁኔታው ስላሳዘነኝ በነፃ ለቀቅኩት ። ከዚህ ሁሉ በኋላም ሊገድለኝ መጣ!"

ጋዜጦችም ሰዒድን በዕብደት ትልቅ ሰው ለመሆንና የበላይነትም ስሜት እንዳለው በማስመሰል ወነጀሉት ። የባለቤቱ ክህደት አዕምሮውን እንዲስት ስላደረገው ጥይትን እንዳስፈለገው በሰው ላይ ይተኩሳል ። ረዑፍን አልገደለውም ። የሞተው ግን አንድ ምስኪን ዘበኛ ነው ። "ውሸት". አለ ሰዒድ ዜናዎችን እያነበበ ። ድርጊቱን በማውገዝ ነገሩ እየተሳፋፋመ መምጣቱን ተረዳ ። ሰዒድ የት እንዳለ ለሚጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቁም ሰውም ክፍ ያለ የገንዘብ ስጦታ የሚሰጠው በመሆኑን በጋዜጦች ከመስፈሩም በላይ ህዝቡ ትብብር እንዳያደርግለት ጋዜጦቹ በጥብቅ ያሳስባሉ ።

"ወይ ጉድ ዛሬ በአገሪቷ ጋዜጦች ታላቁ ዜና አንተ ነህ! ታላቅ ዜና እንደሆንክም ትቆያለህ ። እስከሞትህ ድረስ። አንተ የፍርሃትና የአድናቆት ቀስቃሽ ስውር ኃይል ሆነሃል። ኑሮ የሰለቸው ሁሉ በደስታ ይመለከትሃል ። ሽንጥህ ግን ከንፁሀን በስተቀር ሌላ ሰው የሚገድል አይመስለኝም ። አንተም ጭምር በዚህ ትሰዋለህ ። ዕብደት ማለት ይህ ነው እንዴ?" አለ በሻከረ ድምፅ ። የሰርከስ ተጫዋች ሳለሀም ቢሆን የአንተ ምኞት ዓለምን ከሥር መሰረቷ ማናጋት ነው ። ታላላቅ ፎቆችን በምትሰርቅበት ጊዜ ጭንቅላትህ ልክ እንደሰከረ ሰው በደስታ ይዋጥ ነበር ። አንተ የምታምንባቸው እሱ ጨርሶ የተዋቸው የረዐፍም ቃላት አንተን ለሞት አፋፍ አደረሱህ ።

ሰዒድ ብቻውን በዚያ በጨለማ ቁጭ ብሎ ነገሮችን ያብሰለስላል ። በጠርሙስ ውስጥ ያለችውን ጭላጭ መጠጥ እስከመጨረሻ ጠብታ ጨለጣት ። በጨለማ እንደለም ብድግ አለ ። የመቃብሮቹ ርጭታ ተጫነው ። ጭንቅላቱ ቀስ በቀስ ይዞር ጀመር ። ችግሮችን ለማሸነፍ የሚታገልና ለሞትም ደንታ ያለው አይመስልም ።

"ዓላማዋን የሳተች ጥይት የእለቱ ታላቅ ሰው አደረገችኝ!" አለ ጨለማን እያወያየ ። ወደ መስኩቱ አመራ ። ቧቀዳደው መቃብሮች ላይ የጨረቃ ብርሃን አርፎባቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ሙታን በሰላም መተኛታቸውን አስተዋለ ። በዚህ ጊዜ ዳኞች ተቀምጠው የሱን ጉዳይ የሚሰሙ መስሎ ስለተሰማው "እረ እናንተ ዳኞች የኔን ጉዳይ በጥሞና ስሙ ። እኔ ራሴን በራሴ ለመከላከል ነው የምፈልገው" ሲል ተናገረ ።

ዓየሩ ይወብቅ ስነበረና ሰውነቱም በመጠጥ ስለተታጠለ ወደ ክፍሉ ገባ ብሎ የለበሰውን ቢጀም አወለቀ ። በጨርቅ የታሠረው ቁስሉም ትንሽ የህመም ስሜት ቢሰማውም በመዳን ላይ እንደሆነ ተሰማው "እኔኮ ከዚህ በፊት ከናንተ ዘንድ ተከሰው እንደቀረቡት እንደሌሎች ሰዎች ዓይነት አይደለሁም" አለ ጨለማን አፍጥጦ በመመልከት ። "በእኔና በእናንተ መሀከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም ። እኔ ከዚህ ተከሰሼ ከክብ ሳጥን ውስጥ መቆሜና እናንተም ለፍርድ ተሰይማችሁ መቀመጣችሁ ብቻ ነው ። በእኛ መሀከል የጐላ ልዩነት የለም ። ግን ከሁሉ የሚገርመው የእኔ አስተማሪ የሆነው ረዐፍ አስጊ ሰው ከመሆኑም በላይ የመጨረሻው እርኩስ ነው ። ይህም በርግጥ ሊያስገርማችሁ ይችል ይሆናል ። ስዚሁ በምሳሌነት ላስረዳችሁ ። ኤሌክትሪክን የሚያስተላልፈው ሽቦ በዝንቦችና በወፎች ኩስ የቆሸሸ ሊሆን አይችልም?

ወደ ሶፋው ዘምበል ብሎ ተቀመጠ ። ከሩቅ የውሻ ዋይታ ሰማ ። ግን እንዴት በዳኞች ላይ እምነት ሊኖርህ ይችላል? በአንተና በነሱ መሀከል የግል ጠብ አለ ። ስለ ጠቅላላው የህዝብ ጥቅም የሚባለው ነገር ዋጋ አይሰጠውም ። የርኩሱ ዘመዶች ናቸው ። ከአንተና ከነሱ መሀከል የመኖ

t.me/OLDBOOKSPDF

አመት ያህል ትልቅ ልዩነት አለ ። አንተ የምትፈልገው ትክክለኛውን ፍርድ ነው ። ከሀያት በድብብቆሽ ትክክለኛ ፍርድን ሳታገኝ እንዳትቀር ነው ።" ክለ በኋላ በሆዱ "እኔ ዘበኛ አልገደልኩም የማላውቀውና የማያውቅኝን ሰው እንዴት እገድላለሁ?" የረዐፍ ዘበኛ የተገደለው በቀላሉ አንጋገር የረዐፍ ዘበኛ ስለሆነ ብቻ ነው ። ትናንትም መንፈስ ወዲያ መጥታ ገመገችኝ ። እኔም በሀፍረት የምገባበትና የምደርስ በት ጠፋብኝ ተሸማቀቅሁኝ ። ግን እንዲህ ስትል ነገረችኝ ። "በስህተትና አለአንዳች ምክንያት በየጊዜው የሚገደለው ሰው በሚሊዮን የሚቆጠር ነው" አምን እነዚህ ታላት ምንጊዜም ሲንዐባረቁ ይኖራሉ ለእንተም ወንጅለኛ ላለመሠ ንህ አጥጋቢ ምስክሮች ናቸው ። የተናገርከው ም በመሉ ትክክል ነው ። ከዚህም ሌላ ዳኞቹ የእንተን ሥራ ሀጋዊና የተከበሩ ሰዎች ሥራ መሆኑን ከልብ ያምናሉ ። ከዚህ ላይ በማም አድርገው የሚገርመው ግን የእንተን ህይወት በቤሳ ቤስቲን ሲገሙቱ ሞትህን ማን በአሥር ሽህ ብር ይገምታሉ ። በስተግራ በኩል ያለው ዳኛ በዓይኑ ጠቀስ አድርጎ አይህህ በርታ ይልህል ። እኔ ምንጊዜም ቢሆን የረዐፍን ሞት ነው የምመኝ ። በስቅላት ከመሞትህ በፊትም የመጨረሻው ፍላጐትህ ምንድነው? ብለው ቢጠይቁኝ ልጇን ከማየቱ የምሰጠው መልስ የረዐፍን ሞት ለማየት ነው ። ለህይወቱ ፍፃሜ ስንት ቀን እንደቀረኝ አላውቅም" ። በመታደን ላይ ያለ ሰው ምን እንደሚደርስበት ስለማያውቅ እንደ ድንገተኛ ጐርፍ ዕድሉን መጠበቅ ብቻ ነው ። በአንተ ላይ የሚሰጠው

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍርድ ሰናእ አንተን እምቢ ብላ ከመራቂ የባሰ አይሆንም ። የስትላት ፍርድ ሳይፈረድብህ እርሷ ነች የገደለችህ ። የብዙ ሚሊዮን ህዝብ ድጋፍም ዋጋ ያለው አይደለም ። እንደሞት የማይንቀሳቀስ ነው ። ለምንድነው ለሽንጡ ይቅርታ የማያደርግለት በእሱ አይደለም እንዴ የሚያምኑት?" እኔን የሚገድል በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን እንደገደለ ነው የሚቆጠረው ። እኔ የፈሪዎች ምኞት ተስፋና ቤዛ ነኝ ። እኔ አርአያና ማስተማሪያ ነኝ ። እኔን ፅብድ ነህ ማለት ሌሎችንም እኔን የሚደግፉትን በሙሉ ስለሚመለከት ይህን ጉዳይ አጣርታችሁ ካወቃችሁ በኋላ የሚስማማችሁን ደስ የሚላችሁን ፍርድ ስጡ ።

ጭንቅላቱ ይበልጥ ሠረበት ። ከዚያም የዳኞችን ፍርድ ሰማ ። በጣም አድርገው አደነቁት ። ትልቅ ሰው መሆኑንም አላንዳች ጥርጣሬ አመኑ ። የሰውነቱ ታላቅነት ከሞት በኋላም ቢሆን እንደተጠበቀ ነው ። እንቅልፍ ሸለብ አድርጐት ነበር። ግን እንዴት እንደሆነ አያውቅም ፡ ሊያውቅም አልቻለም ። ከፍሉ ውስጥ ብርሃን ገብቶ አጥለቀለቀው ። ከእንቅልፉም እንዲነሳ ስላደረገው ዓይኖቹን ገለጥ ሲያደርጋቸው ኑር ቅም ብላ በጣም በተዳከመ አይኖቿ ስትመለከተው አየ ።

የታችኛው ከንፈሯን ጥላዋለች ። ጀርባዋም ተስፋ በመቁረጥ የጐበጠ ይመስላል ። በእርግጥ የተስፋ መቁረጥና የጥፋት ሀውልት ትመስል ነበር ። ለእሱም ነገሩ ወዲያውኑ ገባው ። በመጨረሻ የፈፀመው ወንጀል ነው እንዲህ አድርጐ ያስደነገጣት ፡ ትንፋሿም እንዲጠፋ ያደረገው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ ከማስበው በላይ ክፉ ሰው ነህ ። በሰውነቱ ልረዳህ አልችልም ። በእግዚር ይሁንብህ እዘንልኝ ግደለኝ!" አለችው። ከሶፋው ተመቻችቶ ተቀመጠ ። መልስ ግን አልሰጣትም "አንተ የምታስበው እንዴት አድርገህ ለመሸሽ ሳይሆን ለመግደል ነው ። ለአንተም መገደል አይቀርልህም" ካለች በኋላ "ምን ማለትህ ነው ጌዳናዎችን ያጥለቀለቁትን የመንግሥት ወታደሮችን ለማሸነፍ የምትችል ይመስልሃል?"

"ተቀመጪ ነገሩን በርጋታ እንወያይበት"

"እርጋታ ከየት ይመጣል? ስለምንስ ነው የምንወያየው? ሁሉ ነገር አልቋል ። እዘንልኝ ብትገድለኝ ነው የሚሻለኝ!"

"አንቺን ምንም ዓይነት ጉዳት እንዲደርስብሽ አልፈቅድም" አለ ረጋ ብሎ ለስለስ ባለ ድምፅ ።

"እኔ አንተ የምትለውን ነገር አልቀበልም ለምንድነው ዘበኞችን የምትገድለው?"

"እባክሽ እሱን ለመግደል አስቤ አይደለም" አለ በቁጣ።

"ሌላው ማነው? ይህ ረዐፍ የምትለው ምን ግንኙነት አላችሁ? ከአንተ ባለቤት ጋር ግንኙነት ነበረው ማለት ነው?"

"የሚያስቅ ሀሳብ ነው! ሌላ ምክንያት አለ ። እሱም ከሀዲ ነው ። የእሱ ክህደት ሌላ ዓይነት ነው" ካለ በኋላ ደረቅ ሳቅ ሳቀ ።

"እኔ የአንተ ነገር ምንም ሊገባኝ አልቻለም የኔም

t.me/OLDBOOKSPDF

ስቃይ የሚያበቃው ስሞት ብቻ ነው” አለችው በንዴት ።

“ባክሽ ተቀመጪ በርጋታ እንነጋገርበት”

“አንተኮ ያቺን ከሃዲ ባለቤትህን እንዳፈቀርካት ነህ በዚህ መሀል እኔን ታሰቃያለህ”

“ኑር ባክሽን ስቃዬን አታባብሽብኝ እኔ የመጨረሻ የስቃይ ደረጃ ላይ ነው የደረስኩት” አለ ነገር ዓለሙ እንደጨለመበት ሰው ።

“እሷም የእሱ ስቃይ ስለተሰማትና በዚህ ዓይነት ሁኔታው አይታው ስለማታውቅ ዝም ካለች በኋላ “በህይወቱ ውስጥ ያለ እጅግ በጣም ውድ የሆነ ነገር በሞት አፋፍ ላይ እንደደረሰ ሆኖ ይሰማኛል” በማለት በሀዘን መልክ ነገረች ።

“ይህ የአዕምሮ መረበሽና ከፍርሃት የሚመነጭ ነው ። እንደኔ ያለ ጅብደኛ ችግር አይፈታውም ። ይህንንም አንድ ቀን አሳይሻለሁ ።

“መቼ ነው የምታሳየኝ?” አለች በርጋታ ።

“በቅርቡ አንቺ ከምታስቢው ቀን በፊት” አለ ሰዒድ በከፍተኛ የራስ መተማመን ። ወደሷ ዘምበል ብሎ እጇን ሳብ እያደረገ ፊቱን ከፊቷ ጋር አገጣጠመው ። ከልብ በመነጨ የእውነተኛ ፍቅር ስሜት ሳማት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 16 —

ጐሀ ሊቀድ እየተቃረበ ነው ። ኑር ግን አልተመለሰ ችም። ስለዚህ ሰዒድ እሷን በመጠበቅና በጭንቀት ምክንያት ከባድ ድካም ተሰማው ። የእንቅልፍ እጦትም አዕምሮውን አናወፀው ። በቅፅበትም አንድ መጥፎ ሀሳብ ብልጭ አለበት "በጋዜጦች የወጣውና ለጠቋሚው ሰው ከፍተኛ የገንዘብ ሽልማት ይደረግለታል የሚለው ማስታወቂያ የኑርን ልብ አባብሎት ይሆን ?" አለ ። በዚህ ጊዜ መላ ሰውነቱ በጥርጣሬ ተበከለ ። ከሀደትም እንደ መጥፎ ሽታና አቧራ በንፋስ ኃይል የትም የተበተነ መሰለው ። ከአሁን በፊትም ቢሆን ነበዊያ በኔ ቁጥጥር ሥር ነበረች ። በፍቅሬ ተማርካለች ስል አልነበረም እንዴ ? በአፍላ ፍቅራችን ጊዜያት ካልሆነ በስተቀር በውነቱ ከሆነ አትወጂኝም ነበር ። ኑር ግን እንደማትከዳኝ እተማመና ለሁ ። ለገንዘብ ብላ ለፖሊስ አሳልፋ አትሰጠኝም ። ኑሮ ያስጠላት ፡ ለገንዘብ ብዙ ጉጉት የሌላት ናት ። ዕድሜዋም እየገፋ ስለሚመጣ ከአንድ ሰው ጋር በፍቅር ለመኖር ነው የምትፈልገው" ። ስለዚህ እሷን በመጠርጠሩ የማይፋት ኃጢአት እንደሠራ ሆኖ ተሰማው ። ነገር ግን ኑር መቼ ነው የምትመለሰው ? ረሀብና መጠበቅ በዛ ። ልክ ነበዊያን ድሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዘንባባዋ ሣር ቆሞ ለረጂም ጊዜ ሲጠብቃት እንደነበረው በመጨረሻም ተስፋ ከቆረጠ በኋላ እሷ መምጣቷን ሲያይ ምን ዓይነት ደስታ ይሰማው እንደነበር ! ሰውነቱ በሙሉ በስሜት ተውጦ እንደሰከረ ሰው ወደ ሰባተኛው ሰማይ የተወረወረ መሰለው ። አሁን ግን የዘንባባውን ጊዜ ልታስታውሰው አይገባህም ። በደም ፡ በጥይቶችና በዕብደት ምክንያት ለመጨረሻ ጊዜ ተሰርዟል ። ማሰብ ያለብህ ስለ አሁኑ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብህ ብቻ ነው ። በዚህ ድቅድቅ ብሎ የሚተናነቅ ጨለማ አስከፊና መራራ ስሜት እየተሰማህ ነው። ማነው አሁን ከስቃይ ፡ ከብቸኝነት ጨለማ፡ ረሀብና ጥም የሚያወጣህ ? ኑር እንደሆነ የምትመለስ አትመስልም ?

በመጨረሻ ከእንቅልፉ ሲነሳ ዓይኖቹን ሲከፍት ደማቅ የፀሀይ ብርሃን ክፍሉን አጥለቅልቆት አገኘው ። በመስኮቱ በኩል የገባው ፀሀይ ጨረር የክፍሉን መቀት በጣም አድርጐ ክፍ አደረገው ። በብስጭትና በመርበትበት ከአልጋው ብድግ ብሎ ወደ መኝታ ቤት አመራ ። ምንም ለውጥ የለም ክፍሎቹን ተዘዋውሮ ተመለከተ ። ኑር እንደሆነ አልተመለሰችም ።

የት አድራ ይሆን ? አለ በመገረም ። ለመመለስ የከለከላት ፡ኃይል ምን ይሆን ?" ምን ያህልስ ከዚህ የበቃ አስረኝነት ልቆይ ይሆን ?" ምንም እንኳን በጭንቀት ላይ ቢሆንም ረሀብ እየሞረሞረው ነው ። ስለዚህ ወደ ምግብ ጠረጴዛው ሄዶ ካልታጠበ ሰሀን ቁርስራሽ ቂጣዎችን እንዲ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁም ከአጥንት ጋር የተያያዙ ስጋዎችንና የሰላጣ ቅጠሎችን አገኘ ። እንደ ውሻ አጥንቶችን ቁርጥሞጥም ቂጣዎችንም ጥርግርግ አድርጎ ከበላ በኋላ ስለ ኑር አለመመለስ በአእምሮው ሲያጉላላ ዋለ ።

አንድ ጊዜ ይቀመጣል አንድ ጊዜ ደግሞ ከፍሉን ይዛራል ። ለሱ እንደመገናኛ ሆኖ የተገኘው በመስኮት ቀዳዳ በኩል የመቃብርን ቦታ ማየት ፡ አስከሬኖችን መመልከት ፡ መቃብሮችን አላንዳች ጥቅም መቁጠር ነበር ። ሰዓቱ እየመሸ መጣ ። ኑርም አልመጣችም ። አንድ ምክንያት መኖር አለበት። "ኑር የት ነው ያለሽው ?" አለ በሜንቀት ፡ በንዴትና በረሀብ እየተሰቃየ ። ኑር በችግር ላይ እንደሆነች አይጠራጠርም ። ከችግሯ ተላቃ ካልመጣች በስተቀር ሀይ ወቱ ምን እንደሚመስል ለመገመት ያስቸግራል!

ኩቱው ሳይሰማ ቤቱን ትቶ ወጣ ። ሰዓቱም ከውድቅት ሌሊት በኋላ ነበረ ። በረሃውን ተሻግሮ ወደ ታርዛን በ-ና ቤት ደረሰ ። ከተለመደው ቦታ ቆም ብሎ ሶስት ጊዜ አፏጨ ። ትንሽ ከጠበቀ በኋላ ታርዛን መጣ ፡ ተጨባበጡ ።

"በጣም አድርገህ ተጠንቀቅ ነጭ ለባሾች በየአንዳንዱ ስንዝር ላይ ተሰማርተዋል"

"እባክህ የሚበላ ነገር እፈልጋለሁ !"

"ምን ማለትህ ነው ! እርቦሀል እንዴ ?"

"ደሀና ሠራተኛውን እልከዋለሁ ከሥጋ የተሠራ ምግብ ያመጣልሃል ። ደጋግሚ የምነግርህ ግን በአደገኛ ሁኔታ ላይ ስላለህ ከመደበቂያህ መውጣት የለብህም"

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደምታስታውሰው እኔና አንተ ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጠን ነበር ። የአሁኑ ግን ሌላ ነው ። በመጨረሻ ያደረግኸው ማጥቃት ዓለምን አናውሷል” ።

“ዓለም ምንጊዜም ቢሆን እንደተናወጠች ነች” አለ ሰዓድ ።

“ትልቅ ስህተት ነው የፈፀምከው ትልቅ ሰው ለመግ ደል መሞከርህ !” ካለ በኋላ ትዞት ሄደ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ምግቡ መጣለት ። ከአሸዋማው መሬትም ሙሉ ጨረቃ ልትሆን ትንሽ ከቀራት ሥር ተቀምጦ ምግቡን ላስ አድርጎ በላ ። ከዚያም ሆኖ በታርዛን በና ቤት በኩል በኮረብታው ስር ብርሃን ተመለከተ ። በሀሳቡም የበና ቤቱ ደምበኞች ከክፍል ተቀምጠው ሲጫወቱ ስለሰማ ብቸኝነት እንዳስጠላው ተሰ ማው ። ከሀገሩ መሀል ሲሆን ግዙፍ ሰው የሆነ ይመስለዋል ። ፍትርም ፡ መሬትም ጅግንነትም እንደሚፈልም መስሎ ይታየዋል ። ያህ ካልሆነ ህይወት ምኗ ደስ ይላል ? “ኑር ተመልሳ ይሆን ? እሷ ከሌለች ተፋፊ ብቸኝነት ነው የሚጠብቀኝ ካለ በኋላ ቆም ብሎ ሱሪው ላይ ያለውን አሸራ እያራገፈ ወደ ሜካው አመራ ።

በሰማዕታት መታሰቢያ በስተደቡብ በኩል ባለው መን ገድ አድርጎ ተጓዘ ። ከዚያ ቢያዛን አማኙቱ እንት አድርጎ ከያዘበት ቦታ ሲደርስ ከየት መጡ ሳይባሉ ሁለት አጋንንት መሳይ ብት አለ ። መድሱም ዘለው በሁለት አትጣጫ ከበቡት።

“ባለሀበት ቱም !” አለ አንዱ የገጠር አነጋገር በሚመ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስል ። "መታወቂያህን አሳየን !" አለ ሲላው በመጮህ ።

የመጀመሪያው ከሰዲድ ፊት ላይ ባትሪውን አበራበት ። ሰዲድ በንዴለ ቃል ።

"ለመሆኑ እናንተ እነማን ናችሁ ?"

ሁለቱ ሰዎች በቁጣ አንጋጠሩና በባትሪ ብርሃንም አማካይነት ዩኒፎርሙን ስላዩ ተደናገጡ ።

"ከቡር መኮንን ይቅርታ አድርጉልን በሚኪ ውስጥ እያለ ማንነትዎን ለማወቅ አልቻልንም" አለ አንዱ ፈገክ ብሎ ።

"እሪ ለመሆኑ እናንተ እነማን ናችሁ?" አለ ሰዲድ በድጋሚ በንዴል ቃል ።

"ከዋይሊ ፖሊስ ጣቢያ ነን ጌታዬ" አሉ በፍጥነት ። ምንም እንኳ ባትሪው ቢጠፋም ሁለተኛው መታደር ትክ ብሎ ስላስተዋለው ጥርጣሬ አደረበት ። ሰዲድም ሁኔታው ከቁጥጥር ሥር ሳይወጣ ፈጣን እርምጃ መወሰድ ያለበት መስሎ ስለተሰማው በንዴል ተጠቀመ ። ሁለቱንም ከቦርሳቸው ላይ አከታትሎ በቡጢ መታቸው ። ከዚያም ስትሬቲጂክ ቦታ እየፈለገ ደጋግሞ ከአገጫቸውና ቦርሳቸው ላይ መታቸው ። ወደቁ ። እሱም እግሬ አውጪኝ ብሎ ሸመጠጠ ። በነጅመዲን መንገድ መጠምዘዣ ሲደርስም ቆም ብሎ ሰው የሚከተለው እንደሆነ ለማየት አስተዋለ ። ከዚያም ረጋ ባለ ሁኔታ መንገዱን ቀጥሎ ወደቤቱ አመራ ።

ከክፍሉም ሲገባ ምንም ለውጥ የለም። እንደነበረው ባዶ ነው ። ብቸኝነት አሰልችነት ብስጭትና ኑርን መጠበቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይብሱኑ ተጠናከረው ጠበቱት ። ኮቱንም አውልቆ በጨለማ
ከሶፋው ላይ ዘርፈጥ አለ ። "ኑር የት ነው ያለሽው ?" አለ ከፍ
ባለ አሳዛኝ ድምፅ "በደሀና እንዳልሠንሽ እርግጠኛ ነኝ ።
ፖሊስ ይዞሽ ይሆን ? አንዳንድ እርኩሶች ደብድበውሽ ይሆን?
ያም ሆነ ይህ በደሀና አይደለሽም ። እያለ ተከዘ ። ደሀና
አለመሆኗን ልቡም ሆነ ስሜቱ ያረጋግጡለታል ። ኑርን
እንደገና ለማየት ምንም ዓይነት ዕድል የለውም ። ተስፋ
መቁረጥ ጭንቅ አድርጐ ያዘው ። ከባድ ሀዘንም በድንገት
አጠቃው ። ይህም ሰላማዊ መጠለያውን በቅርቡ ስለሚያጣ
ብቻ ሳይሆን ከልብ የመነጨ ፍቅርና ርህራሄንም ስለሚያጣ
ጭምር ነው ። በዚያ ጨለማም ኑር ፈገግ ብላ በስሜት ፡
በፍቅርና በሀዘን መልክ ሆና ታየችው ። ልቡ ተሰበረ። ለካ
ይሆን ያህል በሰውነቱ ጠልታ ንብታ ነበር ? በመጥፋት ላይ
ላለው ሀይወቱም ዋና አለኝታው እሷ ነበረች ማለት ነው?
ዓይኖቹን በጨለማው ጭጉን አድርጐ የሚወዳት መሆኑን
አመነ ። የሚከፍለውን መስዋእትነት ሁሉ ከፍሎ ወደእሱ
በደሀና ለመመለስ ከቻለች ወደኋላ የማይል መሆኑን አረጋ
ገጠ ። ማንም ሰው በዚህ ዓለም ስለእሷ መጥፋት ቅንጣት
ያህል የሚያስብላት የለም ። በሀዘን ከንፈር የሚመጥላትም
ቢሆን አይገኝም ። በዚህ ዓለም ረዳት የሌላት ሴት ነች ።
ሰናእም ብትሆንም እኮ ከዚህ የተሻለ ዕድል አይገጥማትም ።
ከዕለታት አንድ ቀን ስለሷ የሚያስብ ልብ አይኖርም ። ስሜድ
ከልቡ አዘነ ። ፍርሃት ፍርሃትም አለው ። ተናደደ ። ሽጉጡን
በእጁ ያዘ ፡ በጨለማ ደገነው ። ላልታወቀ ሰው እንደሚያስጠ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነቅቅ ተስፋ በመቁረጥ ጥልቀት ያለው ስቃይ ተሰማው። በቅዠት በጨለማ ውስጥ ተዘፍቆ እያለ ሌሊቱ ሊያበቃ ሲል እንቅልፉ መሰደው ።

ከእንቅልፉም ሲነቃ የቀትር ብርሃን በክፍሉ ገብቷል ። ከእንቅልፉም የተነሳው በሩ ሲንኳኳ በድንጋጤ ብድግ ብሎ ነበር ። ቀስ ብሎ በእግር ጣቶቹ ወደክፍሉ በር ሄደ ። በሩም ይንኳኳል ። የሴት ድምፅ ተሰማ "ወ/ሪ ኑር ! ወ/ሪ ኑር !" የሚል ። "ማናት ሴትየዋ ምንስ ትፈልጋለች?" ወደክፍሉ ሄዶ ለጥንቃቄ ያህል ሽጉጡን ይዞ ተመለሰ "ወጥ ይሆናል" አለ አንድ የወንድ ድምፅ።

"በዚህ ሰዓት ምንጊዜም አትጠፋም ነበር ። ከአሁን በፊት የቤት ኪራይ ሳትከፍል እንዳሁኑ ዘግይታ አታውቅም" አለች ።

"የቤቱ ባለቤት መሆኗ ነው" አለ ሰዒድ እሷም በቁጣ ለመጨረሻ ጊዜ በሩን በኃይል አንኳኩታ "ወሩ ከገባ ዛሬ አምስት ቀኑ ነው ከዚህ የበለጠ አልታገሳትም !" ብላ እሷና ሰውዬው የዛቻና የማስፈራሪያ ቃላትን እየተለዋወጡ ተመልሰው ሄዱ ።

ሰዒድ በዚህ ጊዜ ሁኔታዎች እንደ ፖሊስ እየተከታተሉት መሆናቸውን አመነ ። ሴትየዋ አልታገስም ብላለች። ከፍሉን በሆነ ነገር በርግዳ ልትገባ ትችላለች ። ስለዚህ የተሻለ ነገር ቢኖር ክፍሉን ትቶ በተቻለ መጠን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሌላ ቦታ መሄድ ነው ። ግን ወዴት ነው የሚኬደው ?

t.me/OLDBOOKSPDF

— 17 —

ከሰዓት በኋላም የቤቱ ባለቤት እንደገና መጥታ በሩን አንኳኳች ። ቀጥሎም ፀሐይ ልትጠልቅ ስትል መጥታ ማንኳኳቷን ቀጠለች ።

"ወ/ሪ ኑር ! ወ/ሪ ኑር ! ይህ ጥሩ አይደለም ለማንኛውም ነገር መጨረሻ አለው" እያለች በዛች ተመልሳ ሄደች ።

ሰዒድ እኩለ ሌሊት ሲሆን ሹልክልክ ብሎ ከቤቱ ወጣ። በማንኛውም ነገር ዕምነት አልነበረውም። ራሱን በመቆጣጠር በተቻለ መጠን አረማመዱን አስተካክሎ በዝግታና በርጋታ መሄድ ጀመረ ። መንገደኞችም ሆኑ በየመንገዱ ዳርቻ የቆሙ ሰዎች ነጭ ለባሾች ሳይሆኑ አይቀርም የሚል ጥርጣሬ ስላደረበት ሽጉጡን በጥንቃቄ ይዞ የመጨረሻ ቀቢፀ ተስፋ ፍልሚያ ለመግጠም ዝግጁ ነበር ። ሆኖም ባለፈው ምሽት ከፖሊሶች ጋር ባደረገው ግጭት ምክንያት የታርዛን ቡና ቤት አካባቢ እንደሚከበብ ስለሚያውቅ ረሀብ እየሞረሞረው ወደ ጅበል መንገድ አመራ ። በመጨረሻም ወደ ሼኩ ቤት መሄዱን ወሰነ ። ሌላ የተሻለ መጠለያና ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚያስችለው እስኪያገኝ ድረስ በምሽት የበለጠ ጭርታ ወደሰፈነበት የሼኩ ቤት ተሸለኩኩ ደረሰ ። የሚሊቱሪውን ዩኒፎርም ቤት በመረሳቱ ግን በጣም ተናደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ፡ ሦስም ወደ ሼክ ክፍል አመራ ።

"ሼኽ፡ንም በፋኖስ ብርሃን ተመለከታቸው ። ከዚያው ከተነጠፈው ስጋጃው ላይ ተቀምጠው ያነበንባሉ ። አሰም መፅሀፉ ወዳስቀመጠበት ግድግዳ ተጠጋ ፡ ቁጭ አለ ። እጅግ በጣም አድርጉ ደክሞታል ሼኽም ማነብነባቸውን ተጠሉ ።

"ጊታዬ እንደምን አምሽተዋል ?" አለ ። ሼኽም ወለታቸውን ሳያቋርጡ እጃቸውን አንስተው ወደ ጭንቅላታቸው አደረጉ ። ለሰላምታው አፀፋውን መመለሳቸው ነው ።

"ጊታዬ እርቦኛል"

ሼኽ ወለታቸውን ሳያቋርጡ አተኩረው ተመለከቱት ። አግጫቸውንም በማወዛወዝ ወደ ጠረጴዛው አትጣጫ አመለከቱት ። ከዚያም የተቆራረሰ ዳቦዎችና የበለስ ፍሬ አገኘ ። በአንድ ጊዜ ጥርግ አድርጎ ከበላ በኋላ ሼኽን አተኩሮ ይመለከታቸው ጀመር ። እንዳልጠገበም ያስታውቅ ነበር ።

"ገንዘብ የለህም ማለት ነው?" አሉት ሼኽ በመገረም ።

"አለኝ"

"ሂድና የሚበላ ነገር ግዛ"

መልስ ሳይሰጣቸው ወደ ማረፊያው በዝምታ አመራ ። ሼኽም ትኩር ብለው ተመለከቱት ። "መቼ ይሆን ዕረፍት የምታገኘው ?" አሉት ።

"በዚህ ዓለም አይደለም"

"ለዚህ ነዋ ገንዘብ ይዘህ የምትራበው"

"አዎን"

"እኔ በአሁኑ ጊዜ ልቤ በደስታ ተውጦ አላህን የሚያሞግስ ግጥም እያጋግም ነበር" አሉ ሼኽ ።

"እርስዎኮ የታደሉ ሼኽ ነዎት ። "እርኩሶቹ በሙሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሽሹ እንዴት እረጥት አገኛለሁ” አለ ሰዒድ ።

“ቁጥራቸው ስንት ነው?”

“ሶስት ናቸው” ሲል መለሰ ።

“ዓለም ሰላም ነች ማለት ነዋ እርኩሶቹ ሶስት ብቻ ከሆኑ”

“እነሱማ ብዙ ናቸው ሶስቱ የኔ ጠላቶች ናቸው ማለቱ ነው” ካለ በኋላ ቀጠል አድርገው “እኔኮ ስለ ዓለም ተጠያቂ አይደለሁም” አለ ።

“አንተ በዚህኛውም ዓለም ሆነ በዚያኛው ቢሆን ተጠያቂ ነህ ትዕግሥት የተቀደሰ ነገር ነው ። ሁሉም የሚያምረው በትዕግሥት ነው” አሉ ሼኹ ፡ ሰዒድ በብስጭት ረጂም ትንፋሽ ሲተነፍስ ስለተመለከቱ ።

“ወንጀለኞቹ በሰላም ሲኖሩ ንፁሆቹ ግን ይሞታሉ” አለ ሰዒድ በሀዘን ። “መቼ ይሆን የታዘዘውን ፍርድ በጥሞና የምንቀበለው ?” ሲሉ ጠየቁት ።

“ፍርዱ ትክክለኛ ሲሆን ብቻ ነው” አለ ሰዒድ ።

“ምንጊዜም ትክክል ነው” በማለት አረጋገጡለት ።

“ወይኔ እርኩሶች ሽሹ” አለ ሰዒድ ጭንቅላቱን በማወዛወዝ በንዴት መልክ ። ሼኹም ፈገግ አሉ ምንም አልተናገሩም ። ሰዒድም ንዴቱን በማብረድ ድምፁን አለስልሶ የውይይቱን አቅጣጫ ለመለወጥ እንዳሰበ ።

“ፊቴን ወደ ግድግዳ አድርጌ ነው የምተኛው እርስዎን ለመግበኘት ከሚመጡት ሰዎች ማንም ሰው እንዲያየኝ አልፈልግም ። እምነቱ በርስዎ ስለሆነ ጠብቁኝ” አላቸው ።

“ጥበቃውም እምነትህም በአላህ ብቻ ቢሆን ይበጃል” አሉ በለሰለሰ አንደበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

“አይጠብቁኝም ማለት ነው?”

“እረ አላህ ይሰውርህ እንደሱ ማለቴ አይደለም”

“በተሰጥዎት ችሎታ ሁሉ እኔና ሰማዳን አይችሉም ?” አለ ሰዒድ ተስፋ በመቁረጥ ።

“ብትፈልግ አንተ ራስህን ማዳን ትችላለህ”

“እኔማ ንዑሀኖችን እየገደልኩ ነኝ” አለ በማሾከሾክ ከራሱ ጋር እየተወያየ ። ቀጥሎም “የገመጠውን ጥላ ማስተካከል ይችላሉን ?” ብሎ በከፍተኛ ድምፅ ጠየቃቸው ።

“እኔ ስለገመጠ ጥላዎች የማውቀው ነገር የለም” አሉ ሼኹ በለዘበ አነጋገር ።

ፀጥታ ሰፈነ ። ከጨረቃ የሚመጣ አስደሳች ብርሃን በመስኮቱ በኩል አድርጎ ከመቼውም ይበልጥ ሆኖ በነይል ወደ ጣሪያው ገባ ። በዚህ ጊዜ ሼኹ ማንብንብ ጀመሩ “ማንኛውም ውብ ነገር ከፈጣሪያችን ነው የሚመነጨው” አሉ ።

“እውነት ነው” አለ ሰዒድ ረጋ ብሎ ። ሼኹ ለማንኛውም ነገር ተስማሚ ምርጥ ቃላት አላቸው ። ቀጠል አድርጎም “ጌታዬ ምንም እንኳ እርሱ የእምነት መደምደሚያ ቢሆኑም ቤትዎ አስተማማኝ አይደለም” አለና “ከዚህ ቤት እንደምንም ብዬ መጥፋት አለብኝ ። ስለኑር ጉዳይ ግን ምን ይደረጋል ። ዕድሏ ይመር ፡ ፍትህም ርህራሄም ያጋጥማት። በጣም የሚያሳዝነው ግን ዩኒፎርሜን እንዴት ልረሳው እንደቻልኩ ነው ። በደምብ ጠቅልዬ ስነሳ ይዤ እሄዳለሁ ብዬ በመጨረሻ ሰዓት እንዴት ልረሳ ቻልኩ ። በእንቅልፍ እጦት ፡ በብቸኝነት ፡ ጨለማና ብስጭት አዕምሮዬን ሳልስት አልቀረሁም ። ውሾች ዩኒፎርሙን ካገኙ ወደ እኔ ለመምጣት

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍንጭ አገኙ ማለት ነው። ዩኒፎርሙን አሽትተው በከተማው መውጫና መግቢያ በኩል ይከታተሉኛል ፡ ያድኑኛል ፡ ጋዜጣ አንባቢዎችም ስለእኔ ታሪክ ለጀመሩት ድራማ ጥሩ አጋጣሚ ይሆንላቸዋል" እያለ ሲናገር በድንገት ሼኽ በሚያ ሳዝን ድምፅ "እኔ የጠየኩህ ፊትህን አንጋጠህ ወደ ሰማይ እንድትመለከት ነበር አንተ ግን ወደግድግዳው ነው የማደፍጠው ትላለህ !" ሲሉ ጠየቁት ።

"ስለ እርኩሶች የነገርኩዎትን አያስታውሱም እንዴ?" አለ ሰዒድ በሀዘን ሼኹን እየተመለከተ ። የችግር ስሜት እየተሰማው ዓይኖቹን ጨፍኖ ራሱን ጠየቀ ። "እንዴት ዩኒፎርሙን ልረሳ ቻልኩ ?" ሼኹ በዚህ ጊዜ ለሌላ ሰው እንደሚናገሩ መስለው "አየህ ፀሎት ብናደርግ ፡ መድሃኒትም ብንወስድ ፡ ክታብም ብናጠልቅ የተፈረደውን ፍርድ መለ ወጥ አንችልም ። የአላህ ፈቃድ ነው!" ብለው መልስ ሰጡት።

"ምን ማለትዎ ነው?" አለ በስቃይ መልክ ።

"አባትህ የኔ ንግግር አያመልጠውም ነበር"

"የሚያሳዝነው እኔ ከርስዎ ዘንድ በቂ ምግብ አላገኘ ሁም ። መጥፎ ዕድልም ሆኖ ዩኒፎርሚን ረሳሁ ። ስለዚህ የሚሉትን ልረዳው አልችልም ። ፊቱን ወደ ግድግዳው አስጠጋለሁ ያልኩት ግን እርግጠኛ ነኝ ትክክል ነኝ ።

ሼኹም በፈገግታ ለማስተዛዘን ሲሉ "ከእለታት አንድ ቀን የኔ ጌታ የሆኑት እንዲህ አሉ ፊቱ ጠቁሮ እንዳይሆን በመስጋት መስተዋት በየዕለቱ እየደጋገምኩ አላይም"

"የርስዎ ፊት?" ሲል ሰዒድ ጠየቀ ።

"የጌታዬን ፊት ነው የምልህ በማለት መለሱለት ።

"ግን እርኩሶች እንዴት አድርገው ነው በየሰዓቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፊታቸውን በመስተዋት የሚያዩ ?" አለ ሰዒድ በመገረም ።

ሺህም ራሳቸውን ደፋ በማድረግ ማንኛውም ሙበ ነብር ከአንተ ነው የሚመነጨው" አሉ ሰአላህ እንደሚናገሩ መሰለው ።

"በዕውነቱ በጣም አድርጎ ደክሞኛል ፡ ግን ሰላም ላገኝ አልችልም ፡ ዩኒፎርሙን ካላመጣሁ በስተቀር" አለ ሰዒድ ዓይኖቹን ጭፍን አድርጎ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

— 18 —

ሰዲድ ድካም ስላጠቃው ዩኒፎርሙን የማምጣቱን ሀሳብ ፈፅሞ ረሳ ። እልም ብሎ ተኛ ። ማግሽ ቀን ካለፈ በኋላ ከእንቅልፉ ነቃ ። በሌሊት ካልሆነ ለመንቀሳቀስ ስለማይችል ካለበት ሆኖ እንደ'ት እንደሚሸሽ እቅድ ማውጣት ጀመረ ። ማንኛውም ትላልቅ እርምጃዎች ግን ለጊዜው መዘግየት እንዳለባቸው አመነ ። የማንኛውም እቅድ መነሻው የታርዛን ቡና ቤት አካባቢ ስለሆነና በአውኑ ጊዜ የታርዛን ቡና ቤት አካባቢ ፖሊሶች ስላተኮሩበት ውኔታው ትንሽ ጋብ እስቲል መጠበቁ አያከራም ።

ከእኩለ ሌሊት በኋላ ወደ ነጀመዲን ጉዳና ሂደ ። ከዚያም ከክፍሉ መስኮት ብርሃን ሲወጣ በማስተዋል ቆም ብሎ አፍጥጦ ይመለከት ጀመረ ። የልቡ አደላለት ከፍተኛ ሆኖ ጅሮዎቹን ያደነቆራቸው መስሎ ተሰማው ። የደስታ ስሜትም በድንገት የሰፈነበት መሰለው ። ካለበት አዘቅትና ቅዠት ያዳነው መስሎ ተሰማው ። "ኑር ከክፍሏ አለች ማለት ነው ። የት ነበረች?" አለ ። ስለዚሁ ጉዳይ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አጣርቶ ያውቃል ። ያም ሆነ ይህ ተመልሳለች ማለት ነው ። እሷም ብትሆን እሱ ከፉኛ ተሰቃይተዋል ። አሁን ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

የማይዋሸው ስሜቱ ኑር እንደተመለሰች ያረጋግጥለታል ። በክንዱ በኃይል እቅፍ አድርጎ በዚያ በተሰበረው ልቡ ለዘላለም የሚያፈቅራት መሆኑን ይገልፅላታል ።

ወደቤቱ በደስታና በጋለ ስሜት የሰከረ መስሎ ተሽከርክሮ ገባ ። ደረጃዎቹን በከፍተኛ ስሜት በድል አድራጊነትና በሀልም ዓለም እንደተዋጠ ሆኖ ወጣቸው ። አንድ ጊዜ ያጣት እንጂ ከእንግዲህ ወዲያ ከኑር ጋር አብረው ይሸሻሉ ። ለረጅም ጊዜ ከውጭ አገር ሄደው ይኖራሉ ። እዚያም ብዙ ከቆዩ በኋላ ተመልሰው ይመጣሉ ። እርኩሶችንም ድምጥማጣቸውን ያጠፋቸዋል ።

ጫን ጫን እየተነፈሰ ከክፍሉ በር ስር ደረሰ ። "ኑር እወድሻለሁ ። በሙሉ ልቤ እወድሻለሁ ። አንቺ ካፈቀርሽኝ በእጥፍ አፈቅርሻለሁ ። በደረትሽ ላይ ሰውነቴን ፡ የርኩሶችን ክህደትና የልጇን ከኔ ነሽሽ ማለት አቀብረዋለሁ" እያለ በሀሳቡ፡ በሩን አንኳኳ ። ሲከፈት አጭር የውስጥ ልብስ የለበሰ ሰው ቆሞ አገኘ ። ሰዒድ በዚህ ጊዜ እንደ ውሃ ተኖ አመድ ብቻ መስሎ ቀረ ። ሰውየውም በመገረም አተኩሮ እየተመለከተ "ማን ትባላለህ? ምንስ ትፈልጋለህ?" አለው በጥርጣሬና በፍርሃት እየተመለከተ ። ሰዒድ ሰውዬው እንዳያውቀው በማሰብ በቅድሚያ አፉን በግራ እጁ እፍን አድርጎ ያዘው ። በቀኝ እጁም በቡጢ ሆዱ ላይ መታው ። በሁለት እጆቹ ይዞ ከክፍሉ በራፍ ድምፅ እንዳማይሰጥ አድርጎ ጠምዝዞ አስተኛው ። ወደ ውስጥ ዩኒፎርሙን ለመፈለግ ለመግባት አሰበ ። ግን ምናልባት ሰው ሳይኖር አይቀርም

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚል ጥርጣሬ አደረበት ። በዚህ ጊዜ አንድ ሴት "ማነው በሩን ያንኳኳ ጥቅሬ?" አለች ።

ተስፋ በመቁረጥ ሀሳቡን ለውጦ ደረጃዎችን እየዘለለ ወረዶ ፡ ከመንገዱ ደረሰ ፡ የመሳኒዕን መንገድ አልፎ ወደ ጀበል መንገድ አመራ ። ከዚያም አጋንንት መሳይ ሲንቀሳቀሱ አየ ። ከአንድ ግድግዳ ሥር ለጥ ብሎ ተኛ ። መንገዱ ከማንኛውም ሰው ነፃ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ጉዞውን በጥንቃቄ ቀጠለ ። እንደገና ወደ ሼኩ ቤት ገሀ ሳይቀድ ተሽሎክልኮ ደረሰ ። ሼኩም ከዚያ ከተለመደው ቦታቸው ተቀምጠው የጐህን ስግደት ጥሪ ይጠባበቁ ነበር ። ልብሱን አውልቆ ራቱን በግድግዳው ሽፍኖ ከሰሌኑ ምንጣፍ ላይ ለመተኛት ሞከረ ። እንቅልፍ ግን የሚወስደው አይመስልም። ሼኩም "ተኛ ለእንዳንተ ያለ ሰው መተኛት እንደ ፀሎት ነው የሚቆጠርለት አሉት ።" ሰዒድ ምንም ዓይነት መልስ አልሰጠም ። ሼኩ "አላህ" የሚለውን ቃል በፍጥነት እየደጋገሙ ያነበንባሉ ።

የጐህ ስግደት ጥሪ ሲደረግ ሰዒድ ገና እንቅልፍ አልወሰደውም ። ትንሽ እንደቆየም ወተት እያዞረ የሚሸጥ ሰው ድምፅ ሰማ ። መተኛቱንም ያወቀው በቅዠት ተደናግጦ ሲነሳ ብቻ ነው ። ዓይኖቹን ሲገልጥ ደብዘዝ ያለ ብርሃን ከአንድ ፋኖስ ወደ ክፍሉ ጭጋግ መስሎ ሲገባ አስተዋለ ።

"ምናአልባት አንድ ሰዓት ያህል ሳልተኛ አልቀርም" አለ ። ወደ ሼኩ መኝታ ዞር ብሎ ሲመለከት ባዶ ሆኖ አገኘው ። ከዚያም መፅሀፎቹ ወደተደረደሩበት አቅጣጫ ዞር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲል ጥብስ ስጋ ፡ የበለስ ፍራፍሬና በትንሽ ገንቦ ውሃ አገኘ ። በዝምታ ሼኩን ከልብ አመሰገነ ። "ለመሆኑ መቼ ሄደው ለማምጣት ቻሉ?" እያለ ተገረመ ። ከክፍሉ ውጭ ድምፅ ሰማ። ገረመው ። በመንፈቀቅ ትንሽ ወደተከፈተው በር ብቅ ብሎ በቀዳዳ ተመለከተ ። በጣም አድርጉ የገረመው ግን በርከት ያሉ ሰዎች ከሰሌኑ ምንጣፍ ለፀሎት ተቀምጠው ሲመለክት ነው ። ሠራተኛውም ከውጭ በር ላይ ያለውን ትልቁን ፋኖስ ሲያበራ አስተዋለ ። ፀሀይ የጠለቀች መሆኗንም አወቀ ። በሱ ሀሳብ ግን ገና ጉህ መስለት ነበር ።

ስለዚህ ሙሉ ቀን የተኛ መሆኑን ለማመን አቃተው ። ምን ዓይነት ከባድና በጣም ጥልቅ የሆነ እንቅልፍ ነው! ነገር ዓለሙን ትቶ ሀሳቡ ወደ ምግቡ ብቻ ሆነ ። ደህና አድርጉ ከበላና ከጠጣ በኋላ የውጭ ልብሱን ለብሶ ከወለሉ ላይ ተቀመጠ ። ጀርባውን ወደ መዕሐፎቹ አስደግፎ እግሮቹንም ዘረጋ ። ሀሳቡ ወደ ረሳው ዩኒፎርም እንዲሁም በሩን ወደከፈተለት አጭር ሰው ፡ ወደ ሰናአ ፡ ኑር ፡ ረዑፍ ፡ ነበዊያ ፡ ዓሊሽ ፡ ነጭ ለባሾች ፡ ታርዛንና ወደ መኪናዋ ገሰገሰ ። እንዴት አድርጉም ከበባውን በጣጥሶ እንደሚያመልጥ እንደ አውሎ ነፋስ ከአዕምሮው ላይ አቃጨለበት ። በዕውነቱ ከሆነ ትዕግሥትም ሆነ ወላዋይነት በአሁኑ ሰዓት ምንም ጥቅም እንደሌለው ማወቅ አለበት ። የሚከፈለውን መስዋእትነት ሁሉ ከፍሎ በደረቱም እየተሳበ በረሃውን አቋርጦ ከታርዛን ጋር በዛሬ ሌሊት መገናኘት አለበት ። በነገው ዕለት ግን ፖሊሶቹ በየቦታው እንደሚሰማሩ እርግጠኛ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከውጭ የእጅ ጭብጨባ ተሰማ ። የሰዎች ድምፅ ወጥ አለ ። ቦታውም ፈዕሞ እረጭ አለ ። ሼክ ዓሊ "አላህ" የሚለውን ቃል ሶስት ጊዜ ደጋገሙ ። ሌሎችም ይህን በማዕመ ዜማ ተቀበሉ ። ድምፃቸውም አንድ ግዜ ከፍ አንድ ግዜ ዝቅ እያለ የሚጓዝ ፈጣን ባቡር ድምፅ ይመስል ነበር ። በዚህ መሀል አንድ ሰው እንዲህ ሲል አንጐራጐረ ።

"መገናኘት እንኳ እንዲያ ሲናፍቀኝ
ጊዜዬም ባከነ ምንም ሳይሆንልኝ ።
የሰላሙም ተስፋ በቃ ጨለመብኝ ።
የህይወት እርገማኔ ቀኑ ቢሆን ሁለት
አንዱ ለንትርክ ሌላው ለመለያየት።"

ሰዒድ ሌሎች ሰዎች ይህን እየደጋገሙ በማድነቅ ሲያንጐራጉሩ ከመካከላቸው አንዱ በጣዕመ ድምፅ

"ጥቅር ብቻ ሲሆን የሚያንበረክከኝ
ከፊቱ ተመስጦ ከኋላዬ ዕጣ አለኝ"

አለ ። ይህ መገመር በብዙዎች ዘንድ የጋለ ስሜት አሳደረባቸው ። በበለጠ እንዲዘምሩም ገፋፋቸው ።

ከዚያም "አላህ" የሚለውን ቃል በህብረት ማዜም ጀመሩ። ሰዒድም በድምፃቸው ተማረከ ። ሌሊቱም እየገፋ መጣ ። በዚህ ጊዜ ትዝታዎች እንደጸመና እየገሰገሱ መጡ ። አባቱ ዓም ማሀራን ከሌሎች ፀሎት አድራጊዎች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተወዛወዙ ሲዘምሩ ፡ እሱ ከዘንባባዋ ዛፍ አጠገብ ቁጭ ብሎ ትርዒቱን በመገረም ሲመለከት ታየው ። እንድ ነገርም ትዝ አለው ። እሱም ነፍስ ከሞት በኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለዘልዓለም እጅግ በጣም ሩህሩህ በሆነ ጌታ ዘንድ እንደምት
ጠበቅ እንዲሁም ትዝታው አረንጓዴ መስክን ጨርሶ አንድ
ዛፍ ብቻ ወዳለችበት ቦታ የመጀመሪያው ፍቅሩ ወደ ተጠነሰ
ሰበትና ሰናእ ልጁንም ታቅፎ በህፃንነት ምላሷ እየተኮላተ
ፈች የሆኑ ቃሎችን ስትናገር ትዝ አለው ። ከዚያም በጣም
ኃይለኛ ነፋስ ከሲኦል ሲነፍስ ተሰማው ። አከታትሎም
ከግጭት የሚፈጠር ዓይነት ድምፅ ተሰማ ። በዚሁ ጊዜ
ዘማሪዎቹ በመሪያቸው በኩል ዝማሬያቸውን አንጐራጐሩ ።

“መቼ ይሆን ከቶ ዕረፍት የማገኘው
ጊዜዬ በከንቱ እንዲሁ የሚያልፈው ።
ዕጣ አይሉት ዕድል ይጠባበቀኛል
ድልንም አላገኝ ምንስ ይሻለኛል?”

ይህ በኪሱ ውስጥ በተጠንቀቅ የሚገኘው ሽጉጥ አንድ
ተአምር ይሠራ ይሆናል ፣ ክህደትንና ብኩንነትን ድል
ያደርግ ይሆናል ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሌባው ውሾችን ያባር
ራል ።

ሳይታሰብ ከክፍሉ መስኮት ሥር በውጭ በኩል አንድ
አስደንጋጭ የሆነ ድምፅ ተሰማ ። ውይይትም አስከተለ ።

“ምን ዓይነት ነገር ነው ሰፈሩ በሙሉ ለምን ተከበበ!” አለ
አንድ ሰው በመገረም ።

“ከጦርነት ጊዜም የባሰ ሆኗል አይደል?” አለ ሌላው ።

“በሰዒድ ምክንያት ነው” አለ ሶስተኛው ።

ሰዒድ ባለበት ክው አለ ። ኤሌክትሪክ እንደጨበጠ ሰው
ሆነ ። ሽጉጡን በጥንቃቄ አጥብቆ ይዞ የደም ሥሮቹም በሙሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቆጠ ተገኑተሩ ። በአይኖቹ ግራና ቀኙን ታኘ ። ብዙ ሰው በአካባቢው ይኑየል ። ለነሱ ለባሾችም እንደዚህ ያለ-ት ሁኔታዎች ሠርግ ነው ።

"ነገሮቹ ከእጇ እንዳያመልጡ ማድረግ አለብኝ" አለ ሰዒድ በሀሳቡ ። በአሁኑ ጊዜ ዩኒፎርሙን እየመረመሩ ይሆናል። ውሾችም ከዚያው ሊኖሩ ይችላሉ ። እኔ ከዚህ ከተጋለጠ ቦታ ነው ያለሁት ። የበረሃው መንገድ ፀጥታው አስተማማኝ አይደለም ። ግን የሞት ሽለቆ እየተባለ የሚጠራው ከዚያ አቅራቢያ ስለሆነ ከዚያ ሄጇ ነው እስከሞት ድረስ የምዋጋቸው" አለ ።

ብድግ ብሎ ወደበሩ ተንቀሳቀሰ ። ሽኩና ተከታዮቻቸውም ጣዕመ ዜማ እያሰሙ ውዝዋዜያቸውን ቀጥለዋል ።

ወደ ውጭ በር የሚወስደው መተላለፊያ ነባ ነው ። በዚያ በኩል አድርጎ ወደ ዋናው ጉዳና ገባ ። ከዚያም ወደ ግራ ተጠመዘዘ ። ረጋ ብሎ በተረጋጋ አረማመድ ወደ መኖሪያ ቤታ አመራ ። ሴሊቱ እየተጠናከረ መጣ ። ፈሐረቃም አልነበረችም ። በፈለማ ምክንያት መሄድ አቃተው ። ጥቁር ግድግዳ ከፊቱ የተደቀነበት መስሎ ታየው ። ወደፊት መሄዱንም ሆነ ወደኋላው ለመለየት አልቻለም ። አንድም ተስፋ ያሰው ብልጭታ ባይታየውም ቅሉ እንቅስቃሴው ግን ከመጠን በላይ ነበር ። ከሞታቱ ዓየር ጋር ሜዳዲታ አብሮ መጣ። "ምነው ተብሩ በሞጠኝ?" ብሎ ተመኘ ። ሆኖም ንብሙን አላቋረጠም ። ውሾችን ይፈራ ነበር ግን ምን ማድረግ ይቻላል። ለማቆምም ጉዩል የለውም ። ከጥቂት ደቂቃዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

በኋላ ወደ መጨረሻ የመቃብሩ ረድፍ ደረሰ ። ከፊቱም አንድ የታወቀ ምልክት ለመለየት ቻለ ። በስተሰሜን በኩል ያለውን የመቃብሩን መግቢያ ከነጀመዲን ጐዳና ጋር የሚያገናኝ ነው አቤት! ከዚህ የኑር ቤት ይታያል ። ብቸኛው ክፍል እንሆ ይታያል ። ወደ መስኮቱም እያመለከተ "ክፍት ነው ። ብርሃንም ከዚያ ሲወጣ ይታያል" አለ ። አፍጥጠ አስተዋለ ። በመስኮቱ የሴት ቅርፅ ያየ መሰለው ። ምንም እንኳን ፊቷ በትክክል ባይታይም የጭንቅላቷ ቅርፅ የኑር ሳይሆን አይቀርም አለ ። ኑር ተመለሰች ማለት ነው? እረ አሁንም ዓይኖቹ እያታለሉት ነው ። "ከአሁን በፊት ስሚትህ እንደአታለለህ መታለል በዛብህ ። ይህም የሚያመለክተው የህይወትህ መጨረሻ ምዕራፍ ወደሆነው መድረስህን ነው!" አለ በሀሳቡ።

"መቼም የምመለከታት ሴት ኑር ብትሆንልኝ የመጨረሻ ቃሌን ከመስጠቱም በላይ አደራ ስለ ሰናእ ልጇ እላት ነበር ። ምንም እንኳን አደጋ ላይ ብሆንም ጮክ ብዬ የፊልኩትን በነገርኳት ነበር ። አለ ከአፉ ድምፅ ሳይወጣ ።

ውሾቹ ከሩቅ መጮህ ጀመሩ ። ጩኸታቸውም ወጥታ የሰፈነበትን አካባቢ አደፈረሰው ። የጥይት ኳኳታ ያስተጋባ ጀመር ። ሰዓድ በመስጋት ወደኋላው አፈገፈገ ። ከመቃብሮች መካከል ገባ ። ጩኸቱም እየተባባሰ መጣ ። ጀርባውንም ከአንድ ቀብር አስደግፎ ሽጉጡን ደቅኖ ዓይኖቹን አፍጥጦ በጨለማ ያመለክት ጀመር ። ከዚህ ዓለም የሚሰናበትበት ሰዓት መድረሱን አረጋገጠ ። በመጨረሻም ውሾች መጡ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ተስፋው አከተመ ። እርኩሶችም ነፃ ወጡ ። ህይወቱ አጉል መሆኗን አመነ ። የውሾች ዋይታ ከንፋስ ጋር በየአቅጣጫው ስለሚመጣ የድምፁን አቅጣጫ ለመለየት ዘበት ሆነበት ። ይህ ድቅድቅ ያለ ጨለማ ለመሮጥ አያመችም ። እርኩሶች ነፃ ወጡ ። ህይወትህ ግን አጉል ጠፋች ። ዋይታው እየተጠናከረ ስለመጣ ሽጉጡን በንዴት አሽከረከረው ። በዚህ ጊዜ የፀሐይ ብርሃን የሚመስል ከፍተኛ መብራት አካባቢውን ቁልጭ አድርጐ አበራው ። ዓይኖቹን ጭፍን አድርጐ ከቀብሩ ሥር ሰጥ ብሎ ተኛ ።

"እጅህን ስጥ ከእንግዲህ ለመከላከል መሞከር ዋጋ የለውም" ከፖሊሶቹ አንዱ ፈክ ብሎ በድል አድራጊነት ድምፅ አስጠነቀቀው ።

ቦታው በከባድ የሰዎች ኮቴ ተናወጠ ። ብርሃንም እንደ ፀሐይ አካባቢውን አጥለቀለቀው ።

"ሰዒድ እጅህን ስጥ" አለ አንድ ሌላ ፖሊስ ።

ሰውነቱ ከመቃብሩ ጋር ተጣበቀ ። ለመተኮስ ተዘጋጀ ። "እጅህን ስጥ ለሰው ልጅ ሊደረግ የሚገባው ርህራሄ እንደሚ ደረግልህ አረጋግጣለሁ!" አለ አንድ ግርማ ያለው ድምፅ ።

"እንደ ረፀፍ ፡ ነበሚያ ዓሊሽና ውሾች ያለ ርህራሄ ነው?" አለ በሀሳቡ ።

"ተከበሃል ። መቃብሩ በሙሉ ተከቧል ። ደህና አድርገህ አስብና እጅህን ስጥ" የሚል ሌላ ማስጠንቀቂያ ሰማ ።

ሰዒድ ግን መቃብሮቹ ከዚህም ከዚያም ተበታትነው ስለሆኑ ልታይ አልችልም የሚል ዕምነት አደረበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እስክሞት ድረስም መዋጋት አለብኝ ብሎ ወሰነ ።

"ያሁን መንፈራገጥ ምንም ፋይዳ እንደሌለው አይሰማህም እንዴ?" አለ አንዱ በተረጋገጠ ድምፅ ።

"ወየውለት ወደኔ ለሚቀርብ ሰው! አለ ሰዒድ ሳይወድ የፖሊሶች ድምፅ እየቀረበ መምጣቱ ሲሰማው ።

"እሺ ምን ለማድረግ ነው የምትፈልገው? ከሞትና ፍትህ ከማግኘት ምረጥ"

"ፍትህ!" አለ በማሽሚጠጥ ።

"አንተ እኮ እልከኛ ነህ ለውሳኔ አንድ ደቂቃ ጊዜ ብቻ ነው የምንሰጥህ"

በፍርሀት የተጐሳቆሉ ዓይኖቹ የሞት ጥላ ጨለማውን አቋርጦ ሲመጣ ተመለከቱ ። ሰናእም ተስፋ በመቁረጥ ከሱ ሸሽታ ስትሮጥ ታየው ። በዚህ ጊዜ ተንኮለኛ እንቅስቃሴ ሰማ። በንዴት ተኩስ በየአቅጣጫው የጥይት ውርጅብኝ ዱዱ! ኳኳ! እያለ እንደበረዶ ወረደበት ። የጀሮዎቹ ሥሮች የተበጣጠሱ መሰለው ። የቀብሩም ድንጋይ ፍንጣሪዎች ሲያበሩ ታየው ። ለሁለተኛ ጊዜ ተኮሰ አሁንም ጥይት እንደዝናም ወረደበት ።

"ውሾች!" አለ ሰዒድ እንደዕብድ ጮክ ብሎ በየአቅጣጫው ተኩሱ ቀጠለ ።

በድንገት ኃይለኛው ብርሃን ጠፋና አካባቢውን ጨለማ ዋጠው ። ተኩሱም ፀጥ ብሎ ዝምታ ሰፈነ ። ዓለም ፀጥ አለች። እሱም ተገረመ ። ብዙ ጥያቄዎች በአዕምሮው መጡበት ። ግን ጥያቄዎችን አቋረጠና : "እነዚህ ሰዎች ወደኋላ አፈግፍገው

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆን ወይም ሉሊቱ ውሏቸው ይሆን? ይህ ከሆነ አሸነፍኩ ማለት ነዋ!" አለ በሀሳቡ ።

ጨለማው በጣም ከባድ ስለነበረ የመኰብሮችንም ቅርፅ ቢሆን ለመለየት አልቻለም ። በሀሳቡም ነጐደ ። በዚህ ጊዜ ምንም ቦታና ዓላማ እንደሌለው ሆኖ ተሰማው ። አንድ ዓይነት እርምጃም ለመውሰድ አቃተው ። የመጨረሻውን ፍልሚያ ለማድረግ አንድ ትልቅ ጅብዱም ለመፈፀም አሰበ ። ነገር ግን እጅ ከመስጠት የማያመልጥ መሆኑ ተረጋገጠለት ። በመጨረሻ በግዴለሽነትና በደንታ አልባነት እጁን ሰጠ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቃላት ትርጉም

ሙዓለም	መምህር ማለት ሲሆን በግብፅ አገር በዘልማድ ለአንዳንድ ኒጋደምች በተለይ ለባለ ቡና ቤት ጌታ የሚሰጥ ቅፅል ስም ነው ።
ጀለቢያ	በልዩ ልዩ የዓረብ አገሮች የሚለበስ ግራና ቀኝ ተከፋች የሉለው ረዥም እጄ ጠባብ የሚመስል አንድ ወጥ ልብስ ነው ። በግብፅ አገር አብዛኛውን ጊዜ በገጠር ነው የሚለበሰው ።
ጀበል	ተራራ ማለት ነው ።
ገከር	በፀሎት ፡ በመፀመርና በውዝዋዜ በተለይ የነቢዩ መሐመድ ታሪክና ሰውነትን በማውሳት የሚደረግ ውዳሴ ነው ።
ዓፆ	አጌት ፡ የእባት መንድም ማለት ሲሆን ጋቬ በማለት ይጠቀሙበታል ።
አላህ	እግዚአብሔር ማለት ነው ።
ወዲኽ	ከስግድትና ቁርዓን ከመንካት በፊት የተመሰኑ አካላትንና መታጠብ ማለት ነው ።
ሙተወፎ	በካይሮ ከተማ ከልል የሚገኝ ተራራ ።
ኑር	ብርሃን ማለት ሲሆን ለወንድም ፡ ለሴትም የመጠሪያ ስም ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አዛን — ለስግደት የሚደረግ ጥሪ ነው ።

አቡልሆል — አስፈንከስ ማለት ሲሆን ፡ ከፒራሚድ ጐን ያለ ታሪካዊ ሐውልት ነው ። ደራሲው የአንድ ታዚማ መመሪያ ስም እንዲሆን አድርገውታል ።


ሳቢር — ታጋሽ ማለት ነው ።

ረዑፍ — የወንድ ስም ሲሆን ሩህሩህ ማለት ነው ።

አልነዚር — ማስጠንቀቂያ ማለት ነው ።

አህመድ አህመዲን

t.me/OLDBOOKSPDF



t.me/OLDBOOKSPDF